ቀን Date ጥር 06 2018
ቁጥር Ref.No 3.1/208/18

**በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ**
**ባሉበት**

ጉዳዩ፡- **<u>የኤክሳይዝ ታክስ የአሰራር ማኑዋሎችን መላክን ይመለከታል</u>**፤

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (እንደተሻሻለው) እና መመሪያ ቁጥር 1071/2017፣ 1072/2017 እና 1079/2017 አፈፃፀሙን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግና በሁሉም ቅ/ፅ/ቤቶች ወጥ የሆነ የኤክሳይዝ ታክስ አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት ከታክስ ትራንስፎርሜሽን ፅ/ቤት ጋር በመተባበር የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰር ማኑዋል፣ የኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች ማኑዋል እና የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋሎች ተዘጋጅተዋል።

ስለሆነም እነዚህ ማኑዋሎች ተግባራዊ እንደደረጉና ስራዎች በማኑዋሉ መሰረት እንዲከናወኑ እና የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰር ማኑዋል እና የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋል ለታክስ ባለስልጣን መ/ቤቱ አመራር እና ሰራተኞች እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች ማኑዋል ደግሞ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርቱ አምራች ድርጅቶችና አስመጭዎች እንዲያውቁትና እንዲደርሳቸው እንዲደረግ እናሳስባለን።

"ከሠላምታ ጋር"

ዮሴፍ በፈራሙ
የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

**<u>ግልባጭ</u>**

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ
- ለታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
- ለተቋማዊ ስጋት ስራ አመራርና ስነ ምግባር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዘርፍ አገ/አስ/ማሻሻያ ሪፎርም ፅ/ቤት
- ለታክስ ትራንስፎርሜሽን ፅ/ቤት

**<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>**

**በአባሪ የተዘረዘሩት**

ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት

ለምስራቅ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለምዕራብ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለሰሜን ምዕራብ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

**አዲስ አበባ**

ለባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ባህር ዳር/

ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /አዳማ/

ለመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /መቐለ/

ለኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/

ለሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሀዋሳ/

ለጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅማ/

ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ድሬዳዋ/




የገቢዎች ሚኒስቴር

# የኤክሳይዝ ታክስ የኢንስፔክሽን ማኑዋል

የታክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት

ከታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የተዘጋጀ

ጥቅምት 2018



| | |
|---|---|
| ማኑዋሉን ያዘጋጀው፡ | ፊሊፕ ግሪፍዚስ (Philip Griffiths (TTP)) |
| ግምገማውን ያካሄደው፡ | ተመሰገን ታከለ |
| የተዘጋጀበት ጊዜ | ግንቦት 2017 |
| በቀጣይ የተያዘው የግምገማ መርሃ-ግብር፡ | ግንቦት 2019 |
| የግምገማው ማሻሻያዎች፡ | |
| በድጋሜ የከለሰዉ | |
| ያፀደቀው | |

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር የሰነዶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

Table of Contents


ምዕራፍ አንድ፡ የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ..... 9

1. መግቢያ ..... 9

1.1 የማኑዋል ዋነኛ ዓላማ ..... 9

1.2 ዝርዝር ዓላማዎች ..... 10

1.3. የማኑዋሉ አጠቃቀም ..... 10

1.4. ማጠቃለያ ..... 12

ምዕራፍ ሁለት፡ የዕቅድ ዝግጅት ..... 13

2. መግቢያ ..... 14

2.1. የተጠቅላላ የኢንስፔክሽን ዕቅድ ዝግጅት ..... 14

2.1.1. የኢንስፔክሽን መረጣ ..... 14

2.1.2. የንግድ ሥራዎች ውስብስብነት ..... 14

**2.1.3. ግብር ከፋዮችን መምረጥ** ..... 17

2.1.4. ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ብቁ የሆኑ የቡድን አባላት ..... 17

2.1.5. ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን የቡድን አባላትን መምረጥ ..... 19

2.1.6. መደበኛ ክትትል ..... 19

2.2. የዕቅድ ዝግጅት ምዕራፍን ማከናወን ..... 20

**2.2.1 ስጋቶችን መለየት** ..... 20

2.2.2. ድርጅቱን እና የሥራ እንቅስቃሴዎችን መረዳት ..... 20

2.2.3. ዝርዝር የዕቅድ ዝግጅት ..... 22

2.2.4. የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ ..... 23

2.2.5. የሚታዩ መረጃዎች ..... 27

2.2.6. ሁለተኛ የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ ..... 28

2.2.7. የቁጥጥር ፕሮግራም ..... 29

2.3. ጉብኝትን ለኤክሳይዝ ታክስ ክፋይ ማሳወቅ ..... 29

ምዕራፍ ሦስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋል፡- አፈፃፀም ..... 31

3.1. የኢንስፔክሽን አፈፃፀም መግቢያ፡- አጠቃላይ ..... 32

3.1.1. የፀደቁ ቅጾች ..... 32

**3.1.2. አጠቃላይ መርሆዎች** ..... 32

**3.1.3. በኢንስፔክሽኑ ወቅት** ..... 33

**3.1.4. የመዝጊያ አያያዝ ሥርዓቱን ይረዱ** ..... 33




የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ የሰነድ አስተዳደር ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

3.1.5. የማምረቻ ቦታ ጉብኝት ..... 34
3.1.6. ኢንስፔክሽኑን ማካሄድ፡ በኢንስፔክሽን አይነት ..... 35
3.1.7. ማጠቃለያ ..... 35
3.2. የኢንስፔክሽን አይነቶች፡ ዝርዝር አፈፃፀም ..... 36
3.2.1. መግቢያ ..... 36
3.3. ፈቃድ አሰጣጥ፡ የፈቃድ አሰጣጥ ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ..... 36
3.3.1. ፈቃድ ለሚፃኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ስለመቀበል ..... 36
3.3.2. የቀረበውን ማመልከቻ ማጣራት ..... 37
3.3.3. ማመልከቻን በመቀበል ሂደት የሚጠየቁ የማረጋገጫ ጥያቄዎች ..... 37
3.3.4. ለጉብኝቱ ዝግጅት ማድረግ ..... 38
3.3.5. ጉብኝቱን ማቀድ እና ጉብኝት ማካሄድ ..... 38
3.3.6. ከጉብኝቱ ቡኋላ ..... 38
3.3.7. የክትትል እርምጃ ..... 39
3.3.8. ነባር ግብር ከፋዮች ..... 39
3.4. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆን ዋጋ ..... 40
3.4.1. መግቢያ ..... 40
3.4.2. የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ የሚሰላበት ዋጋ፡- ኢንስፔክሽን ..... 41
3.4.3. ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ..... 42
3.4.4. ከኢንስፔክሽኑ በፊት የሚገመገሙ ሰነዶች እና መረጃዎች ..... 42
3.4.5. መረጃውን መሰብሰብ ..... 42
3.4.6. መረጃውን መተንተን ..... 43
3.4.7. ለኤክሳይስ ታክስ የዋጋ ቁጥጥር የቅድመ-ኢንስፔክሽን ሰብሰባ ..... 44
3.4.8. በኢንስፔክሽኑ ወቅት ..... 45
3.4.9. ማጠቃለያ ..... 45
3.5. የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ትርጓሜ እና አመዳደብ ..... 47
3.5.1. መግቢያ ..... 47
3.5.2. ትርጓሜዎች/ሲያሚዎች ..... 47
3.5.3. የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔዎች ..... 48
3.5.4. ሸጋቶች ..... 48
3.5.5. ምርቱ ቲኮር ትርጓሜዎች (Specific definition) ..... 49
3.5.6. ምርቶችን መመርመር ..... 51



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

3.5.7. የአልኮል ጥንካሬ ..... 52
3.5.8. የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች ..... 52
3.5.9. ብራንዶች እና ዋና መረጃ ..... 52
3.5.10. ለትንተና የሚያግዙ መረጃዎች ..... 53
3.5.11. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች(Working notes) ..... 53
3.5.12. ማጠቃለያ ..... 54
ክፍል 3.6. ጥሬ ዕቃዎች ..... 54
3.6.1. መግቢያ ..... 54
3.6.2. የገቢ ስጋቶች ..... 55
3.6.3. መዝገቦች ..... 55
3.6.4. የሚያስፈልጉ መረጃዎች መረጃዎች ..... 56
3.6.5. መረጃውን መሰብሰብ ..... 56
3.6.6. መረጃውን መተንተን ..... 57
3.6.7. ሽለታሰበው ጉብኝት እና የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ ለግብር ከፋዩ ማሳወቅ ..... 57
3.6.8. የቁጥጥር እቅድ ..... 58
3.6.9. የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም ላይ የሚጣል ዝቅተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጫኔ አጠቃቀም ..... 58
3.6.10. የሚያስፈልጉ መረጃዎች ..... 59
3.6.11. የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን አላማዎች ..... 60
ክፍል 3.7: ከጥሬ ዕቃ የሚጠበቅ ምርት ወይም ያለቀለት ምርት ኢንስፔክሽን ..... 62
3.7.1. መግቢያ ..... 62
3.7.2. የገቢ ስጋቶች ..... 62
3.7.3. መዝገቦች ..... 62
3.7.4. የሚያስፈልጉ መረጃዎች ..... 63
3.7.5. መረጃውን መሰብሰብ ..... 63
3.7.6. መረጃውን መተንተን ..... 64
3.7.7 የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ..... 65
3.7.8. በኢንስፔክሽኑ ወቅት ..... 65
3.7.9. ማረጋገጫ የሚካሄድባቸው መዝገቦች ..... 66
3.7.10. ከጥሬ ዕቃዎች የሚጠበቅ የምርት መጠን/ገደብ ..... 66
3.7.11. መረጃ ..... 67



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

3.8. የብክነት / ብልሽት ኢንስፔክሽን ..... 69
**3.8.1. መግቢያ** ..... 69
**3.8.2. ስጋቶች** ..... 69
**3.8.3. መዝገቦች** ..... 69
**3.8.4. የሚያስፈልጉ መረጃዎች** ..... 70
**3.8.5. መረጃውን መሰብሰብ** ..... 70
**3.8.6. መረጃውን መተንተን** ..... 71
**3.8.7. የኢንስፔክሽን እቅድ** ..... 71
**3.8.8. በኢንስፔክሽኑ ወቅት** ..... 72
**3.8.9. መረጃ** ..... 72
ክፍል 3.9: ከፋብሪካ የሚወጡ ዕቃዎች ላይ የሚካሄድ ኢንስፔክሽን ..... 73
**3.9.1. መግቢያ** ..... 73
**3.9.2. ቅድመ-ኢንስፔክሽን** ..... 73
**3.9.3. በኢንስፔክሽኑ ውስጥ የሚጠየቁ ሰነዶች** ..... 74
**3.9.4. የመረጃ ትንተና** ..... 74
**3.9.5. የመረጃ እና ትንተና ማጠቃለያ** ..... 74
**3.9.6. በኢንስፔክሽኑ ወቅት** ..... 75
3.10. የምርት እና የማሽጊያ ኢንስፔክሽን ..... 76
**3.10.1. መግቢያ** ..... 76
**3.10.2. መዝገቦች** ..... 76
**3.10.3. የሚያስፈልጉ መረጃዎች** ..... 76
**3.10.4. መረጃውን መሰብሰብ** ..... 77
**3.10.5. መረጃውን መተንተን** ..... 77
**3.10.6. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች** ..... 77
**3.10.7. በኢንስፔክሽኑ ወቅት** ..... 77
**3.10.8. ማረጋገጫ የሚካሄድባቸው መዝገቦች** ..... 78
**3.10.9. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች** ..... 78
3.11. የመለኪያ እና የመቁጠሪያ መሣሪያዎች ..... 78
**3.11.1. መግቢያ** ..... 78
**3.11.2. ሜትሮሎጂ** ..... 78
**3.11.3. ትክክለኛነት** ..... 79



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 መዛግብትና ያለመንቀሳቀስ
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

**3.11.4. የመሣሪያዎች የንባብ ድግግሞሽ** ..... 79
3.12. ከማሽኒያ እስከ ማከማቻ እንዲሁም የቆጠራ ማመሳከሪያ ኢንስፔክሽን ..... 81
**3.12.1. መግቢያ** ..... 81
**3.12.2. የሚጠበቁ መዝገቦች እና የማከማቻ መሰረርቶች** ..... 81
**3.12.3. የሚተነተኑ መረጃዎች** ..... 81
**3.12.4. በቦታው ላይ የሚከናወኑ ተግባራት** ..... 81
3.13. የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ..... 82
**3.13.1. መግቢያ** ..... 82
**3.13.2. መረጃ** ..... 82
**3.13.3. ስጋቶች** ..... 83
**3.13.4. የመዝንብ አያያዝ ሥርዓቶች** ..... 83
**3.13.5. ነፃ የአየር ሰዓት** ..... 83
**3.13.6. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች** ..... 83
ምዕራፍ 4፡ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች(working notes) ..... 85
4.1. መግቢያ ..... 85
4.2. የኤክሴል ሠንጠረዥ ..... 85
4.3. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶቹን / የኤክሴል ሠንጠረዦቹን ለሥራ ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ ..... 85
4.4. ከኢንስፔክሽኑ በፊት ጥቅም ላይ የሚውሉ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ..... 86
4.5. ግብር ከፋይን ስለማሳወቅ ( Notify Taxpayer) ..... 93
4.6. በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ የስራ ማከናወኛ ሰነዶች ..... 93
6.5 ፡ ለሎች መተማመኛዎች ..... 98
ምዕራፍ አምስት፡ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች፡ ለእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን ዓይነት የቀረቡ ማሳያ ምሳሌዎች(Templates) ..... 99
5.1. መግቢያ ..... 99
5.6 የምርት ትርጓሜዎች እና አመዳደቦች(classification) ..... 112
5.7. ጥሬ ዕቃዎች፡- በሀገር ውስጥ የሚመረቱ እና ከውጭ የሚገቡ ..... 114
5.7. የባከኑ / የተበላሹ ምርቶች ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን ..... 117
5.7. ከማምረት እስከ ማሸግ ያለው ሂደት ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን ..... 121
5.8. የመለኪያ እና መቁጠሪያ ኢንስፔክሽን ..... 124
5.9. ከማሽኒያ ጀምሮ እስከ ማከማቻ እና ዕቃ ቆጠራ ድረስ የሚደረግ ማስታረቅ ..... 127
5.9.1. የሚጠበቀው ምርት (expected yield)፡- ከጥሬ ዕቃ እስከ የመጨረሻ ምርት የሚደረግ ኢንስፔክሽን ..... 127



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ዕቅ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

5.10. ከፋብሪካ የሚወጡ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን ..... 130
5.11. የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኢንስፔክሽን ..... 136



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

# ምዕራፍ አንድ፡ የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን

## 1. መግቢያ

የኤክሳይዝ ታክስ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚመረቱ እና/ወይም ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ የተወሰኑ ምርቶች ላይ የሚጣል ታክስ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ብዙ ዕቃዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም የአልኮል እና አልኮል አልባ መጠጦችን፣ የትምባሆ ምርቶችን፣ አልባሳት ጨርቃ ጨርቅእና ሌሎች በአዋጁ ሰንጠረዥ ሁለት የተዘረዘሩትን ይጨምራል ::

የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርና አሰባሰብ ወደ አገር በሚገቡ (በጉምሩክ ቁጥጥር በሚደረግባቸው) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ በሚጣል የኤክሳይዝ ታክስ እና በአገር ውስጥ በሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ በሚጣል የኤክሳይዝ ታክስነዉ፡፡ ይህ የአሠራር ማኑዋል በአገር ዉስጥ በምመረቱ ኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸዉ ምርቶች ጋር በተያያዘ የቁጥጥር ጽንሰ ሃሳቦችን እና ሂደቶችን ያብራራል፡፡

ይህ ሰነድ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 እንደ ተሻሻለዉ (1287/2015) በመመሪያ ቁጥር 1071/2017 በኤክሳይዝ ታክስ ቴምብር አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1072/2017፣እና የኤክደሳይዝ ታክስ ቁጥጥር መመሪያ 1079/2017 የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 መሠረት የሚደገፍ ነዉ ::

ይህ ሰነድ ፈቃድ የተሰጠውን የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ የመረዳትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ላለባቸው ለሁሉም ኦፊሰሮች ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሰነዱ የአገር ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስየሚከፈልባቸዉን ምርቶች የሚያጠቃልል በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸውን ዕቃዎች ከሚያመርቱ ግብር ከፋዮ የሚሰበሰበዉን የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ይመለከታል፡፡ (ሆኖም አንዳንድ ጥሬ ዕቃዎች ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው በጥሬ ዕቃዎች ላይ ለሚደረገዉ ቁጥጥር ከጉምሩክ ኮሚሽን መረጃ መዉሰድን ይጠይቃል)፡፡

በዚህ ሰነድ የተቀመጡትን መመሪያዎች እና ጽንሰ-ሐሳቦች መከተል ስንችል የሚከተሉትን ነጥቦች ለማሳካት ጥረት እያደረግን ነው ለማለት እንችላለን፡-

- በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የሀገር ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች ጋር በተያያዘ የእኩል አረዳድ እንዲኖር ማድረግ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርአግባብ እና የሕግ ተገዢነትደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ማረጋገጥ፤ እና
- የግብር ከፋዮች የኤክሳይዝ ታክስ የማስታወቅ የሕግ ተገዢነት ደረጃ እንዲጨምር ማድረግ፡፡

ለማናቸውም ዝርዝር ማብራሪየዎች በተመለከተ የኤክሳይዝ ታክስ ኦፊሰርስ ማኑዋል ይመልከቱ፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ደህመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

## 1.1 የሚኑዋል ዋነኛ ዓላማ

በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር መስፈርቶች ውስጥ የተዘረጋውን የቁጥጥር ሥርዓት በመከተል ከፈቃድ አሰጣጥ ጀምሮ የኤክሳይዝ ታክስን እስከ ማስታወቅ እና መክፈል ድረስ ባለው ሂደት የኤክሳይዝ ታክስ ሕግን ማስከበር እና የሕግ ተገዢነትን ማረጋገጥ፡፡ እንዲሁም በሁሉም የፌዴራል ገቢ ሰብሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው አካሄድ እና አሠራሮችን መዘርጋት፡፡

## 1.2 ዝርዝር ዓላማዎች

በዚህ ማኑዋል የተቀመጡትን አሠራሮች በመከተል የሚከተሉት ዓላማዎች እንዲሳኩ ይጠበቃል፡-

- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርሁኔታን ይበልጥ የተደራጀ ለማድረግ ፤
- በኤክሳይዝ ታክስ ገቢ ሰብሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች የታክስ ተቋማት መካከል የሚኖርየስራ ግኑኝነትን ለማጠናከር፤
- የሚቀርቡ የታክስ ማስታወቂያዎች እና የፀደቁ ቅጾችን በመጠቀም የተሻለ የመረጃ ትንተና ለማከናወን ፤
- የኤክሳዝ ታክስ መዝገቦች ደረጃውቸወን በጠበቀ መንገድ እንዲያዙ በማስቻል የታክስ ከፋዮች ትምህርን ለማጉልበት ፤
- በኢንዱስትሪው ያሉትን አዝማሚያዎችን ለመለየት ከኢንስፔክሽንና ከመረጃ የተገኘ የኢንዱስትሪ ዕውቀት ለማግኘት እና፤
- ሌሎች ቀልጣፋ የሆነ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርና ወጥ አሰራር በመዘርጋት፣ ከኤክሳይዝ ታክስ የሚጠበቀዉን ገቢ መሰብሰብ እና የሕግ ተገዢነትን ለማሳደግን ፡፡

የኢንስፔክሽን ሥራዎቹ እያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የስጋት አካባቢን ይሸፍናሉ፡፡ እያንዳንዱን የስጋት አካባቢ በተናጠል በመመልከት የእያንዳንዱ ታክስ ከፋይ የሕግ ተገዢነት እና የእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከጫፍ እስከ ጫፍ ይተነተናል፤ ይመረመራል፤ በዚህም የሕግ ተገዢነት እና ገቢ ይጨምራል፡፡

የሚከተሉት የኢንስፔክሽን ሥራዎች በዚህ ውስጥ ይጠቃለላሉ፡-

| | |
|---|---|
| የየኤክሳይዝ ፈቃድ አሰጣጥ ኢንስፔክሽን | ይህ ለአዲስ ፈቃድ አመልካቾች መከናወን የላባቸዉ ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | ይህ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን በማረጋገጥ ላይ ያተኩራል፡፡ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ዋና መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና ትርጉማቸዉ | ይህ ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ ጥቅም ላይ መዋሉን ወይም አለመዋሉን በመለየት ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን፡- ከውጭ የሚገቡ እና የሀገር ውስጥ | ይህ በጥሬ ዕቃ አጠቃቀምና ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ በሚያመርቱ ምርት የጥሬ ዕቃዎቹ ብዛትና መገኛቸውን(source) ማረጋገጥ በሚችልበት መንገድ ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የመጨረሻ ምርት / የምርት ውጤት ኢንስፔክሽን | ይህ ለተለያዩ የኤክሳይዝ ታክስ ከተጣለባቸው ምርቶች የሚጠበቁ የተለያዩ የምርት ውጤቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ከተቀመጠው መጠን ውጭ የሆነን ማንኛውንም የምርት ብዛት ለማጣራት ይህንን እንደ መነሻ መጠቀም ይቻላል፡፡<br><br>ይህ ኢንስፔክሽን ማንኛውም የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያ ላይ እንዲሁም የርቀት መከታተያ መሣሪያ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚደረግ ክትትልና ማጣራትን ይጨምራል፡፡ |
| የባከኑ ወይም የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | ይህ ከማምረቻ እና ማከማቻ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ይህም በዕቃ ቆጠራ ቅጹ እና በማስታወቂያ ቅጹ ላይ የተመዘገቡት ብክነቶች እና የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎችን የተመለከቱት መረጃዎች ከመሣሪያዎች እና ከማምረት ሂደት ጋር የተጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ |
| ማምረቻ እና ማሽጊያ | የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረቻ እና ማሽጊያ መሳሪያዎች ልከትና የምርቶቹን ትክክለኝነት(መጣጣም) ማጣራት፡፡ |
| የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያ/የርቀት መከታተያ | ይህ የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያዎች በትክክል እንዲሠሩ መፈተሻቸውን እንዲሁም ትክክል መሆናቸውን እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡ |
| ከማሽጊያ እስከ ማከማቻ | የተመረተው እና የታሸገውን የምርት ብዛት በማከማቻ ካለው ጋር በማስታረቅ ያረጋግጣል፡፡ |
| ከፋብሪካ ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | ይህ ወደ ውጭ ሀገር ለምላክ፣ ከቀረጥ ነፃ ለሆነ ዓላማ (ለዲፕሎማቶች)ለሚወጣ፣ ሽያጭ ላይከናወን የሚወጡትን እንዲሁም በገበያ ውስጥ ለሽያጭ ለመዋል ከማምረቻው ቦታ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| | ወጪ የሚደረጉትን ዕቃዎች ጨምሮ ሁሉንም ከዕቃ አወጣጥ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን የማጣራ ስራን ያጠቃልላል፡፡ |
| የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | ቴሌኮም የኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልባቸው የአገልግሎት አቅርቦት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቁልፍ ስጋቶች ሁሉም ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉ አገልግሎቶች የታክስ ግደታ ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ይህም የነፃ የአየር ሰዓት አቅርቦትን ይጨምራል፡፡ |

ከላይ በሠንጠረዡ ከቀረቡት የኢንስፔክሽን ሥራዎች በተጨማሪ ይህ ማኑዋል በኢንስፔክሽን ዕቅድ እና ዝግጅት፣ በታክስ ከፋዩ የሥራ (የማምረቻ/ማከማቻ) ቦታ ውስጥ በሚካሄድ ኢንስፔክሽን፣ በግኝቶች እና በኢንስፔክሽን ወቅት በተከናወኑ ተግባራት ሪፖርት አቀራረብ ላይ የሚረዱ ቴምፕሌቶችን ያቀርባል፡፡

### 1.3. የማኑዋሉ አጠቃቀም

ይህ የኢንስፔክሽን ማኑዋል አግባብነት ስላላቸው ሕጎች እና እያንዳንዱ የስጋት አካባቢ እንዴት ባለ መልኩ በኤክሳይዝ ታክስ ገቢ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያስከትል የበለጠ ዝርዝር መረጃ የሚሰጠውን በተናጠል የተዘጋጀውን የኤክሳይዝ ታክስ የኦፊሰር ማኑዋል የሚደግፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ይህ የኢንስፔክሽን ማኑዋል የኦፊሰር ማኑዋሉን እንዳነበቡ እና ግብር ከፋዩ ሥራውን እንዴት እንደሚያከናውን እንዲሁም ምርመራ የምታደርጉበትን የስጋት አካባቢ በተመለከተ ጥሩ ግንዛቤ እንዳለዎት ታሳቢ ያደርጋል፡፡

**ማስታወሻ፡-** ስለ ግብር ከፋዩ ዝርዝር መረጃ ወይም እውቀት ከሌለዎት እንደ መጀመሪያ ኢንስፔክሽንአዲራጊ የግብር ከፋዩን ከፋዩን ፋብርካ በመጎብኘት በአባሪው የቀረቡትን ተገቢ መጠይቆች ለድርጅቱ የቅርብ ኃላፊዎች በማቅረብ መረጃዉን ይሙሉ፡፡

የዚህ ማኑዋል ወሰን ከላይ በክፍል 1.1 ሠንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ የስጋት አካባቢዎችን ያጠቃልላል፡፡

የእያንዳንዱ የስጋት አካባቢ ኢንስፔክሽን ራሱን ችሎ (ማለትም አንድ የስጋት አካባቢንብቻ በማየት)፣ አለያም በተመሳሳይ የኢንስፔክሽን ወቅት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የስጋት አካባቢዎችን በማጣራት ላይ ተመስርቶ ኢንስፔክሽን ሊካሄድ ይችላል፡፡

ለምሣሌ የጥሬ ዕቃ እንስፔክሽን ሲደረግ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን (ለቢራና ወይን)፣ ወደ ማምረቻ የገባ ና በፋብሪካዉ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎች መጠን በማጣራ እና ከኢንስፔክሽኑ በሚገኘው መረጃ መሰረት የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶችን መጠን እንዲሁም ይገኛል ተብሎ የተገመተውን የምርት ውጤት ለማረጋገጥም ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ኢንስፔክሽን በሚካሄድበትና በሚታቀድበት ጊዜ ቀደም ሲል የተካሄዱ ኢንስፔክሽኖችን ማጣራት እና ተያይዞም የተሰጡ ማናቸውንም አስተያየቶች ማስታወሻ በመያዝ መተግበራቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

አምራቾች በጊዜ ሂደት የአመራረት ቴክኒኮች እና የጥሬ ዕቃ ዓይነቶች ላይ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ። በመሆኑም ከእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን በኋላ የኢንስፔክሽን ማኑዋሉን ውጤታማነትና ይዘት መተንተን ጠቃሚ ሲሆን፣ ማንኛውንም ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለቡድን መሪዎ የማሻሻያ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል።

ይህ ማኑዋል የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ለሚሠሩ ለሁሉም ታክስ ከፋዮች ተፈፃሚ ይሆናል፤ እነዚህም የሚከተሉትን ይጨምራሉ፦

- ፈቃድ የተሰጣቸው አምራቾች፣
- ፈቃድ ያልተሰጣቸው አምራቾች፣
- የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች አስመጪዎች፣
- የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማሩ፣
- የቴሌኮም/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች አቅራቢዎች (ፈቃድ ያላቸውም ሆነ የሌላቸው)።

በኢትዮጵያ ከሚመረቱና ከውጭ ከሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በተጨማሪ ኤክሳይዝ ታክስ ቴሌኮሙኒኬሽንን ጨምሮ ኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

### 1.4. ማጠቃለያ

ይህ የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋል ፈቃድ ባላቸው የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች የሚቀርብ የኤክሳይዝ ታክስ መረጃ ለማጣራት ኃላፊነት ያላቸውን ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ ኦፊሰሮች እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በተጨማሪም ፈቃድ የሌላቸውን ታክስ ከፋዮች መለየትና ኢንስፔክት ማድረግ የማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ ገቢ ሰብሳቢ ባለሥልጣን ዋነኛ የሥራ ድርሻ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ግብር ከፋይ ሥራውን እንዴት እንደሚያከናውን፣ የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱን፣ እንዲሁም የዕቃ ቆጠራ የሚያካሂድበትን ጊዜ መረዳት አስፈላጊ ነው። ከዚህም አልፎ የሥራ ማከናወኛ ሰዓታቸውን እና የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታቸውን የሚወጡበትን አግባብ መገንዘብ እጅግ ጠቃሚ ነው።

በመጨረሻም ይህን ማኑዋል በምታነቡበት ወቅት ጊዜ ወስዳችሁ እያንዳንዱን ስጋት መረዳታችሁን አረጋግጡ።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

# ምዕራፍ ሁለት፡ የዕቅድ ዝግጅት

## 2. መግቢያ

ማንኛውም ኢንስፔክሽን ከመካሄዱ በፊት በታክስ ከፋዩ ከቀረቡት የፀደቁ ቅጾች የተገኘውን መረጃ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የጉምሩክ መረጃን በመጠቀም ግብር ከፋዩን መምረጥ፣ የሚካሄደውን የኢንስፔክሽን ዓይነት መምረጥ እንዲሁም ለኢንስፔክሽኑ ማቀድና መዘጋጀት አለብን፡፡ በተጨማሪም ቀደም ሲል በተደረጉ ጉብኝቶች ማናቸውንም የተሰጡ አስተያቶች ወይም የተነሱ ችግሮችን ለመለየት ቀደም ሲል የቀረቡ የኢንስፔክሽን ሪፖርቶችን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ዕቅዱ የተወሰኑ የስጋት አካባቢዎችን እና መስፈርቶችን በመጠቀም መመረጥ አለበት፡፡

ይህ ክፍል ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ዕቅድ የሚዘጋጅበትን መንገድ ያብራራል፡፡

## 2.1. የተጠቃለለ የኢንስፔክሽን ዕቅድ ዝግጅት

የተጠቃለለ ኢንስፔክሽን ዕቅድ ማለት በገቢዎች ሚኒቴር ደረጃ በአመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ላይ ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚቀጥለዉ አመት ኢንስፔክሽን በስጋት ደረጃቸዉ የተለዩትን ዝርዝር ድምር የያዘ ነዉ፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን የንግድ ሥራዎች እና የአቅርቦት ሰንሰለቶች ሙሉ በሙሉ መታወቃቸውን እና በዚሁ ላይ ያተኮረ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ የሚያስችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የኤክሳይዝ ፈቃድ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

ማንኛውም የሚሰበሰብ መረጃ በቀጣይ ኢንስፔክሽን የሚያካሂዱ ኦፊሰሮች የሥራውን ሙሉ መረጃ በመገምገም በአቅራቢዎች፣ በደንበኞች ወይም በሥራዎች ላይ የሚደረጉ ማናቸውንም ለውጦች በቀላሉ ማየት እንዲችሉ ተመዝግቦ በታክስ ከፋዩ ፋይል ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

አንዱ ቁልፍ ጉዳይ በእያንዳንዱ ጽ/ቤት ውስጥ የተለመዱትን ኢንዱስትሪዎች መረዳት ነው፡፡

በዚህ ማኑዋል አባሪዎች የቀረቡትን ተገቢ መጠይቆች ለመመሉላት ታክስ ከፋይን በተለይም አዲስ ታክስ ከፋይን መጎብኘት ተቀባይነት ያለው አሠራር ነው፡፡ እነዚህ መጠይቆች የታክስ ከፋዩን የንግድ ሥራ የሚመለከት ዝርዝር ማብራሪያ የሚሰጡ ሲሆን ማንኛውም ለውጥ መኖሩን ለማጣራት በየዓመቱ ሊከለሱ ይችላሉ፡፡

እያንዳንዱ ኦፊሰር በተገቢው የቁጥጥር አካባቢ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጣቸውን ግብር ከፋዮች የያዘ የኤክሴል ስፕሬድሺት/ሠንጠረዥ ማዘጋጀት እና በየኢንዱስትሪዎቹ መከፋፈል አለበት፡፡

### 2.1.1. የኢንስፔክሽን መረጣ



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

የኢንፔክሽን ሥራዎች የሚከተለውን ዝርዝር መስፈርት በመጠቀም አስቀድመው ዒላማቸውን መለየት እና መታቀድ አለባቸው፡-

| የግብር ከፋይ ስም | | |
|---|---|---|
| **መረጃ** | **ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች** | **የደረጃ መመዘኛዎች** |
| ግብር ከፋዩ ባለፉት 6 ወራት ተጎብኝቷል? | መልሱ አዎ ከሆነ የመፍትሄ እርምጃ የሚጠይቁ ማናቸውም ችግሮች ተገኝተዋል? ለምሳሌ ከመዝገብ አያያዝ አንፃር በገቢዎች ሚኒስቴር የቀረበ ማንኛውም የማሻሻያ አስተያየት ነበረ? | ባለፉት 6 ወራት ከተጎበኘና ያለፈው ኢንስፔክሽን አጥጋቢ ከነበረ፡- ስጋቱ ዝቅተኛ ተደርጎ የሚቀጥለው ዓመት እቅድ ይዘጋጃል።<br><br>ባለፉት 6 ወራት ከተጎበኘና ያለፈው ኢንስፔክሽን አጥጋቢ ካልነበረ፡- ማንኛውም አስተያየት መተግበሩን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጉብኝት ይደረጋል። |
| ታክስ ከፋዩ ባለፉት 3 ወራት ፈቃድ ነበረው? | አዲስ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ በመሆኑ መዝገቦቹ በቂ ላይሆኑ ይችላሉ። | ባለፉት 3-6 ወራት ፈቃድ ያለው ከሆነ፡- ከፍተኛ ስጋት |
| ታክስ ከፋዩ ባለፉት 2 ዓመታት ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች በጊዜው አቅርቧል? | የቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎችን እና በማስታወቂያዎች መጠን ያለውን ማንኛውንም አዝማሚያ ያጣሩ። የተገለፀው የኤክሳይዝ ታክስ ትክክል ይመስላል? | ሁሉም የታክስ ማስታወቂያዎች ከቀረቡ በትክክል መሞላታቸውን ለማረጋገጥ አልፎአልፎ ናሙና (random sample) በመውሰድ ያረጋግጡ። ማንኛውም አስጊ ወይም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ካለ ተጨማሪ ጉብኝት ያድርጉ።<br><br>ሁሉም የታክስ ማስታወቂያዎች ከቀረቡ፡- ዝቅተኛ ስጋት። |
| ግብር ከፋዩ ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ በጊዜው ከፍሏል? | | መልሱ የለም/አይ ከሆነ፣ ከፍተኛ ስጋት በመሆኑ ኢንስፔክት መደረግ አለበት። |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | | |
|---|---|---|
| ታክስ ከፋዩ የዕቃ ቆጠራ እና የዋጋ ዝርዝር ቅጾችን በጊዜው አቅርቧል? | | መልሱ የለም/አይ ከሆነ፣ ከፍተኛ ስጋት በመሆኑ ኢንስፔክት መደረግ አለበት። |
| ታክስ ከፋዩ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ እና የዋጋ ዝርዝር አቅርቦ ከነበረ፣ በትክክል የተሞሉ ናቸው? የቀረበውን መረጃ መረዳት ይችላሉ? መረጃውን ማንበብ ይችላሉ? | የቅጾቹን ትክክለኛነት ያረጋግጡ። በዋጋ ዝርዝሩ የአንዱ ዋጋ በግልፅ ተቀምጧል? የዕቃ ቆጠራ ቅጹ ማንኛውንም ኤክስፖርት ወይም ያልተለመደ መረጃ ያሳያል? | ቅጾቹ በትክክል ያልተሞሉ ከሆኑ ጉብኝትበማድረግ ያረጋግጡ ። በታክስ ከፋዩ የሥራ ቦታ በሚሆኑበት ጊዜ ቅጾች እንዴት እንደሚሞሉ ትምህርት ይስጡ። |
| ታክስ ከፋዩ ባለፉት 12 ወራ ዉሥጥ አዳዲስ ዳይሬክተሮችን ጨምሮ የመዋቅር ለውጥ አድርጓል? | ማንኛውምቁጥጥር ሥርዓት ለውጥ የተደረገበት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ያጣሩ። | መልሱ አዎ ከሆነ፣ ጉብኝት ማድረግዎን ያረጋግጡ። |

በሰንጠረዥ ዉስጥ የተመለከቱት የሲጋት መመዘኛዎች ታይተዉ የስጋት ደረጃቸዉ አነስተኛ መሆኑና ሁሉም ታክስ ከፋዮች ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች በጊዜው ካቀረቡ እና በጊዜው ከከፈሉ በኢንዱስትሪ ደረጃ መረጣ ይደረጋል።

በዚህም መሰረት አልባሳትና ጨርቃጨርቅ ከፊተኛ ሲጋት ቢሆን በቁጥጥር አካባቢዎ ለሁሉም የተፈቀደላቸው የአልባሳት እና ጨርቃ-ጨርቅ ታክስ ከፋዮች የኢንስፔክሽን ዕቅድ በማዘጋጀት የኢንዱስትሪውን አዝማሚያዎች የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ይተንትኑ። የእያንዳንዱ ንግድ ሥራ አቅራቢዎች እነማን ናቸው? የዕቃዎቹ አስመጪዎች እነማን ናቸው? ዋጋው ለኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው እንዴት ነው?

በማስከተልም ወደሚቀጥለው ሲጋት ያለዉ ኢንዱስትሪ ይሸጋገሩ (ለምሳሌ የአልኮል መጠጦች)።

በሰንጠረዡ ከተመለከቱ በተጨማሪ ለሁለት ዓመታት ኢንስፔክት ያልተደረገ ማንኛውም ቢዝነስ/ኩባንያ በኢንስፔክሽኑ ዝርዝር ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተሰጥቶት መቀመጥ አለበት።

በዚህ መልክ የተደራጀ መረጃ ለአመታዊ እቅድ መምረጫ መነሻ ሰነድ ይሆናል።

ለኤክሳይዝ ታክስ የሚመደቡ ሠራተኞች ብዛት ከኢንስፔክሽን ዕቅዱ፣ እንዲሁም ከንግድ ሥራው ስፋት እና ውስብስብነት ጋር መጣጣም አለበት።

ስጋቶች መለየታቸውንና በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

በተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች ከተደረጉ ኢንስፔክሽኖች ጋር በተያያዘ በግኝቶች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች ከሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ጽ/ቤቶች ጋር የቅርብ ትብብር ማድረግ ጠቃሚ ነው።

ለምሳሌ፣ አንድ ጽ/ቤት በአልባሳት/ጨርቃ-ጨርቅ ኩባንያዎች ወይም በማዕድን ውሃ፣ ወዘተ ኩባንያዎች ላይ ኢንስፔክሽን ካካሄደና በሆነ መንገድ በታክስ ማስታወቂያዎች ላይ ከዋጋ በታች



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ዋተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ዝቅ አድርጎ የማቅረብ አዝማሚያ ካገኘ ሌሎች ኦፊሰሮች በራሳቸው ክልል አንድ ዓይነት ችግር እየተከሰተ መሆኑን ለመለየት በተመሳሳይ የንግድ ሥራዎች ላይ ኢንስፔክሽን ማካሄድ አለባቸው።

ምንም እንኳ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኢንስፔክሽኖች የሚታቀዱበት ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅ ቢችልም፣ ይህ ተለዋዋጭነት ያለው መሆን አለበት።

ሆኖም ሁሉም እንቅስቃሴዎች መመዝገብ ያለባቸው ሲሆን አጠቃላይ ዕቅዱ በየወሩ ወይም በየሩብ ዓመቱ ሊከለስና እዳስፈላጊነቱ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል።

### 2.1.2. የንግድ ሥራዎች ውስብስብነት

**ውስብስብ የንግድ ሥራ ምንድነው?**

ውስብስብ የንግድ ሥራ የሚባሉት የሚከተሉት ገፅታዎችአሏቸው፡- ፡-

- በርካታ የማምረቻ ቦታዎች አሉት፤
- በርካታ ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎችን ያመርታል፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል፤
- በጥሬ ዕቃዎች ላይ የተከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ በታክስ ማስታወቂያው ላይ ሊከፈል በሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ ያካክሳል፤
- ምርትን/ዕቃን ወደ ውጭ ሀገር ይልካል፤
- እንደ የአውሮፕላን ማረፊያ የቀረጥ ነፃ መደብሮችን እና ዲፕሎማቶችን ለመሳሰሉት ሌሎች ከቀረጥ ነፃ ባለመብቶች ዕቃዎችን ያቀርባል፤
- ከወረቀት የማስረከቢያ ሰነዶች ጋር ግንኙነት በሌለው መልኩ መዝገቦችን በእጅ (ማኑዋል በሆነ መንገድ) ይይዛል።

ከላይ ከተገለፁት መስፈርቶች ውስጥ 3 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን የሚሠራ እና ያሉት ማንኛውም ኩባንያ ውስብስብ የንግድ ሥራ ነው።
ውስብስብ የንግድ ሥራ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ቢያንስ 3 ወይም 4 ኦፊሰሮችን፣ አንድ የቡድን መሪን እና አንድ የሥራ ሂደት ባለቤትን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል።

### 2.1.3. ግብር ከፋዮችን መምረጥ

እያንዳንዱ ቅርንጫፍ የተለያየ ቁጥር ያላቸው ኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች ይኖሩታል። በመሆኑም ከላይ በክፍል 2.1.1. የተመለከተውን የኢንስፔክሽን መስፈርት ይከተሉ።

ያንን ሂደት ተከትሎ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ታክስ ከፋዮች ለዚህ ዙር ኢንስፔክሽን ቸል ሊባሉ ይችላሉ።

ከታች በሰንጠረዡ በተዘረዘሩት መስፈረቶች መሰረት እንደ ሲጋት ደረጃቸዉ ከከፍተኛ የስጋት ወደ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ በማስቀመጥ ለከፍተኛ ደረጃዎች ቅድምያ በመስጠት ይመረጣሉ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| መስፈርት | መመዘኛዎች |
|---|---|
| የገቢ መጠን | ከፍተኛ ሽያጭ ያለው ኩባንያ = 10 ነጥብ ወደ ታች ለዝቅተኛው 1 ነጥብ |
| የታክስ ማስታወቂያው የቀረበ እና የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ | ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ የከፈለ ኩባንያ = 10 ነጥብ ወደ ታች ለዝቅተኛው 1 ነጥብ |
| ለመጨረሻ ጊዜ ኢንስፔክት የተደረገበት ጊዜ (የኢንስፔክሽኑ ዓይነት ምን ነበር?) | በ6 ወራት ውስጥ ኢንስፔክት ከተደረገ = 2 ነጥብ<br>ከ6-12 ወራት ውስጥ ኢንስፔክት ከተደረገ = 5 ነጥብ<br>ከ1 ዓመት በፊት ኢንስፔክት ከተደረገ = 7 ነጥብ<br>ኢንስፔክት ተደርጎ የማያውቅ ከሆነ = 10 ነጥብ |
| በቅርቡ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ | በ6 ወራት ውስጥ ኦዲት ከተደረገ = 2 ነጥብ<br>ከ6-12 ወራት ውስጥ ኦዲት ከተደረገ = 5 ነጥብ<br>ከ1 ዓመት በፊት ኦዲት ከተደረገ = 7 ነጥብ<br>ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ ከሆነ = 10 ነጥብ |
| ፈቃድ የተሰጠው መቼ ነበር? (ከ1 ዓመት በታች ከሆነ ቅድሚያ ይስጡ) | ፈቃድ የተሰጠው ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ከሆነ = 10 ነጥብ<br>ፈቃድ የተሰጠው ባለፉት ከ3-6 ወራት ውስጥ ከሆነ = 7 ነጥብ<br>ፈቃድ የተሰጠው ከ6-12 ወራት በፊት ከሆነ = 5 ነጥብ<br>ከ1 ዓመት በላይ ከሆነው = 2 ነጥብ |

ማስታወሻ፡- የሽጭ መረጃዎች መጠን እና የተከፈለ ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ሲወሰድ እንደየ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኤክሳይዝ ታስ ከፋዮች መጠን ከከፍተኛ አስከ ዝቅተኛ ነጥብ(10-1) የሚያሰጠዉን መመዘኛ ጣሪያዎችን በስጋት ሁኔታቸዉ በአመቱ ከተለዩት ታክስ ከፋዮች ዝርዝር በመነሳት የጣሪያ ገደብ ከ- አስከ በማስቀመጥ ነጥብ እንዲሰጥ ያደረጋል፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ★ ቁጥ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenue Records & Documentation No.1

ከላይ በተቀመጡት መስፈረቶች መሰረት ለኢንስፔክሽን የተመረጠዉ ድርጅት ከተለየ በኃላ በሚከተለው መልኩ የኢንስፔክሽኑን ዓይነቱ ደግሞ ይምረጣል፡-

- አንድ የኢንስፔክሽን ዓይነት ባለፈው 1 ዓመት ውስጥ ተደርጓል ወይ? ከተደረገ፣ የተለየ የኢንስፔክሽን ዓይነት ይምረጡ፡፡
- ምንም ኢንስፔክሽን ካልተደረገ፣የዋጋ ኢንስፔክሽን ያካሂዱ ከዋጋ በታች አሳንሶ ማስታወቅ ትልቅ ስጋት በመሆኑ ::
- ከዋጋ ኢንስፔክሽኑ በኃላ ከፋብሪካ ወጪ በተደረጉ ዕቃዎች ላይ ኢንስፔክሽን ያካሂዱ፡፡

እነዚህ የኢንስፔክሽን ዓይነቶች ከተካሄዱ በኃላ በቀጣይ የኢንስፔክሽን ሥራዎች ሌሎች የኢንስፔክሽን ዓይነቶች በየዙሩ ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ዙር ከአንድ በላይ የኢንስፔክሽን አይነቶችን መካሄድ ይቻላል፡፡

### 2.1.4. ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ብቁ የሆኑ የቡድን አባላት

ለኢንስፔክሽን ከተመረጠ ታክስ ከፋይ ጋር የግል ግንኙነት ያለው ማንኛውም ኦፊሰር በዕቅድ ዝግጅት ደረጃም ቢሆን በኢንስፔክሽን ሥራው ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

ሁሉም ኦፊሰሮች በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስር ያሉትን ታክስ ከፋዮች ዝርዝር ማግኘት እና እያንዳንዱ ኦፊሰር ግጭት ውስጥ የገባባቸውን ሁሉንም ታክስ ከፋዮች መለየት አለባቸው፡፡

ኦፊሰሩ ከታክስ ከፋዩ ጋር የጥቅም ግንኙነት እንዳለዉ ስሳዉቅ/ሲታወቅ ኦፊሰሩ ከታክስ ከፋዩ ጋር በተያያዙ ማናቸውንም መዝገቦች ማግኘት የለበትም፤ እንዲሁም ከታክስ ከፋዩ ጋር በተያያዘ በማንኛውም ኢንስፔክሽን ወይም ሌላ ሥራ መሳተፍ የለበትም፡፡

### 2.1.5. ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን የቡድን አባላትን መምረጥ

ለሥራው ብቁ የሆኑ የቡድን አባላት ከተለዩ በኃላ የሥራ ሂደት ባለቤቱ እና የቡድን መሪው ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን የሚያስፈልገውን ኃብት (ሙያተኞችና ለስራዉ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን) መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡

የሥራ ሂደት ባለቤቱ የኢንስፔክሽን ዕቅዱን ይከታተላል፡፡

የቡድን መሪው በኢንስፔክሽን ዕቅድ ዝግጅቱ እገዛ ያደርጋል፤ በዕቅድ ዝግጅት ጊዜ ውስጥ የሚጠየቁ መረጃዎችን ተደራሽ ያደርጋል፡፡ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

- ሁሉም የዕቃ ቆጠራ ቅጾች እና የዋጋ ዝርዝሮች መቅረባቸውን ማረጋገጥ፤
- ከዳታ ቄርሃውስ ማንኛውንም ተገቢ መረጃ ማቅረብ፤
- ከኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት (ECMS) ማንኛውንም የኢምፖርት/ኤክስፖርት መረጃ ማቅረብ፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ ኦፊሰሮች ሁሉንም አግባብነት ያለውን መረጃ ይሰበስባሉ፤ አሳሳቢ ወይም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለመለየት ትንተና ያካሂዳሉ፤ እንዲሁም በታክስ ከፋዩ የማምረቻ ቦታ



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ከመሄዱ በፊት በተለዩ አመላካች ነጥቦች (በተለዩ አሳሳቢ ጉዳዮችን) በተመለከተ የማጣሪያ የጥያቄዎች ቴምፕሌት ያዘጋጃሉ።

2.1.6. መደበኛ ክትትል

በተፈቀደላቸው የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች የሚቀርብ በርካታ መረጃ ያለ ሲሆን ይህም መረጃ ምንጊዜም በሲግታስ (SIGTAS) ላይ መገኘት አለበት።

የሚከተሉት ቅጾች እንዲቀርቡ በሕግ የሚጠየቁ ናቸው፡-

- ወርሃዊ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ፤
- ወርሃዊ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ፤
- የዋጋ ዝርዝር።

አብዛኞቹ ግብር ከፋዮች የታክስ ማስታወቂያን በኦንላይን ያቀርባሉ። ሆኖም ሌሎች መረጃዎች በወረቀት ፎርማት በእጅ ሊቀርቡ ይችላሉ።

መረጃው ለሪፖርት ዝግጅት እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ወይም ልዩነቶችን ለመለየት ለሚደረግ ትንተና ምንጊዜም ወደ ሲስተሙ መግባት አለበት።

## 2.2. የዕቅድ ዝግጅት ምዕራፍን ማከናወን

### 2.2.1 ስጋቶችን መለየት

የተተነተነ መረጃ (በምዕራፍ 3 ተዛማጅ በሆነው የኢንስፔክሽን ክፍል የተዘረዘረው) በታክስ ከፋዩ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚታዩ አዝማሚያዎችን ይለያል፤ እንዲሁም ኢንዱስትሪ ተኮር አዝማሚያዎችን መተንተን እና መገምገም ያስችላል።

ለምሳሌ አንድ የማዕድን ውሃ አምራች አንድን ማጣሪያ በየስድስት ወሩ እንደሚተካ ቢገልፅ፤ ሌላው ግን በየሦስት ወሩ የሚቀይር ከሆነ በየስድስት ወሩ የሚቀይረው አምራች በእርግጥ እውነቱን እየተናገረ ነው ማለት ነው።

የማምረት ደረጃቸውን እና የሚጠቀሙበትን የማጣሪያ ዓይነት ለመፈተሽ ይህንን በመነሻነት ይጠቀሙ። ከእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን ዓይነት ጋር በተያያዘ በገቢ ላይ ሊከሰት የሚችል ስጋት ይኖራል፤ እነዚህ ስጋቶች በእያንዳንዱ ክፍል ተሸፍነዋል።

የኢንስፔክሽኑ ዓይነትና ኢንስፔክት የሚደረገው ድርጅት ከተመረጠ በኋላ የዕቅድ ዝግጅት ምዕራፍ ይጀመራል።

ምርመራው የሚካሄድበት ድርጅት እና የኢንስፔክሽኑ ዓይነት ስምምነት ከተደረገበት ዓመታዊ ዕቅድ ወይም በልዩ ሁኔታ ከመረጃ ትንተና በተገኘዉ ማሳያዎች በመነሳት ወይም ለምሳሌ አንድ



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ የተ መ ግ ብ ና ና የ ክ መ ን ጉ ዶ ች ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ግብር ከፋይ ተገቢ የሆኑ ቅጾችን ሳያቀርብ ወይም ተዓማኒነት ያለው መረጃ ሳይሰጥ ሲቀር ሊመረጥ ይችላል፡፡

ይህ ማኑዋል የሚያጠቃልላቸው የኢንስፔክሽን ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

| | |
|---|---|
| የየኤክሳይዝ ፈቃድ አሰጣጥ ኢንስፔክሽን | ይህ ለአዲስ ፈቃድ አመልካቾች መከናወን የላባቸዉ ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | ይህ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን በማረጋገጥ ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና ትርጉማቸዉ | ይህ ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ ጥቅም ላይ መዋሉን ወይም አለመዋሉን በመለየት ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን፡- ከውጭ የሚገቡ እና የሀገር ውስጥ | ይህ በጥሬ ዕቃ አጠቃቀምና ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ በሚያመርቱ ምርት የጥሬ ዕቃዎቹ ብዛትና መገኛቸውን ማረጋገጥ በሚችልበት መንገድ ላይ ያተኩራል፡፡ |
| የመጨረሻ ምርት / የምርት ውጤት ኢንስፔክሽን | ይህ ለተለያዩ የኤክሳይዝ ታክስ ከተጣለባቸው ምርቶች የሚጠበቁ የተለያዩ የምርት ውጤቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ከተቀመጠው መጠን ውጭ የሆነን ማንኛውንም የምርት ብዛት ለማጣራት ይህንን እንደ መነሻ መጠቀም ይቻላል፡፡<br>ይህ ኢንስፔክሽን ማንኛውም የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያ ላይ እንዲሁም የርቀት መከታተያ መሣሪያ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚደረግ ክትትልና ማጣራትን ይጨምራል፡፡ |
| የባከኑ ወይም የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | ይህ ከማምረቻ እና ማከማቻ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ይህም በዕቃ ቆጠራ ቅጹ እና በማስታወቂያ ቅጹ ላይ የተመዘገቡት ብክነቶች እና የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎችን የተመለከቱት መረጃዎች ከመሣሪያዎች እና ከማምረት ሂደት ጋር የተጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ |
| ማምረቻ እና ማሽጊያ | የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረቻ እና ማሽጊያ መሳሪያዎች ልከትና የምርቶቹን ትክክለኝነት(መጣጣም) ማጣራት፡፡ |
| የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያ/ የርቀት መከታተያ | ይህ የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያዎች በትክክል እንዲሠሩ መፈተሻቸውን እንዲሁም ትክክል መሆናቸውን እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡ |
| ከማሽጊያ እስከ ማከማቻ | የተመረተውን እና የታሸገውን የምርት ብዛት በማከማቻ ካለው ጋር በማስታረቅ ያረጋግጣል፡፡ |
| ከፋብሪካ ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | ይህ ወደ ውጭ ሀገር ለምላክ፣ ከቀረጥ ነፃ ለሆነ ዓላማ (ለዲፕሎማቶች)ለሚወጣ፣ ሽያጭ ላይከናወን የሚወጡትን እንዲሁም በገበያ ውስጥ ለሽያጭ ለመዋል ከማምረቻው ቦታ |



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| | ወጪ የሚደረጉትን ዕቃዎች ጨምሮ ሁሉንም ከዕቃ አወጣጥ ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን የማጣራ ስራን ያጠቃልላል፡፡ |
| የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | ቴሌኮም የኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልባቸው የአገልግሎት አቅርቦት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቁልፍ ስጋቶች ሁሉም ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉ አገልግሎቶች የታክስ ግደታ ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ይህም የነፃ የአየር ሰዓት አቅርቦትን ይጨምራል፡፡ |

የዚህ ማኑዋል ክፍል 3 በእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ላይ የሚያተኩር ሲሆን ከእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ባህርይ የሚመነጩ ስጋቶችን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ እንዲሁም በኩባንያው ውስጥ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች እና ማንኛውንም የሕግ ተገገርነት ጉዳይ ለመለየት የዳታ እና የመረጃ ትንተና እንዴት እንደሚከናወን ይገልፃል፡፡

### 2.2.2. ድርጅቱን እና የሥራ እንቅስቃሴዎችን መረዳት

ከላይ የተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ታክስ ስጋቶች በባህሪያቸው አጠቃላይነት ያላቸው ሲሆን በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ በመሆኑም የኤክሳይዝ ኦፊሰሮች ከሚመለተዉ ታክስ ከፋይ ጋራ ቀጥተኛ ግኑኝነት ባላቸዉ ስጋቶች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማኑዋል ከእያንዳንዱ ግለሰብ ግብር ከፋይ ጋር በተያያዙ ስጋቶች ላይ ለማተኮር እንዲቻል የሥራ እንቅስቃሴን እንዴት መተንተን እንደሚቻል፣ የሚያስፈልጉ ዝርዝር ጥሬ ዕቃዎችን ፣ የመዝገብ አያያዝን፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን እና የምርት ሂደትን ያብራራል፡፡ ኢንስፔክሽን የሚካሄድበት መንገድ እንደ አቅራቢዎቹና ደንበኞቹ ሁኔታ እንዲሁም እንደሚጠቀሙት የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት ከግብር ከፋይ ግብር ከፋይ እንደሚለያይ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ኢንስፔክሽን የሚደረግበት ግብር ከፋይ ለመረዳት የሚያስችሉ ከእያንዳንዱ ግብር ከፋይ ጋር በተገናኘ መሞላት ያለባቸው መጠይቆች ከዚህ በታች በአባሪው ላይ ቀርበዋል፡፡

እነዚህ መጠይቆች እና መረጃዎች ሁሉን አቀፍ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ተጨማሪ ጥሬ ዕቃዎች መኖራቸው ከታወቁ እነዚህን መረጃዎች ወደ ሠንጠረዥ ማስገባት አሰፈላጊ ነዉ ::::

መጠይቆቹ በድርጅቱ ዉስጥ ስለ ድርጅቱ የንግድ ሁኔታ የተሻለ ዕዉቀትና ኃላፊነት ያለዉ ሰዉ ወይም ድርጅቱ የሚወክለዉ ሰዉ ቃለመጠይቆቹ መሞላት ያለባቸው ሲሆን፣ከመጠይቁ የሚገኘዉ ምላሽ በኢንስፔክሽን ጊዜ ከግብር ከፋዩ በሚቀርቡ ማንኛውም መረጃና ኢኒሰፔክተሩ ከምልከታዉ ከሚያገኘዉ መረጃ ጋር ተመሳክሮ ማረጋገጥ ያስፈልጋል ::

ይህ ከተጠናቀቀ በኋላ የተሞላው መጠይቅ በታክስ ከፋዩ የፋይል ማህደር ውስጥ በግልፅ በሚታወቅ ቦታ መቀመጥ አለበት፡፡

በተመሳሳይ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ግብር ከፋዮች ኢንስፔክት ሲደረጉ እና መረጃው ሲሰበሰብ በሁሉም ተመሳሳይ ግብር ከፋዮች መካከል ያሉትን የአቅርቦት ሠንሰለቶችና ደንበኞች በመገምገም የአቅራቢዎችን እና የደንበኞችን መረጃ እንዲሁም የተመሳሳይ ጥሬ ዕቃዎችን እና ምርቶችን ዋጋ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ተመሳሳይ ግብር ከፋዮች ለጥሬ ዕቃዎች የተለያዩ ዋጋዎችን



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁጥጥር መዝገብና የሰነድ ማህደር ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የሚከፍሉ ወይም ለተጠናቀቁ ምርቶች የተለያዩ ዋጋዎች የሚያስከፍሉ ከሆነ ይህ በገበያው ሁኔታ ላይ ያለንን ግንዛቤ ያሳድጋል፡፡

ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን የመረጃ/ውሂብ ትንተና እንዴት እንደሚካሄድ የበለጠ ዝርዝር መረጃ በዚህ ማኑዋል ክፍል አራት ውስጥ ቀርቧል፡፡ ይህ ክፍል በእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለውን አጠቃላይ ጽንሰ ሃሳብ ያጠቃልላል፡፡

### 2.2.3. ዝርዝር የዕቅድ ዝግጅት

ይህ ክፍል እያንዳንዱን የኢንስፔክሽን ዓይነት በመውሰድ በእያንዳንዱ የስጋት አካባቢ ለተለመዱ ስጋቶች ፕሮግራም/ቼክሊስት ማዘጋጀት፡፡

| **የኢንስፔክሽን ዓይነት** | **በእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ያሉ ስጋቶች** | **ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን መለየት** |
|---|---|---|
| የፈቃድ አሰጣጥ ኢንስፔክሽን | ለአዲስ ፈቃድ ማመልከቻዎች፡-<br>- የፍቃድ ማመልከቻ ያቀረበው ድርጅቱ ህጋዊ ውክልና መኖሩን ማጣራት<br>- ድርጅቱ ለንግድ ስራው ብቁ ስለመሆኑ በህጉ መሰረት የንግድ ፍቃድ/ምዝገባ፣ የድርጅቱ መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መቅረባቸውን ማረጋገጥ<br>- የፋብሪካ የማምረቻ ህንፃ ፕላን በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ መቅረቡን ማጣራት<br>- በተጨማሪም በፈቃድ ምዝገባ ማመልከቻ ላይ የተገለፁትን በመመልከት በቸክ ሊስቱ መሰረት ማጣራት | - አመልካቹ ከአሁን ቀደም በማንኛውም በታክስ ማጭበርበር እና በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት መሆኑን ማጣራት፡፡<br>- አመልካቹ ከሌሎች ኩባያንዎች የሚፈለግባቸው ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ፡፡<br>- የንግድ ሥራው ለጥሬ ዕቃዎች ግልፅ የአቅርቦት ሰንሰለት ማረጋጥ፡፡<br>- ህንፃው ከግቢው ጀምሮ የማምረቻ ቦታ፣ የጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣ ያለቀለት ምርት ማከማቻ መጋዘን፣ የቢሮ እና ሌሎች የተመለሱ ዕቃዎች የሚቀመጡበት መጋዘን የተለዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ<br>- በማመልከቻው የቀረበው የንግድ ስር አሁን ከሚጠይቀው የኤክሳይስ ታክስ ፍቃድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ እና የቀረቡት |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | | |
|---|---|---|
| | | ሰነዶች ህጋዊነታቸውን ማጣራት<br>- የቢዝነስ ዕቅዱ ከብዛት/መጠን ጋር የተያያዘ ትንበያ ማስቀመጡን ማጣራት፡፡<br>- ኩባንያው የተዘረጋው የኤክሳይዝ ታክስ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን ማጣራት፡፡<br>- በቦታው ላይ የግቢው አካላዊ ደህንነት የተጠበቀ እና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ ፡፡<br>- የንግድ ሥራው ከፍተኛ የብድር ዕዳና ምክንያታዊ ያልሆነ የአከፋፈል ሁኔታ ማጣራት፡፡ |
| የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ | - የዕቃዎች/ምርት ወጪ ስሌት ሁሉንም የማምረቻ ወጪዎች ላያካትት ይችላል፡፡<br>- የትርፍ ህዳጉ በጣም ዝቅተኛ (ከ10% በታች) ከሆነ፡፡<br>- በደረሰኝ ላይ ያለው ዋጋ ከችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ከሆነ፡፡ |
| የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና ምንነታቸው | - የአልኮል መጠጦች በአልኮል አልባ መጠጦች ምድብ የተመደቡ ከሆኑ፡፡<br>- ከ7% በላይ የሆነ የአልኮል መጠን ያላቸው የአልኮል መጠጦች ከ7% በታች የሆነ የአልኮል መጠን ባላቸው ምድብ ውስጥ ከተመደቡ፡፡<br>- ጣዕም እንዲኖረው የተደረገ የማዕድን ውሃ በተፈጥሮ ማዕድን ውሃ ምድብ ከተመደቡ፡፡ | - መግለጫው ላይ የተለጠፈው መጠን/ብዛት ወይም የአልኮል ጥንካሬው ትክክለኛ አለመሆን ፡፡<br>- ጣዕም እንዲኖረው የተደረገ የማዕድን ውሃ ምርት እንደ መደበኛ ማዕድን ውሃ ተቆጥሮ መገኘት ፡፡ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቢ.ተ. መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | | |
|---|---|---|
| የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን፡- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ እና ወደ ውጭ የሚላክ | በኢትዮጵያ ውስጥ የበቀሉ/የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች ለምርት ሲውሉ የቢራና የወይን ምርቶች ከኤክሳይዝ ታክስ ቅናሽ ተጠቃሚ ከሆኑ፡፡ | - ከውጭ እንደገቡ የሚጠቁሙ ማሸጊያዎች ያላቸው ጥሬ ዕቃዎች በጥሬ ዕቃ ማከማቻ ውስጥ ከተገኘ፡፡<br>- የጥሬ ዕቃዎች አቅራቢው በሀገር ውስጥ የተመረቱ ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ አለመቻል፡፡<br>- አምራቹ ተዛማጅ ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ ካስመጣ ፡፡ |
| የመጨረሻ ምርት / የምርት መጠን ኢንስፔክሽን | ምርትን በማሳነስ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ | - እያንዳንዱ አምራች ጥቅም ላይ ከዋሉ ጥሬ ዕቃዎች አንፃር መጠነኛ ልዩነት ያለው የለቀለት ምርት ብዛት የተገኘ ሲሆን፡፡<br>- ሆኖም ለእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት/ብራንድ ከ12 ወራት በላይ ለሆነ ጊዜ ያሳወቁት የሚርት መጠን በየወራቱ የግብአት ምርት ጥምርታ ከሚያሳየዉ የምርት መጠን የ የወራቱ አማካኝ ምርት ከመዝገቦች ከሚታይ ማንኛውም ልዩነት ስነጸጸር ልዩነት ሲገኝ፡፡ |
| የባከኑ ወይም የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | የብክነት/ብልሽት መጠንን ጨምሮ ማስታወቅ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያን አሳንሶ ማስታወቅን ያስከትላል፤ እንዲሁም ዕቃዎች ኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደገበያ የሚወጡበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡ | - ብክነት እና ጉድለት በዕቃ ቆጠራ ቅጽ መመዝገብ አለበት፡፡<br>- የብክነት/ጉድለት አሃዞችን ማጣራትና ምን እንደሆኑ ማረጋገጥ፤<br>- እንዲሁም ለብልሽቶች ትክክለኛውን ሂደት መከተላቸውን እና ከአወጋገድ በፊት ለገቢዎች ሚኒስቴር ማሳወቃቸውን ያረጋግጡ፡፡ ካላሳወቁ እንዳልተወገዱ ተቆጥሮ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | | |
|---|---|---|
| ማምረቻ እና ማሽጊያ | የምርት መጠን እንዲያንስ ተደርጎ የተገለፀባቸው መዝገቦች የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ማስታወቅን ያስከትላሉ። | - ይህ ኢንስፔክሽን የመጨረሻ ምርት ከሚመረትበት ጀምሮ እስከ አስከሚታሸግበት ድረስ የሚሄድ ነዉ።<br>- የምርት ባች ቁጥሮች ከማሸጊያ ቁጥሮች ጋር መተሳሰር(መገናኘት) አለባቸው (ይህ የተመሳከረዉ የምርት ቁጥር ከጥሬ ዕቃው አጠቃቀም ጋር መተሳሰር(መመሰከር) አለበት)<br>- የዕቃ ቆጠራ ማጣራት በሚደረግበት ጊዜ የወሩ የመዝጊያ ቆጠራ/መጠን ከሚቀጥለው ወር መክፈቻ መጠን ጋር እኩል መሆኑ መመሳከር አለበት ፤ ከዚያም የዚያ ወር የመዝጊያ ቆጠራሂሳብ በወሩ መጀመሪያ የነበረዉ የምርት መጣን ላይ በወሩ የተመረቱ ምርቶች ተጨምሮ ፣ የጠፉ/የባከኑ ወይም በሽያጭእና በሌሎች ምክያቶች ከፋብርካዉ የወጡ ዕቃዎችን በመቀነስ የሚገኘዉ መጠን ጋር እኩል መሆን አለበት። ነገር ግን የተገኙ ማናቸውም ልዩነቶች ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው። |
| የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያ / የርቀት መከታተያ | የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያዎች በትክክል እንደሚሠሩ ለማረጋገጥ በመሳሪያዎቹ ላይ ምርመራ የሚደረግባቸዉ መሆኑን ማረጋገጥ ነዉ ።ምርመራ የማይደረግባቸዉ ከሆነ ብዛትን አሳንሶ ማስታወቅን የሚያጋል እና በዚህም የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ማስታወቅን ያስከትላል። | - ከጅምሩ መሳሪያዎቹ ሲገዙ ደረጃቸዉን የጠበቁ መሆናቸዉና በየአመቱ<br>- የምርመራ/ፍተሻ መደረጋቸዉን ማረጋገጥ አለበት ።<br>- የተደረጉ የቆጣሪ ንባቦችን የሚያሳይ መዝገብ መኖሩን ማረጋገጥ ። |
| ከማሸጊያ እስከ ማከማቻ እና የክምችት ቁጥጥር | የታሸጉ ዕቃዎች በተወሰነ የማከማቻ ሥፍራ ስለመግባታቸው በትክክል | - የዕቃ ክምችቱ በተወሰኑ ሥፍራዎችአለመቀመጣቸዉ፤ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ማዕከል ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | | |
|---|---|---|
| | ካልተመዘገበ፤ ክምችትን አሳንሶ ማስታወቅን እና የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ማስታወቅን ያስከትላል። | - የምርት ክምችቱ በትክክል የማይቆጠር ከሆነ ፤<br>- የተያዘው የዕቃ ክምችት ከማሽጊያ ቁጥሮች ጋር የማይጣጣም ከሆነ ፤<br>- በእጅ ያለው የዕቃ ቆጠራን ከስቶክ ሪኮርዶች የማይታረቅ ከሆነ በምርመራ ማረጋገጥ። |
| ከፋብሪካ ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | - ከፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ኤክሳይዝ ታክስ ሚከፈልባቸዉ ዕቃዎችን ብዛት አሳንሶ ማስታወቅ የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ማስታወቅን ያስከትላል።<br>- ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ የቀረቡ ዕቃዎችን ኤስክፖርት እንደተደረጉ ወይም ወደ ቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ ወጪ እንደተደረጉ አድርጎ መመዝገብ | - ለኤክስፖርት እና ከቀረጥ ነፃ ለሆነ አጠቃቀም ወጪ ለተደረጉ ዕቃዎች የኤክስፖርት ማስረጃ ወይም ወደ ተገቢው ደንበኛ ስለመድረሳቸው ማረጋገጫ መኖሩን ማጣራት ።<br>- ለሌሎች ማናቸውም ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች የዕቃዎቹ ብዛት ከማዘዣዎች፣ ከማስረከቢያ ሰነድ እና ደረሰኝ ጋር መዛመዱን ማረጋገጥ አለበት። |
| የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | ቴሌኮም የኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልባቸው የአገልግሎትአቅርቦት ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ረገድ ቁልፍ ስጋቶቹ ሁሉም አገልግሎቶች ለታክሱ የሂሳብ መዝገብ ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ይህም የነፃ የአየር ሰዓት አቅርቦትንም ይጨምራል። | - ነፃ የአየር ሰዓት በኤክሳይዝ ማስታወቂያው ላይ መካተቱን ማጣራት።፤<br>- በአዋጁ የተገለጹት አገልግሎቶች ኤክሳይዝ ታክስ ስለመከፈላቸዉ ማጣራት |

2.2.4. የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ

ምርመራ የሚደረግበት ግብር ከፋይ እና የኢንስፔክሽኑ ዓይነት በሚመረጥበት ጊዜ የቡድን መሪው ኢንስፔክሽኑን ከሚያካሂዱት ሁሉም የሚመለከታቸው ኦፊሰሮች ጋር የሚደረግ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዉስጥ ስብሰባ ማዘጋጀት ይኖርበታል። ።

ይህ በኢንስፔክሽን ዕቅዱ ላይ በስፋት ለሚደረግ ውይይት እና በእያንዳንዱ ኦፊሰር የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ከስምምነት ላይ ለመድረስ እድል ይሰጣል።



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ዉስጥ መዛግብትና ደህመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ቢያንስ ሁለት ኦፊሰሮች መመደብ ያለባቸው ሲሆን እንደ ንግድ ሥራው ውስብስብነት ተጨማሪ ኦፊሰሮች ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡፡ በዚህም መሠረት የንግድ ሥራው የበለጠ ውስብስብ ከሆነ ቢያንስ ሦስት ኦፊሰሮች መመደብ አለባቸው፡፡

ለእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን ዓይነት በሚመለከት ግኑኝነት ባለዉ የተወሰነ የስራ ክፍል ውስጥ የሚገኝ የበለጠ በጥልቀት መታየት ካለበቸዉ የስጋት አካባቢዎችና ሰነዶች አንጻርም ተጨማሪ ኦፊሰሮችን ልያስፈልግ ይችላል ፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ከአንድ እስከ ሦስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ በተከናወኑ ተግባራት ላይ ማተኮር አለበት፤ ነገር ግን በታክስ ማስታወቂያ ወይም በ ኢንቮንተሪ ማቅረቢያ ቅጽ ወይም በዋጋ ዝርዝር ላይ ከሚታየዉ ዉጤት የተነሳ እንዲቀርብ የሚያደርጉትን ሁሉንም ግብይቶች እና የሥራ እንቅስቃሴዎችን በዝርዝር መገምገም አለበት፡፡

ይህም ማለት የተገለፀው የኤክሳይዝ ታክስ፣ የምርት መጠን እና የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ትክክለኛ መሆኑን እያረጋገጥን ነው ማለት ነው፡፡

### 2.2.5. የሚታዩ መረጃዎች

የኢንስፔክሽን ቡድኑ ቢሮ ዉሥጥ የመጀመሪያዉን ስብሰባ ከካሄዱ በኃላ ያሚከተለውን አጠቃላይ መረጃ (ለሁሉም የኢንስፔክሽን ዓይነቶች የሚያስፈልገውን) ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ይህም ኢንስፔክተሮቹ በሚከናወኑት ተግባራት ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በዚህም መሠረት ሁሉም ኢንስፔክሽኖች የሚከተለውን አጠቃላይ መረጃ በመገምገም መጀመር አለባቸው፡-

1. በዚህ ማኑዋል ምዕራፍ 3 ተዛማጅ በሆነው ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉንም የግብር ከፋይ መረጃዎች ይገምግሙ፡፡ መረጃው በፋይል ላይ ከሌለ እና በግልፅ ካልተገኘ በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ በመጠይቆቹ ላይ ያለውን መረጃ ከግብር ከፋዩ ለመጠየቅ ማስታወሻ ይያዙ፡፡
2. በኢንስፔክሽኑ ጊዜ ግብር ከፋዩ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ሁሉም ምርቶች በተመለከተ መረጃዉን ያጣሩ፡፡
3. በ የኢንስፔክሽን ጊዜ ፣ ከኢንስፔክሽኑጊዜ በፊትና በኋላ ባለው ጊዜ አንድ የታክስ ጊዜ በሲግታስ (SIGTAS) እና በዳታ ዌርሃውስ ላይ ያለውን መረጃ/ውሂብ ያጣሩ፡፡
4. ቀደም ሲል የተካሄደዉን ማንኛውንም ኢንስፔክሽን ወይም ኦዲት ስራዎችን በመገምገም የታዩ ግኝቶችና የተሰጡ አስተያየቶች ን ማስታወሻ በመያዝ በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ በሚገኙበት ጊዜ በግኝቶቹ ላይ በመወያየት በተሰጡት አሰተያየት መሰረት እርምጃ መወሰዳቸዉን ማጣራት ለውጦች ካልተደረጉ ማስታወሻ ይያዙ፡፡
5. የግብር ከፋዩን ፈቃድ ያጣሩ፡፡ ግብር ከፋዩ እንዲያመርት የተፈቀዱለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ዓይነትን፣ የሚመረቱ ብራንዶችን፣ የማምረቻ/ማከማቻ ቦታውን ጨምሮ በፈቃዱ ላይ ያሉ ዝርዝር መረጃዎችን በማስታወሻ ይያዙ፤ እንዲሁም የቦታውን ፕላን ይመርምሩ፡፡
6. ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገው የዕቃ ቆጠራ መቼ እንደተከናወነ ያጣሩ፡፡ በዕቃ ቆጠራው ላይ የገቢዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቦታው ተገኝቶ መከታተሉን በማጣራት ማስታወሻ ይያዙ፣



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቦታ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

7. ለኢንስፔክሽን ሥራው በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ በሚገኙበት ጊዜ የመጨረሻው የዕቃ ቆጠራ መቼ እንደተከናወነ እና ቀጣዩ የዕቃ ቆጠራ መቼ ሊከናወን እንደታቀደ ግብር ከፋዩን ይጠይቁ፡፡
8. ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገውን የዕቃ ቆጠራ ሪፖርት ይቀበሉ፡፡

***ማሰገንዘቢያ፡-*** *በአባሪው የቀረበው ቴምፕሌት መሞላት ያለበትን መረጃ ምሳሌዎች ያስቀምጣል፡፡ ትክክለኛውን ቴምፕሌት ከምዕራፍ 6 ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህንኑ ቴምፕሌት በመጠቀም የሁሉንም ተገቢ መረጃ ማስታወሻ ይያዙ፡፡ በዚህ ክፍል ከተገለፀው አጠቃላይ መረጃ በተጨማሪ በዚህ ማኑዋል ተዛማጅ ክፍል ውስጥ የተዘረዘረውን እያንዳንዱን የኢንስፔክሽን ዓይነት የሚመለከት ዝርዝር መረጃም መካተት አለበት፡፡*

### 2.2.6. ሁለተኛ የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ

የኤክሳይዝ ሙያተኞች በቢሮ ውስጥ ባሉ ጊዜ በሁለተኛዉ የቅድመ-ኢንስፔክሽን ሰብሰባ ጊዜ ሁሉም አጠቃላይ መረጃ ከተሰበሰበእና ከተተነተነ በኃላ ስለግብር ከፋዩ የሥራ እንቅስቃሴዎች የተሟላ ግንዛቤ ይኖርዎታል፡፡ ለምሳሌ፡-

- *ግብር ከፋዩ ሁሉንም ተገቢ የፀደቁ ቅጾች በጊዜው ማቀረቡን፣*
- *ግብር ከፋዩ ሁሉንም ያልተከፈለ ቀሪ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈሉን፣?*
- *ግብር ከፋዩ ቀደም ሲል ኦዲት ተደርጎ ወይም ተጎብኝቶ ከሆነ የተሰጡ አስተያየቶችና የተደረጉ መሰተካከያዎችን መጣራቱ፣*
- *የማምረት መጠን መጨመርና ወይም መቀነሱንና?*
- *ከኤክሳይዝ ታክስ ክፍያዎች ከምርት አንፃር ሲታይ ግልፅ አዝማሚያ መኖሩን*

በጋራ በወያዩት እና ከእነዚህ ጉዳዮች አንፃር የግብር ከፋዩን የሕግ ተገዢነት ይመዝኑ፡፡

### 2.2.7. የቁጥጥር ፕሮግራም

ያገኙትን ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ከተገመገመ “የኢንስፔክሽን ዕቅድ” በማርቀቅ በተጎቢው የቅርብ የሥራ ኃላፊ እንዲፀድቅ እና እንዲፈረምበት ለማቅረብ የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ይሆናሉ፡፡

በቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባዎች የተስማማችሁባቸውን የታቀዱ ተግባራት በመከተል የኢንስፔክሽን ዕቅድ ቁጥጥርን ረቂቅ ያዘጋጁ (ከእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን ዓይነት ጋር የተያያዘ ተጨማሪ መረጃ ተዛማጅ በሆነው የዚህ ማኑዋል ክፍል ይገኛል)፡፡

ኢንስፔክሽኑ በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የኢንስፔክሽን ዕቅዱ በቂ መጠባበቂያ ያለው መሆኑን ያረጋግጡ፤ ለምሳሌ ኢንስፔክሽኑን በአንድ ቀን ብቻ ሳይገድቡ ቢያንስ አንድ ቀን ቢበዛ እስከ ሦስት ቀን እንደሚወስድ ይጥቀሱ፡፡

የተወሰኑ ምሳሌዎች ቀጥሎ ቀርበዋል፡-

**ጥሬ ዕቃዎች፡-** አንዳንድ ጥሬ ዕቃዎችን ያልተመዘገቡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ጥፋት በመሆኑ በቅድመ-ኢንስፔክሽን ሪፖርቱ የሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች ማስታወሻ መያዝ እና በግብር ከፋዩ ከተያዘው የጥሬ ዕቃ መዝገብ ጋር ማነፃፀር ያስፈልጋል ፡፡ በታክስ ማስታወቂያ መገለፅ



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ሲኖርባቸው ያልተገለፀ ማናቸውንም ጥሬ ዕቃዎች ያጣሩ፤ ለምሣሌ፣ ከኢትዮጵያውያን አቅራቢዎች የተገኙ ጥሬ ዕቃዎች፡፡

**ስቶክ፡-** የኢንቨነተሪ ሪፖርት ቅጹ እና በማስታወቂያ ቅጹ የቀረበውን መረጃ በመጠቀም ከሲግታስ ላይ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡ ግብር ከፋዩ ከተጎበኘበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለውን የቀን ልዩነት ይውሰዱ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞም የመጨረሻው የኢንስፔክሽን ሪፖርት ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ሊተነተንም ይችላል፡፡ የመጨረሻው የኢንስፔክሽን ጉብኝት የክምችት መረጃን ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡ የተሸጠው የመጨረሻ ምርት መጠን ከታገሸዉ የምርት ማጠራቀምያ ላይ ማንኛውም ብክነት በመቀነስ የሚገኝ መጠን ይሆናል፡፡ ማንኛውም ብክነት ከተገኘ እና ብክነቱ በዕቃ ቆጠራ ሪፖርት ላይ ካልቀረበ የኤክሳይዝ ታክሱ መወሰን አለበት፡፡

**ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎች፡-** ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎች ብዛት እና መጠን በዕቃ ቆጠራ ቅጹ ላይ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

ይህም ለሚከተሉት ወጭ ምርቶች የሚይዝ ይሆናል ፡-

ሀ. የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው በሽያጭ ለሚወጡ ዕቃዎች፤

ለ. የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸዉና ምርቶቹ ከመውጣታቸው በፊት የተደረገ የሽያጭ ስምምነት ሳይኖር ለሚወጡ ዕቃዎች፤

ሐ. ለውጭ ሀገር ገበያ ለመቅረብ ለሚወጡ

መ. ከታክስ ነፃ ለሆኑ አቅርቦቶች፤ ወይም

ሠ. ለኪሳራ ወይም ለጠፉ/ለተበላሹ ዕቃዎች

ስለዚህ ለሚመርጡት የኢንስፔክሽን ስራ የቀን ብዛት ከእያንዳንዱ ጋር የተያያዘውን የአወጣጥ ዓይነት የሚያሳይ ሪፖርት ያዘጋጁ፡፡

**ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ፡-** የቀኖችንና የምርቶችን መጠን ማስታወሻ መያዝዎን ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ግብር ከፋዩ በኤክስፖርቱ ቦታ በትክክል የተረጋገጠና ማህተም የተደረገበት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ በማድረግ ዕቃዎቹ ወደ ውጭ ሀገር መላካቸውን እንዲያረጋግጥ ያድርጉ፡፡

**የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ፡-** የሲግታስ ሥርዓቱ በግብር ከፋዮች አማካኝነት በታክስ ማስታወቂያዎች ላይ የሚቀርብ መረጃ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህም በተለያዩ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያዎች ላይ ሪፖርት ያዘጋጁ እና ከዚያም በኢንስፔክሽኑ ወቅት ለመተንተን የሚያስፈልጉትን መረጃዎች በመዘረዘር የኢንስፔክሽን ዕቅድ ያዘጋጁ፡፡

**የዕቃ ቆጠራ፡-** ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች የዕቃ ቆጠራን ያካሂዳሉ፡፡ የኢንስፔክሽን ሥራዎችም የዕቃ ቆጠራን ያካትታሉ፡፡ የመጨረሻውን ኢንስፔክሽን የዕቃ ቆጠራ በመነሻ መረጃነት ይጠቀሙ፡፡ እንዲሁም በመጋዘን የሚገኙትን የሁሉንም ዕቃዎች የሚጠበቅ መጠን ለመተንተን ይህንኑ መረጃ ይጠቀሙ፡፡ በተጨማሪም የቆጠራ ሰነድዎን ከግብር ከፋዩ ሰነድ ጋር የሚያነፃፅሩበት አንዳች ማስረጃ እንዲኖርዎት ያገኙትን ማንኛውም ነገር በቅድመ-ኢንስፔክሽን የማረጋገጫ ዝርዝር ላይ ማስታወሻ ይያዙ፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ለሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ ግብር ከፋዩን ለመጠየቅ የሚያገለግሉ የጥያቄዎች ዝርዝር ያዘጋጁ።

ከታች በክፍል ሦስት የቀረበው በእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን ዓይነት ላይ መረጃን ይሰጣል። እያዳንዱ ክፍል ለኢንስፔክሽኑ ዕቅድ እና ትግበራ የሚረዱ ቼክሊስቶች እና ቴምፕሌቶችን ያካትታል።

### 2.3. ጉብኝትን ለኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ማሳወቅ

ማጣራቶቹን ካከናወኑ እና የተገኘው መረጃ ላይ ትንተና ካካሄዱ በኋላ የቡድን መሪው ጉብኝቱን በተመለከተ ለታክስ ከፋዩ ማሳወቅ አለበት።

ምርመራውን ለማካሄድ ኦፊሰሮቹ በቂ ቦታ ሊሰጣቸው ስለሚገባ እና ማናቸውንም ተዛማጅ መዝገቦች ማግኘትም ስላለባቸው ኢንስፔክሽኑ የሚካሄድባቸውን ቀናት ዝርዝር ያቅርቡ። ማናቸውም ኦፊሰሮች በመዝገብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ልምድ ከሌላቸው ግብር ከፋዩ በሲስተሙ ውስጥ ዕቃዎችን ለመከታተል የሚያገለግሉ የኦዲት መከታተያ እና የኮድ ቁጥሮችን ጨምሮ ለኦፊሰሮቹ በሲስተሙ ዙሪያ ግንዛቤን መስጠት አለበት።

የሚካሄደውን የኢንስፔክሽን ዓይነት በማብራራት

በተቻለ መጠን ስለ ኢንስፔክሽኑ ለማሳወቅ ቢያንስ ከ10 ቀናት በፊት ለግብር ከፋዩ ደብዳቤ መጻፍ ይኖርብዎታል።

እያንዳንዱን የኢንስፔክሽን ዓይነት በሚሸፍነው ተዛማጅ ክፍል ውስጥ ኢንስፔክሽን ማካሄድን የተመለከተ መረጃ ይገኛል።

ታክስ ከፋዩ ቀደም ሲል የሕግ ተገዢነት ችግር ካሳየ ወይም በተደጋጋሚ የታክስ ማስታወቂያ ካላቀረበ ወይም ተገቢውን የኤክሳይዝ ታክስ ካልከፈለ (ወይም ምንም ገቢ እንዳላገኘ አድርጎ ካቀረበ) ድንገተኛ ጉብኝት ታሳቢ መደረግ ይችላል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

# ምዕራፍ ሦስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋል፡- አፈፃፀም

## 3.1. የኢንስፔክሽን አፈፃፀም መግቢያ፡- አጠቃላይ

ይህ ሰነድ የእቅድ ዝግጅቱ ተጠናቆ የኢንስፔክሽኑ አፈፃፀም ሲጀምር ልንከተላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን እና አሠራሮችን ዝርዝር ያቀርባል፡፡

ከላይ የቀረበው ምዕራፍ 2 የኢንስፔክሽኑን የእቅድ ዝግጅት ይሸፍናል፡፡ ይህ ምዕራፍ ደግሞ በግብር ከፋዩ ፋብርካ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚደረገውን የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ይሸፍናል፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን በተሳካ ሁኔታ የሚከናወንበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

- የግብር ከፋዮችን የሕግ ተገገርነት ማሳደግ፤ እና
- ትክክለኛ የታክስ ማሳወቂያዎች በማቅረብ የታክስ ገቢን ለመጨመር ነዉ፡፡

በተጨማሪም የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ከማሳወቅ የተነሳ ውሳኔ እና ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ የሕግ ተገዥነት ችግሮችን ለመለየት፤ የሕግ ተገገርነትን ለማሻሻል አስፈላጊ በሆኑ መዝገቦች ላይ ግብር ከፋዮችን ለማስተማር፤ እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ ኦፊሰሮች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማገዝ ናቸው፡፡

ይህ ክፍል በሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የኢንስፔክሽን ሥራዎች ላይ የተለመዱ አጠቃላይ መስፈርቶች ያቀርባል፡፡

ከግለሰብ የኢንስፔክሽን ዓይነቶች አንፃር ተጨማሪ ዝርዝር ተዛማጅ በሆኑ የማኑዋሉ ክፍሎች ውስጥ ተካትቷል፡፡

### 3.1.1. የፀደቁ ቅጾች

ኢንሰፔክሽን ለማከናወን ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች የሚከተሉትን ቅጾች ማቅረብ አለባቸው፡-

- የየኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ፣
- የኢንቨንተሪ ሪፖርት ቅጽ፣ እና
- የዋጋ ዝርዝር፡፡

በሚካሄደው ምርመራ ውስጥ እነዚህ ቅጾች የተሞሉበትን መንገድ እና የቀረበውን መረጃ መገምገምዎን ያረጋግጡ፡፡

ለምሳሌ፡-

- ለቀረበው የነጠላ ዋጋ / የአንዱ ዋጋ የቀረበዉ መለኪያ ግልጽ ስለ መሆኑ ለመገንዘብ ምን ያህል ነጠላ መጠኖች ከዕቃዎቹ ብዛት ጋር እንደሚታረቁ መረዳትዎን ያረጋግጡ፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ያክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- አስፈላጊ የሆኑት የመረጃ ዓምዶች (data columns) በትክክል መሞላታቸዉን ማረጋገጥ እና
- የኢንሸንተሪ ሪፖርት ቅጹ እና የዋጋ ዝርዝሩን በተመለከተ መረጃው በግልፅ ሊነበብ የሚችል መሆኑን ማየት ያስፈልጋል፡፡

ከምርመራው በፊት እነዚህን ጉዳዮች በማስታዎሻ በመያዝ ከእያንዳንዱ ቅጽ ምን እንደምንጠብቅ ግብር ከፋዩን ለማስተማር ልናነሳቸው እንችላለን፡፡

የሥራ ማከናወኛ ቅጾች እና ቴምፕሌቶች በምዕራፍ 4 ውስጥ ተካትተዋል፡፡

### 3.1.2. አጠቃላይ መርሆዎች

የኢንስፔክሽኑ ምድብ ከተመረጠ እና ምርመራው የሚደረግበት ግብር ከፋይ ከተለየ፣ የኢንስፔክሽን ቡድኑ በመገናኘት በሥራው ወሰን እና የስራ ክፍፍል ላይ በጋራ ይስማማሉ፡፡

ቡድኑ በእቅድ ወቅት የሰበሰቡትን መረጃ በመተንተን እና ቀደም ሲል በግብር ከፋዩ ላይ የተካሄዱ የኦዲቶት እና ኢንስፔክሽን ታሪክ በመገምገም የሚኖርብዎ ሲሆን የተሰጡ ምክረ-ሃሳቦችን እና የተለዩ ጉዳዮችን በማስታዎሻ የተያዙት መሚላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸዉ ::

የመጨረሻው የዕቃ ቆጠራ መቼ እንደተካሄደ እና የሚቀጥለው ቆጠራ መቼ እንደሚካሄድ ማወቅ ይኖርብዎታል፡፡

በገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብት ውስጥ የዕቃ ቆጠራ መካሄዱን የሚያሳይ ምንም ማስረጃ ከሌለ፣ ይህን መረጃ ከግብር ከፋዩ ያግኙ፡፡ በድርጅቱ እዉቅና ያለዉ እና በፊርማ የተረጋገጠ የቆጠራ ሰነድ ከለ በዚያ ቀን የተያዘው የዕቃ ቆጠራ በዚያ በተወሰነ ቀን የተካሄደዉ የቆጠራ መጠን ሆኖ ያገለግላል፡፡ :: ያንን እንደ መነሻ በመጠቀም ከዚያ ቀን ጀምሮ ያለውን መረጃ በመጠቀም ግመገማዉን መቀጠል ይቻላል፡፡

### 3.1.3. በኢንስፔክሽኑ ወቅት

ለኢንስፔክሽን ስራ ወደ መስክ ስንቀሳቀሱ፡-

- በኢንስፔክሽን ጉብኝቱ ላይ ለመገኘት ከቢሮ ከመውጣትዎ በፊት ፎቶግራፍዎ ያለበት መታወቂያ መያዝዎን ያረጋግጡ፡፡የማምረቻ ቅጥር ግቢው ሲደርሱ ትልልቅ የንግድ ድርጅቶች ከሆኑ ስለመገኘትዎ በእንግዳ መቀበያው ቦታ ያሳውቁ፣ እንዲሁም አነስተኛ ንግዶች ከሆኑ ጉብኝት ከማድረግዎ በፊት የመድረሻ ፕሮቶኮሉ መዘጋጀቱን ያረጋግጡ፡፡

- ከተፈቀደላት ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ሰራተኞች ዉሥጥ ከስራዉ ጋር ግኑኝነት ያላቸዉን ኤክሳይዝ ታክስ/ታክስ ማናጀር፣ፋይናሻል ኦፊሰርና ሌሎች ጋር የመግቢያ ስብሰባ በማድረግ እዚያ የተገኙበትን ምክንያት እና ስለሚያካሂዱት የኢንስፔክሽን ምድብ ማብራሪያ ይስጡ፡፡ ስለ ድርጅቱ የንግድ አሰራርና ከማምረት ጋር በተገናኘ ስለ መዝገብ አያያዝ በተመለከተ ግንዛቤ መወሰድ፡፡ እንድሁም ሌሎች ኢንስፔክሽኑን በተመለከተ የሚነሱ ቀደምስል በትንተና ደረጀ ተይዘዉ የሚጣሩ የተወሰኑ ጉዳዮች ካሉ ጥያቄ በማቅረብ ማጣራት፣



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ያሕመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- በአባሪው ላይ ያሉት መጠይቆች ካልተጠናቀቁ እነዚህን መጠይቆች በመሙላት ይጀምሩ። ቀደም ሲል የተጠናቀቁ እና በፋይል ላይ የሚገኙ ከሆኑ በፋይሉ ላይ ያሉትን ክንውኖችን በማየት በተጨባጭ ከሚከናወነው ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

- ይህ መጠይቅ ለሁሉም የኢንስፔክሽን ምድቦች መደረግ አለበት ምክንያቱም ይህ ግብር ከፋዩ ከእኛ ግንዛቤ ጋር በተጣጣመ መልኩ እየሠራ መሆኑን ግልፅ ያደርጋል።

### 3.1.4. የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱን ይረዱ

የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓቱን እንዲሁም የጥሬ ዕቃ አገባብ(receipt) እና የጥሬ ዕቃዎች አጠቃቀም ከማምረት፣ ከማሸግ እና ማከማቸት ጋር እንዴት እንደሚገናኙ(link) መረዳትዎን ያረጋግጡ።

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጣቸው ታክስ ከፋዮች በእጅ የሚያዙ መዝገቦችን እና በሲስተም ላይ የተመሠረቱ መዝገቦችን አጣምረው መያዛቸው የተለመደ በመሆኑ አሰቀድሞ ከሚመለከታቸዉ ድርጅቱ ሰራተኞች መረዳት እንዲሁም
የግብር ከፋዩን የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርአቱንና መረጃዎችን አልፎአልፎ ለማየትና የቁጥጥር አግባቦችን በመረጃ ለማስደገፍ ይጠይቁ

እያንዳንዱ የሚመረተው ምርት (ለምሳሌ ለልብስ አምራች ምርቶች) ለእያንዳንዱ ምርትአይነት የተለየ የምርት ኮድና ምርቱን ለማምረት የሚያስፈልጉ የግብአት ዝርዝርና መጠን የሚገልጽ ዋና መረጃ (master data) ያለው ሊኖረው ይገባል።

እያንዳንዱ ምርት በሲስተሙ ውስጥ እንዴት ተለይቶ እንደሚታወቅ እና በአመራረቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉት ጥሬ ዕቃዎች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ይረዱ።

ከኩባንያው ተወካይ ጋር ተቀምጠው በኮምፒዩተር ላይ ያለው መረጃ ከወረቀት ሰነዱ ጋር የሚዛመድ መሆኑን ያረጋግጡ።

### 3.1.5. የማምረቻ ቦታ ጉብኝት

የፈቃዱን ቅጂ እና የማምረቻውን የቦታ ፕላን በመውሰድ በግቢው ውስጥ ለመዘዋወር እና የፋብሪካውን የውስጥ ክፍሎች ለማየት በድርጅቱ ፋይል ላይ ያለውን የቦታ ፕላን(site plan) እንደ መነሻ መጠቀም ያስፈልጋል።።።

ምንም የቦታ ፕላን በፋይል ላይ ከሌለ ግብር ከፋዩ የቦታ ፕላን እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት።

በማምረቻ ቦታው ጉብኝት ወቅት መግቢያ መውጫ በሮችን፣ የጥሬ ዕቃ ማከማቻዎችን፣ የማምረቻ መሣሪያዎች (የፍሰት መለኪያ ቆጣሪዎችን / ባለቀለም ማስተላለፊያ መስመሮችን) እና የማከማቻ ቦታዎችን በተመለከተ ማስታወሻ በመያዝ መከታተል ያስፈልጋል።

ቦታው አሁን ላይ ምን እንደሚመስል እና በፋይል ላይ ካለው ጋር ያለውን ማንኛውንም ልዩነት በመገንዘብ ከኢንስፔክሽኑ የተገኘውን ልዩነት/ግኝት እንደ አንዱ በመውሰድ ግብር ከፋዩ አዲስ የቦታ ፕላን እንዲያቀርብ አስተያየት ማቅረብ ያስፈልጋል።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቦት መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

የቦታው ፕላን እያንዳንዱ የማምረቻና እና የማከማቻ ክፍል የት እንደሚገኝ በግልፅ ማመላከት አለበት፡፡ ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከእነዚህ ቦታዎች ውጭ ከተመረቱ ወይም ከተከማቹ በተፈቀደ ቦታ ውስጥ ባለመሆናቸው የኤክሳይዝ ታክሱ በዕቃዎቹ ላይ ከነቅጣቱ የሚወሰን መሆኑን እና ለታክስ ባለስልጣኑ ባለማስታወቅ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚጣል መሆኑን በመገንዘብ እንደግችት በመውሰድ ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቃል፡፡

### 3.1.6. ኢንስፔክሽኑን ማካሄድ፡ በኢንስፔክሽን አይነት

ከላይ የቀረቡት የማጣራት ሥራዎች **በእያንዳንዱ** ኢንስፔክሽን መጀመሪያ ላይ መከናወን አለባቸው፡፡ ይህም የኢንስፔክሽን ኦፊሰሩ እየተመረመረ ያለውን የንግድ ሥራ ምንነት መረዳቱን እና የግብር ከፋዩ የፋይል ማህደር በማንኛውም አዲስ መረጃ ወቅታዊ(update) መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለገቢዎች ሚኒስቴር ሳይገለፅ ማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ ከተቀየረ በሕጋዊ መንገድ ቅድመ-ማስታወቂያ ካልቀረበ በህጉ መሰረት አስፈላጊው የህግ ማስከበር እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

በምርመራ ሥራው ውስጥ መረጃን ለመሰብሰብ ሰነዶችን እና መረጃዎችን መተንተን ሲጀምሩ፣ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የቅድመ-ምርመራ (በእቅድ ጊዜ የተያዘ መረጃ) ትንተናውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በኢንስፔክሽኑ ወቅት ያረጋገጡትንና የተገኙ ማናቸውንም ግኝቶች በሚመለከት ማስታወሻ (query) በተዘጋጀዉ ተምፕሌት መያዝ ያስፈልጋልይህም በመጨረሻው የኢንስፔክሽን ሪፖርት ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዲጂታል ምስሎችን በመውሰድ ሊደገፍ ይችላሉ፡፡

ስለ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ ደረጃ በተመለከተ ለኢንስፔክሽን/ለኦዲት አመቺ ያልሆነ የሂሳብ አያያዝ ሁኔታ ካጋጠመ ይህንኑ ማስታወሻ በመያዝ የማተካከያ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ሁሉንም መረጃዎች ለመመዝገብ በምዕራፍ 4 "የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች( working notes)" ውስጥ ያሉትን ቅጾች ይጠቀሙ፡፡

ኢንስፔክሽኑ ሁሉንም ዓላማዎች የሚያሳካ መሆን አለበት፡-

- በዕለቱ መጨረሻ ላይ ሥራውን ካላጠናቀቁ ከስራ ኃላፊው ጋር በመነጋገር ስራው የደረሰበትን አግባብ በመረጃ በማስደገፍ ፋይል ተደርጎ በሚቀጥለው ቀን መመለስ እና መጨረስ ያስፈልጋል፤
- የኤክሳይስ ታክስ ከፋዩ ሠራተኞች አሠራሩን ለማሳየት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ ሊያቀርቡልዎት ካልቻሉ ይህንን ማስታወሻ በመያዝ ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 3.1.7. ማጠቃለያ



ይህ ክፍል ማንኛውም የኢንስፔክሽን አይነቶችን ለማከናወን የሚያስችሉ አጠቃላይ ተግባራትን የሚሸፍን ነው። የሚከተሉትን ሃሳቦች በሚገባ ለመረዳት ከግብር ከፋይ ጋር በቅርበት በመነጋገር መረዳት ያስፈልጋል፡-

የግብር ከፋዩን ሥራዎች እና ምርቶች፤

የሂሳብ መዝገቦቹ እንዴት እንደተያዙ፤

የማምረቻ ቦታውን አቀማመጥ እና ጥቅም ላይ የሚውሉትን መሣሪያዎች፤ እንዲሁም

ለኤክሳይዝ ታክስ ግዴታዎች ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ወይም ግለሰቦች።

በኢንስፔክሽኑ የእቅድ ዝግጅት ደረጃ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙትን ሁሉንም መረጃዎች ይተነተናሉ። መረጃው በግብር ከፋዩ እንዴት እንደተሰበሰበ ማስታወሻ በመያዝ ከኢንስፔክሽን አይነቱ ጋር የተያያዙ በወረቀት ያሉ ሁሉም ሰነዶች ከቀረበው የሲስተም መረጃ ጋር የሚዛመዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## 3.2. የኢንስፔክሽን አይነቶች፡ ዝርዝር አፈፃፀም

### 3.2.1. መግቢያ

የዚህ የኢንስፔክሽን ማኑዋል የቀደሙት ክፍሎች ኢንስፔክሽንን ከመምረጥ እና ከማካሄድ አንፃር ያለውን አጠቃላይ ጽንሰ-ሃሳብ እና ሂደት ይገልፃሉ።

የሚከተሉት ክፍሎች ደግሞ አጠቃላይ ጽንሰ-ሃሳቦቹን በመውሰድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱት በእያንዳንዳቸው የኢንስፔክሽ አይነቶች ላይ ይተገበራሉ።

የኢንስፔክሽኖቹ ዝርዝር ሁሉን-አቀፍ አይደለም። በዚህ ክፍል ያልተካተቱ ሌሎች የስጋት ገፅታዎች በሚታዩበት ጊዜ ኢኒስፔክተሩ ከቅርብ ኃላፊው ጋር በመነጋገር ሌሎች የምርመራ መስፈርቶችን በመቅረጽ ኢንስፔክሽኖችን ማካሄድ ይቻላል።

## 3.3. ፈቃድ አሰጣጥ፡ የፈቃድ አሰጣጥ ኢንስፔክሽን አፈፃፀም

### 3.3.1. ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ስለመቀበል

የገቢዎች ሚኒስቴር የምዝገባ ቡድን የማመልከቻ ቅጹን ሲቀበሉ የማመልከቻውን ዝርዝር መረጃ በመገምገም እና የተቀበሉት መረጃ ላይ አጠቃላይ ማጣራት በማድረግ ማመልከቻው ልዩ የመለያ ቁጥር ተሰጥቶት እንዲሁም የደረሰበት/ገቢ የተደረገበት ቀን ተረጋግጦ በሲስተም ውስጥ እንዲመዘገብ ይደረጋል።

ከዚህ የመነሻ ግምገማ በኋላ ታክስ ከፋዩ የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታውን የተረዳ፣ በቂ መዛግብት መያዝ የሚችል እና ዕቃዎቹ የሚመረቱበት የፋብሪካ ቅጥር ግቢ እና ማንኛውም የተገጠመ መሣሪያ ለሥራው ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጉብኝት እንዲያመቻች ማመልከቻው ወደ ኤክሳይስ ታክስ ማረጋገጫ/ኢንስፔክሽን ቡድን ይተላለፋል።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 3.3.2. የቀረበውን ማመልከቻ ማጣራት

በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ታሪክ ለሌላቸው አዲስ አምራቾች፣ ወይም አገልግሎት አቅራቢዎች፣ መደበኛውን የማመልከቻ ሂደት ሊከተሉ ይገባል።

ፈቃዱን ለመስጠት ወይም ለመከልከል ለሚያስችል የውሳኔ አሰጣጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠየቁ ሂደቶች እና ተግባራት እንደሚከተለው ተብራርተዋል፦

- የገቢዎች ሚኒስቴር የማመልከቻ ቅጹን ይቀበላል፤
- የፈቃድ/የምዝገባ ቡድኑ የቀረቡትን ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ይመረምራል፤
- የንግድ ሥራው ቀደም ሲል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚታወቅ ነው - ለምሳሌ በሌላ የንግድ ዘርፍ፤
- በኩባንያው ላይ ማጣሪያ ማድረግ - ቀደም ሲል የተመዘገበ ስለመሆኑ እና ሌሎች ታክሶችን የሚከፍል ስለመሆኑ ወዘተ፤
- የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች ዝርዝር
- ፋብሪካው የሚገኝበትን ቦታ ማጣራት - ለምሳሌ ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚገኙበት አካባቢ ስለመሆኑ ያጣሩ
- የተገለፀው ፋብሪካ እና መሣሪያ ከሚመለከተው ሥራ አንፃር ተገቢ ሰለመሆኑ ያጣሩ

ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በሪፖርት ውስጥ በማስገባት እና ለአመልካቹ አዲስ የኤክሳይስ ፋይል ይከፈትለታል። ሁሉም ተገቢ መረጃዎች መቅረባቸውን እና ሁሉም የገቡት/የቀረቡት መረጃዎች መጣራታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ። ፋይሉን ከሁሉም አስፈላጊ መረጃዎች እና የተደረጉ ማጣራቶች ጋር ለቡድን መሪዉ ያቅርቡ። ቡድን መሪዉ ደግሞ ለሚመለከተዉ ፋይል አረጋጋጭ ቡድን/ ሙያተኞች ፋይሉን በማከፋፈል እንዲረጋገጥ ያደረጋል።

የፍቃድ ማመልከቻው ሲደርስ፣ ጉብኝት ለማድረግ አመልካቹን ከማነጋገር/ከመቅጠሮ በፊት፣ የማመልከቻውን መረጃ ከዚህ በታች በ3.3.4 ተገለጸዉን ኤክሳይዝ ፈቃድ ቼክ ሊስት ጋር ያገናዝቡ።

### 3.3.3. ማመልከቻን በመቀበል ሂደት የሚጠየቁ የማረጋገጫ ጥያቄዎች

ማመልከቻው ሲደርስ አስፈላጊው መረጃ ከማመልከቻው ጋር ስለመላኩ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ለቼክ ሊስት የሥራ ማከናወኛ ሰነዶችን/ቅጾችን በምዕራፍ 4 ውስጥ ይመልከቱ።

ማንኛውም ያልቀረበ መረጃ ካለ መረጃው እንዲቀርብ መጠየቅ አለበት።

የግድ መካተት ያለበት እና ያልተካተተ የትኛውም ዓይነት መረጃ ካለ አመልካቹን በማነጋገር ሁሉንም ቀሪ መረጃዎችን እንዲቀርቡ ይደረጋል። እንዲህ ያለው ነገር የፈቃድ አሰጣጡን ሂደት ሊያዘገይ እንደሚችል በጽሁፍ ከማስጠንቀቅያ ጋር እንደየ መረጃዉ ሁኔታ የቀን ገደብ በመስጠት ያሳውቋቸው።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

### 3.3.4. ለጉብኝቱ ዝግጅት ማድረግ

ሁሉንም መረጃዎች በምዕራፍ 4 ውስጥ ባለው ተገቢ የሥራ ማከናወኛ ሰነድ(ቼክ ሊስት) ላይ ይጻፉ፡፡

ይህ አንድ ኩባንያ ፈቃድ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ እንዲሆን ካቀረበው ማመልከቻ ጋር በተያያዘ የማረጋገጫ ጉብኝት ለማድረግ ከመዘጋጀት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ጥያቄዎች በማመልከቻ ቅጹ ላይ መልስ አግኝተው ሊሆን ይችላል ነገር ግን መልሶችን ለማረጋገጥ እንደገና መጠየቅ ጠቃሚ ነው፡፡

የቀረቡትን ሁሉንም መረጃዎች ይመርምሩ፤ ይህም ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ሊጠቁሙ የሚችሉ ማናቸውንም የዜና ዘገባዎችን ለማግኘት ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በተመለከተ በኢንተርኔት ፍለጋ ማድረግንም ቢሆን ይጨምራል፡፡

### 3.3.5. ጉብኝቱን ማቀድ እና ጉብኝት ማካሄድ

ሁሉም መረጃዎች የቀረቡ መሆኑን እና መረጃዎቹም ትክክል መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ጉብኝት ያሚካሄድበትን በመወሰን ጉብኝቱን ይዘጋጃል፡፡

ጉብኝቱ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

- ከማመልከቻው ጋር የቀረቡትን መረጃዎች ለመመርመር እና የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታዎቻቸውን መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚካሄድ ስብሰባ፤ እንዲሁም

- ስለ ጊቢዉ ጥበቃ ፣ የጥሬ ዕቃ እና የመጨረሻ ምርት ማከማቻ ቦታዎችን፣ የመዝገብ አያያዝ ብቃትን ፣ ስለ ግቢዉ በሮችና መስኮቶች እና ሌሎች አካላዊ ደህንነትን በተመለከተ ለማረጋገጥ የማምረቻ ቅጥር ግቢውን ተዘዋውሮ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በሰነዱ አባሪ 'ለ' እና 'ሐ' ላይ ያሉት መጠይቆች በስብሰባው ወቅት ሊነሱ የሚገባቸውን ጥያቄዎች እና በቦታው ላይ በሚደረገው ምልከታ መረጋገጥ ያለባቸውን ነገሮች ያቀርባሉ፡፡

ሁሉም ጥያቄዎች የተጠየቁ መሆናቸውን እና ምላሾች መሰጠታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በፋብርካው ግቢ ውስጥ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ወደ ግቢው የሚያስገቡትን ማናቸውንም በሮች በማስታወሻ በመመዝገብ ለቁጥጥር አመች መሆናቸውን እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

### 3.3.6. ከጉብኝቱ በኋላ

ጉብኝቱ ከተከናወነ በኋላ ወደ ቢሮ በመመለስ ሪፖርት ይቀረባል ፡፡

እያንዳንዱን የስጋት አካባቢ በመውሰድ አመልካቹ እና የማምረቻ/ማከማቻ ቅጥር ግቢው ምን ያህል ለኤክሳይዝ ታክስ ሕጉ ተገዥ መሆናቸውን ግምገማ አለበት፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ደህንነት ዳይሬክቶሬት ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

በሥራ ማከናወኛ ሰነዶች(working notes)ምዕራፍ ውስጥ ተገቢውን ቴምፕሌት በመጠቀም ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡

የማረጋገጫ ሪፖርቱ ከተተነተነ በኋላ ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ አጋጣሚዎች ተገቢውን መረጃ በመሰብሰብ ፈቃዱ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ይገመገማሉ ::

መረጃው የብቁነት እና ተገቢነት ምዘናውን ለማለፍ በቂ ከሆነ ፈቃዱ ሊሰጥ ይችላል፡፡

አብዛኛዎቹ ጉዳዮች አጥጋቢ ሆነው ነገር ግን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ስጋት ቢኖር (ምናልባትም የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓቱ ማኑዋል በሆነ መንገድ/በእጅ የሚያዝ ቢሆን) በፈቃዱ ላይ መሟላት የሚገባቸውን አስፈላጊ ሁኔታዎች በማስቀመጥ ፈቃዱ እንዲሰጥ ፍቃዱን እንዲወስዱ በማድረግ በቀጣይ የገቢዎች ሚኒስቴር ወርሃዊ ጉብኝት ማካሄድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

አዳዲስ የንግድ ሥራዎች ወደ ታክስ መረቡ መግባታቸው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠቃሚ ነው፡፡ ነገር ግን ለታክስ ሕጉ ተገገር መሆን አለባቸው፡፡ ሁሉም አዲስ ግብር ከፋዮች ፈቃድ ከተሰጣቸው በኋላ ቢያንስ ለመጀመሪያው ዓመት ጥብቅ ቁጥጥሮች እና ግምገማዎች ይደረግባቸዋል፡፡ የታክስ ሕግ ተገገርነታቸው ደካማ ከሆነ ወይም ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከተገኘ ከባድ ቅጣቶች ሊጣሉ ይገባል፡፡

### 3.3.7. የክትትል እርምጃ

የኤክሳይዝ ፈቃዱን ለመስጠት ተወስኖ ፈቃድ ከተሰጠ ፍቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በሦስተኛ ወር ላይ ጉብኝት ለማድረግ በሲስተሙ ውስጥ ማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል ::

በዚህ ጉብኝት ወቅት፣ ግብር ከፋዩ ግዴታዎቹን መወጣቱን ለማረጋገጥ በተመሳሳይ መጠይቆች(ፈቃድ ሲሰጥ በነበሩ መጠየቆች) መጠቀም ይችላሉ፡፡

የማምረቻ ቦታው ስንት የመግቢያ እና መውጫ በሮች እንዳሉት በማስታወሻ መያዝን ጨምሮ ማናቸውንም ለውጦች ይመዝግቡ፡፡

በምዕራፍ 4 ውስጥ ያለው ተዛማጅ የሥራ ማከናወኛ ሰነድ፣ ፍቃድ ከተሰጠ በኋላ በሚደረገው የኢንስፔክሽን ጉብኝት ላይ ሊከናወኑ የሚገቡ የፍተሻ ተግባራትን በዝርዝር ያብራራል፡፡

ከጉብኝቱ በኋላ፣ ከሕግ ተገዥነት አንፃር ጥሩ የሆኑትን ወይም በቂ ያልሆኑትን አካባቢዎች በመጥቀስ ለለውጥ ከሚያግዙ ምክረ-ሃሳቦች ጋር የግኝት ሪፖርት ይጻፉ፡፡

**በየትኛውም አካባቢ ግዴታን ያለመወጣት ሁኔታ ሲኖር ታክስ ከፋዩን ስለግዴታው በማስተማር ማሻሻያዎችን ለመገምገም በሦስት ወራት ውስጥ ለሚደረግ ተጨማሪ ጉብኝት ማስታወሻ ይያዙ፡፡**

### 3.3.8. ነባር ግብር ከፋዮች



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ ★ የታክስ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 ★ ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

አዲስ ፈቃድ የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን መወጣታቸውን ከማረጋገጡ በተጨማሪ፣ ነባር ባለፈቃዶችም በተሰጣቸው ፈቃድ መሠረት ግዴታቸውን እየተወጡ መሆናቸውን በተለይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብራንድ እና ዓይነት እንዳልተቀየረ እና የማምረቻ ቦታው ፕላንም ከመጀመሪያው ጋር አንድ መሆኑን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡

ማናቸውም ማሻሻያዎች አስቀድመው ለገቢዎች ሚኒስቴር የተገለፀ መሆን አለባቸው፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደላቸው ሁሉም አምራቾች ካሉባቸው ግዴታዎች አንዱ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር መረጃ መለዋወጥ እና በሥራ እንቅስቃሴም ሆነ በተፈቀደ የማምረቻ ቦታ ላይ ስለሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማሳወቅ ነው፡፡

ስለዚህ ማንኛውም የገቢዎች ሚኒስቴር ሠራተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጠውን ግብር ከፋይ በጎበኘ ቁጥር ሁልጊዜም ስለ ፈቃዱ ጥያቄ በመጠየቅ መጀመር አለበት፡፡

በዚህም መሠረት ፈቃዱን እና የተፈቀደውን የቦታ ፕላን ለማየት ይጠይቁ፤ እንዲሁም ሁሉም ሥራዎች፣ በሮች እና ሕንፃዎች በፈቃዱ እና በፕላኑ ላይ በተገለፀው መልኩ እንደሚገኙእና የማረቻ መሳሪያዎች አይነትና ቢዛት ማረጋገጥ ያስፈልጋል

## 3.4. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆን ዋጋ

### 3.4.1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛዎቹ ምርቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው ዕቃዎቹ ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ በሚወጡበት ጊዜ የሚኖራቸዉን ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ምንም እንኳን የኤክሳይዝ ታክሱ በቁርጥ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ዝቅተኛ መጣኔ ያላቸው አንዳንድ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ቢኖሩም፣ አብዛኛው የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ የሚቀርበው እና የሚሰላው ማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለበት ምርት ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ያለው ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡

በዋጋ መቶኛ ዘዴ እና በቁርጥ ዘዴ መካከል ስላለው ልዩነት የበለጠ ዝርዝር መረጃ በኤክሳይዝ ታክስ የኦፊሰሩ ማኑዋል ውስጥ ይገኛል፡፡

ነገር ግን የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላበትን ዋጋ ለመወሰን ያለው ስጋት በማንኛውም መልኩ የሚደረግ ከዋጋ በታች ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ (ለኤክሳይዝ ታክስም ሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ) የገቢ መቀነስ ያስከትላል፡፡

ከተፈቀደለት ፋብሪካ የሚወጡ ሁሉም ዕቃዎች (እንደ ኤክስፖርት ካሉ የተወሰኑ አወጣጦች በስተቀር) ዕቃዎቹ ከፋብሪካው ወጪ በሚደረጉበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱ መሰላት አለበት፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያት ነፃ ርክክብ እንኳን ቢሆን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በመሆኑ እያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ዋጋ አስፈላጊ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ያክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክሱ የሚሰላበትን የዋጋ ስታንዳርድ ለማስቀመጥ ግብር ከፋዮች ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ይህ ዋጋ በቀጣዩ ወር ለሚወጡ እና ለሚሸጡ ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ምርቶች የስሌት መሠረት መሆን አለበት።

ምንም እንኳን የዋጋ ዝርዝሮች መቅረብ ቢገባቸውም ዋጋው የማምረቻ ወጪን እና ምክንያታዊ የትርፍ ህዳግን በግልፅ በሚሸፍን መልኩ መቀመጥ አለበት።

ይህ ኢንስፔክሽን የቀረበውን የዋጋ ዝርዝር በመተንተን የሚከተሉትን ያረጋግጣል፡-

- የቀረበው ዋጋ በጣም ዝቅተኛ አይደለም፤
- ዋጋው ከዕቃዎች ወጪ አንፃር ተመጣጣኝ የትርፍ ህዳግ የያዘ ነው፤
- ደንበኞች የሚከፍሉት ዋጋ ከቀረበው የዋጋ ዝርዝር ጋር ተመሳሳይ ነው፤
- ደንበኛው የከፈለው ዋጋ ከቀረበው ዋጋ ዝርዝር ያነሰ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ የሚሰላው በከፍተኛው ዋጋ ላይ ተመስርቶ ነው

### 3.4.2. የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ የሚሰላበት ዋጋ፡- ኢንስፔክሽን

ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላበት ዋጋ ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ መገለፁን እና መከፈሉን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን ለማስላት የሚውለው ዋጋ የስሌት መሠረቱ የዕቃዎቹ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ይሆናል። ነገር ግን የሚከተሉትን አያጠቃልልም፡-

ሀ) በዕቃ አቅርቦት ላይ የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤
ለ) የኤክሳይዝ ቴምብሮች (ካለ) ወጪ፤ ወይም
ሐ) ሊመለሱ የሚችሉ መያዣዎችን ወጪ።

የኤክሳይስ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች/አገልግሎቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን ለማስላት የሚውለው ዋጋ፡-

ሀ) የተመዘገበው ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች/ አገልግሎቶች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተደረገ ግብይት ከሆነ ተከፋይ የሆነው የ እቃ/አገልግሎቱ ዋጋ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፤
ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የ እቃዎች/አገልግሎቶቹ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ።

የእያንዳንዱ ግብይት/ ዕቃ አወጣጥ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ በደረሰኝ ላይ መታየት አለበት።

ሽያጭ የተከናወነ ባይሆንም እንኳን ሁሉም ከፋብሪካ የሚወጡ ዕቃዎች (ወደ ውጭ ለመላክ ወይም የዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው ሰዎች ወደሚገለገሉበት ቦታ ለመጓጓዝ በትክክል ከወጡት በስተቀር) የኤክሳይዝ ታክስ ሒሳባቸው መመዝገብ እና መከፈል አለበት።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቢሮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

### 3.4.3. ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር

መመሪያ ቁጥር 67/2013 አንቀጽ 25 ወይም በተሸሻለዉ መመሪያ ቁጥር 1071/2017 አንቀጽ 32 ሁሉም የተፈቀደላቸው የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች በሚያመርቷቸው ሁሉም ምርቶች እና የምርት ኮዶች ላይ የሚጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ ለማስላት የሚጠቀሙበትን ዋጋ የሚገልጽ ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር እንዲያቀርቡ ያስገድዳል።

የእያንዳንዱ ምርት ዋጋ በምርት ዓይነት፣ በመያዣው መጠን እና ዓይነት መቅረብ አለበት።

ዕቃው ከቀረበው የዋጋ ዝርዝር በላይ የተሸጠ እንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የሚሆነው ከፍተኛው ዋጋ ይሆናል። ዕቃው ከቀረበዉ ከዋጋ ዝርዝር በታች የተሸጠ እንደሆነ ወይም ሽያጭ ሳይከናወን ከፋብሪካ ከወጣ (ለምሳሌ፣ ምርትን ከማምረቻው ቦታ ወደ ማሰራጫ መጋዘን ማጓጓዝ) የስሌት መሠረቱ በዋጋ ዝርዝሩ ላይ የተመለከተው ዋጋ መሆን አለበት።

ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የማስረከቢያ ሰነድ እና/ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦

- (ሀ) ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበትን ቀን፤
- (ለ) የዕቃውን ማስረከቢያ ቦታ፤
- (ሐ) የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካው የሚወጣ ከሆነ፣ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወሻ፤
- (መ) ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ፣ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወሻ፤
- (ሠ) የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት፤
- (ረ) የዕቃዎቹን ብዛት፤
- (ሰ) የእያንዳንዱ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ዋጋ፤
- (ሸ) ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን፤

### 3.4.4. ከኢንስፔክሽኑ በፊት የሚገመገሙ ሰነዶች እና መረጃዎች

የሚከተለውን መረጃ ለመገምገም በሲግታስ ላይ ወይም ለወርኃዊ የዋጋ ዝርዝር በወረቀት ቅጂ በቀረበው ላይ ይገኛል፦

ሀ. በግብር ከፋዮች የቀረበ የዋጋ ዝርዝር

ለ. የማስታወቂያ ቅጾች

ሐ. እንደ ደረሰኞች እና የማስረከቢያ ሰነዶች ያሉ ከማስታወቂያ ቅጾች ጋር የቀረቡ ተጨማሪ መረጃዎች።

### 3.4.5. መረጃውን መሰብሰብ



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ማዕከል ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

**የዋጋ ዝርዝሮች**

የዋጋ ዝርዝሮች በወረቀት ቅጅ ቅጾች በእጅ ገቢ ይደረጋሉ፡፡

ለምርመራ ለተመረጠው ጊዜ የሁሉንም ምርቶች ዋጋ በኤክሴል ሰንጠረዥ በማስገባት ይተንትኑ፡፡

የቀረበውን ዋጋ እና ማንኛውንም ደጋፊ መረጃ ከታች በአባሪ 'ሀ' ላይ ባለው ቅጽ ይመዝግቡ፡፡

**የማስታወቂያ ቅጽ**

የማስታወቂያ ቅጹ የኤክሳይዝ ታክሱ የተሰላበት ዋጋ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ሳጥን ወይም ክፍት ቦታ ይዟል፡፡ ተገቢውን የማሳወቂያ ቅጽ በተመለከተ ማስታወሻ በመያዝ በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡

**ተጨማሪ መረጃ**

ለማሳወቂያ ቅጹ እንደ አንድ መመዘኛ ግብር ከፋዩ ደረሰኞችን እና የማስረከቢያ ሰነዶችን ያቀርባል፡፡

ከዋጋ ዝርዝሩ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በወረቀት ሰነድ ይቀርባሉ፡፡

ሁሉንም መረጃዎች ወደ ኮኤክሴል የዳታ ትንተና ሰነድ በማስገባት በመተንተን ልየነቱን ማመዛዘን ያስፈልጋል ፡፡

### 3.4.6. መረጃውን መተንተን

በዚህ ሂደት ውስጥ ምርቱን በመያዣው ዓይነት እና መጠን በሚያሳየው የምርቱ ኮድ አማካይነት መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ መረጃ በመያዣው ዓይነት እና መጠን ላይ ያተኮረ የእያንዳንዱን ብራንድ ብዛት ያሳያል፡፡

በኤክሴል ሰንጠረዥ ውስጥ የተተነተነው ዳታ በግብር ከፋዩ የተያዘውን መረጃ ለማረጋገጥ በቂ መረጃ ይሰጣል፡፡

ግብር ከፋዮች ለእያንዳንዱ ብራንድ የመያዣ መጠን እና ዓይነት የምርት ኮድ በመስጠት እያንዳንዱን ምርት ይለያሉ፡፡

ለእያንዳንዱ የምርት ኮድ የቀረበውን ዋጋ በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ፤ በቦታው ላይ በሚገኙበት ጊዜም የእያንዳንዱን የምርት ኮድ የምርት ወጪ እና የትርፍ ህዳግ ለማስላት የአምራቹን ሲስተም መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ለመመዝገብ በምዕራፍ 4 በተዛማጅ የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ውስጥ ያለውን ቴምፕሌት ይጠቀሙ፡፡

ይህ በመነሻነት የሚከናወን የመረጃ መሰብሰብ ሂደት ዓላማው ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚውለውን ዋጋ ለመሞገት የሚያገለግል ማነፃፀሪያ ማቅረብ ነው፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነዶች ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የዋጋ መጠየቂያ ደረሰኞችን ከቀረበው ዋጋ አንፃር በሚተነትኑበት ጊዜ ማናቸውም ምርቶች ከቀረበው የዋጋ ዝርዝር በላይ በሆነ ዋጋ መሸጣቸውን እና ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ የተሰላ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

የተነተኑትን መረጃ እና ግኝቶቹን የሚያሳይ ሪፖርት ያዘጋጁ፡፡

በዚህም መሠረት ምርመራው በዋናነት የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት ዋጋ እና የማሸጊያ መጠን በማረጋገጥ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

### 3.4.7. ለኤክሳይስ ታክስ የዋጋ ቁጥጥር የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ

ሁሉም የሚመለከታቸው ለኢንስፔክሽን ቡድኑ የተመደቡ ኦፊሰሮች በውይይቱ ላይ ሊገኙ ይገባል፡፡ ይህም በኢንስፔክሽኑ ዕቅድ ላይ ለመወያየት እና ማን ምን ዓይነት ተግባራትን እንደሚያከናውን ስምምነት ላይ ለመድረስ እድል ይሰጣል፡፡

የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው ከላይ የተተነተነውን መረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት የቀረበውን የዋጋ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ላይ ያተኩራል፡፡ ለምሳሌ፦

- የዕቃዎችን ወጪ እና የትርፍ ህዳግ ስሌት መፈተሽ፤
- በደረሰኞች ላይ ያለውን ዋጋ ማረጋገጥ፤
- በማስታወቂያ ቅጾች እና በዋጋ ዝርዝሮች ላይ ያለውን ዋጋ እና ፡
- የሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ዋጋን መፈተሽ

ደረሰኞችና የማስረከቢያ ሰነዶችን ከተነተኑ በኋላ ወካይ የሆነ የሰነዶች ናሙና (ከገቡት ውስጥ 20%) በመምረጥ የሰነዶችን ቅጂ ይውሰዱ፡፡

የ20% ናሙናው በዘፈቀደ (Random sampling) የናሙና አወሳሰድ መሰረት መመረጥ አለበት፡፡

እነዚህን ሰነዶች ወደ ጉብኝቱ ቦታ በመውሰድ እና መረጃው ለማስታረቅ በሲስተም/ በእጅ የተያዙትን መዛግብትን አደራጅቶ መያዝ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው የሚከተሉትን መረጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

- በምርመራው ቅልጥፍና ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የግብር ከፋዩ የታክስ ህግ ተገዥነት ታሪክ እና ሌሎች የሚታወቁ የስጋት ምክንያቶች (ጥበቃና ደህንነትን ጨምሮ)፤
- የኤክሳይስ ታክስ ማስከፈያ ግዴታ የሚጣልበት ቦታ፣ የምርት ዓይነቶችን እና የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳደብ ሥርዓት (HS codes) ግንዛቤ፤
- ያለፈው የኢንስፔክሽን ውጤቶች በተለይም በገቢዎች ሚኒስቴር የተጠየቁ የታክስ ህግ ተገዥነት ማሻሻያ ርምጃዎች፤
- በግብር ከፋዩ ፈቃድ ውስጥ የተቀመጡትን ሁኔታዎች ማወቅ፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቢሮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 3.4.8. በኢንስፔክሽኑ ወቅት

መጀመሪያ የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በማግኘት አጠቃላይ ስለኢንስፔክሽኑ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመስጠት ከሁሉም የሚመለከታቸው የድርጅቱ ሠራተኞች ጋር በመነጋገር፣ አጠቃላይ ስለድርጅቱ የንግድ አሰራር፣ የአመራረትና የቁጥጥር አግባብ መረጃ መጠይቆችን በማቅረብ ካሚሉ በኋላ ይህንኑ መረጃ እና ሌሎች በቅድመ ኢንስፔክሽን ስብሰባ ወቅት የተያዙ መረጃዎችን ለማጣራት ቦታውን ተዘዋውረው ከተመለከቱ በኋላ የተመረጡ ሰነዶችን እንዲያቀርብ ለግብር ከፋዩ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

የምርት ወጪ እንዴት እንደሚሰላ እና ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ከሚውለው ዋጋ አንፃር ምን ያህል የትርፍ ህዳግ እንደተቀመጠ ማብራሪያ እንዲሰጥ ግብር ከፋዩን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ለምርመራው ለተመረጡ ወሳይ ናሙና አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም የምርት ኮዶች ጠይቆ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት/ብራንድ የአዘገጃጀት ቀመር (recipe) መረጃ በመውሰድ መረዳት ::

የዕቃዎችን ወጪ በምርቶች ብዛት ይከፋፍሉ እና ግብር ከፋዩ የዕቃዎችን ወጪ በሚያሰላበት ሁኔታ ላይ ወጥ የሆነ አካሄድ መኖሩን ያረጋግጡ፡፡

በእያንዳንዱ የምርት ኮድ ላይ የቀረበውን ሁሉንም መረጃ በማነፃፀር ማናቸውም ልዩነቶች በታዩ ጊዜ ጥያቄ(query)በቴምፕሌቱ መሰረት ለጥያቄው ምላሽ እንዲሰጡበት ጥያቄውንያቅርቡ፡፡ በድርጅቱ አጥጋቢ ምላሽ ካልተገኘ ወደ ግኝት በማስተላለፍ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

ለእያንዳንዱ ብራንድ ወይም የምርት ዓይነት በተመለከተ ሌሎች ማስታወሻዎች በኢንስፔክሽኑ ወቅት የሚያጋጥሙትን በምዕራፍ 4 ውስጥ ባለው የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ላይ ማስታወሻዎችን መያዝ ያስፈልጋል (ከግብር ከፋዩ የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት ለመናበብ እያንዳንዱን የምርት ኮድ ይጠቀሙ)፡፡

### 3.4.9. ማጠቃለያ

የኤክሳይዝ ታክስን ከዋጋ በታች አሳንሶ የማስታወቅ ድርጊትን ከሚያስከትሉ ዋና ዋና ስጋቶች አንዱ አምራቾች የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት በጣም ዝቅተኛ የሆነ ዋጋ ሲጠቀሙ ነው፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ ኦፊሰሮች ከአምራቾች እና ትኩረት ከሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች የሚመነጩ አዝማሚያዎችን ለመተንተን እና ለመለየት የሚያገለግል መጠነ ሰፊ መረጃ ይገኛል፡፡

እዚህ ላይ አንዱ ችግር ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ከሚውለው ዋጋ አንፃር ሲታይ ከዚህ መረጃ ውስጥ አብዛኛው በእጅ (ማኑዋል በሆነ መንገድ) የሚቀርብ ነው፤ በመሆኑም መረጃው ከዚህ ክፍል ጋር በተያያዘው የኤክሴል ሰንጠረዥ ውስጥ በሚገባበት ጊዜ በትዕግስትእና በትክክል በመመርመር ወደ መሥሪያ ወረቀቱ (worksheet) ማስገባት ይገባል፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

አንዱ መረጃው ወቅታዊ ሆነ በኋላ ጥቅም ላይ የዋለው ዋጋ ከቀረበው የዋጋ ዝርዝር ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ መረጃውን ከደረሰኞች እና የማስረከቢያ ሰነዶች ጋር መመሳከር አለበት እንዲሁም በዋጋ ዝርዝሩ ውስጥ በአምራቹ የቀረበው ዋጋ የዕቃዎችን ሁሉንም ወጪዎች እና ተመጣጣኝ የትርፍ ህዳግ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ማቀድ ይችላሉ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

## 3.5. የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ትርጓሜ እና አመዳደብ

### 3.5.1. መግቢያ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ሠንጠረዥ አንድ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር፣ ትርጓሜዎችን እና የግብር ማስከፈያ መጣኔዎችን ይደነግጋል።

ሠንጠረዡ የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ የተጣለባቸውን በርካታ ምርቶችን እና ንዑስ-ምርቶችን የሚያጠቃልል ቢሆንም፣ በዘርፍ ደረጃ ሲቀመጡ የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ የተጣለባቸው ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፦

- የምግብ ምርት፡- (ለምግብነት የሚውሉ የአትክልት ዘይቶች፣ ማርጋሪን፣ ስኳር እና ወለላ/ሽሮፕ፣ ጨው፣ ቼኮሌት እና ጣፋጮች፣ማስቲካ)፤
- መጠጦች፡- የአልኮል እና አልኮል አልባ (በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ለስላሳ መጠጦችን ጨምሮ)፤
- ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው ንፁህ አልኮል(በቀጥታ ለመጠጣት የማይውል)፤
- የትምባሆ ቅጠል እና የትምባሆ ምርቶች፤
- የማዕድን ውሃ፤
- ሽቶዎች እና መዋቢያዎች፤
- ርችቶች፤
- የፕላስቲክ ከረጢቶች (ፌስታል)፤
- ሳማዎች፤
- ጨርቃ-ጨርቅ እና የጨርቃ-ጨርቅ ውጤቶች፤
- ሰው ሠራሽ አበባዎች፤
- ዊግ፣ የውሸት ጢም፣ ቅንድብ፣ ሽፋሎች፤
- አስቤስቶስ፤
- ዕንቁዎች እና ሌሎች ጌጣጌጦች፤
- ተሽከርካሪዎች እና የሞተር ብስክሌቶች፤
- የቁማር ማሽኖች፣ የመጫወቻ ካርታ እና የካርኒቫል/የበዓል መዝናኛዎች፤
- የትንባሆ ማጨሻ ፒፓዎች እና ሲጋር/የሲጋራ መያዣዎች

### 3.5.2. ትርጓሜዎች/ሲያሜዎች

በእያንዳንዱ ምርት ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ የማስከፈያ መጣኔ ለመረዳት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ምንነት የሚገልፁ ትርጓሜዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው።

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ሠንጠረዥ አንድ አንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ትርጓሜዎች በተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳደብ ሥርዓት ታሪፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋሉት የሸቀጦች ኮድ ጋር የተያያዙ ሲሆን ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባት / ከጉምሩክ ቀረጥ አንፃር ይተረጉማሉ። ነገር ግን አንዳንዶቹ ትርጓሜዎች የተሰጡት በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚመረቱ የሀገር ውስጥ ምርቶች ነው።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነድ አስተዳደር ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ በሚተገበርበት ጊዜ በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚመረቱትን ሁሉንም አግባብነት ያላቸው ምርቶች ከትክክለኛው የምርት ኮድ አንባር እንዲፈተሹ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የሸቀጦች ኮዶች እና ትርጓሜዎች አንዳንዴ በጣም አሻሚ ስለሚሆኑ፣ የትኛው የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ እንደሚጣል በትክክል ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፣ ኮድ 2203.0000 "ማናቸውም ቢራ፣ የሚፈሉ መጠጦች (ሳይደር፣ ፔሪ፣ ሜድ፣ ኦፔክ ቢራ)፣ እና የሚፈሉ መጠጦች እና የአልኮል አልባ እና የአልኮል መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ እና ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፣ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ መጠጦችን" ያጠቃልላል።

ነገር ግን ከቢራ እና ወይን ውጪ ያሉት የሚፈሉ መጠጦች (ለምሳሌ ሳይደር እና ፔሪ) በተጣጣመ የሸቀጦች የታሪፍ ኮድ 2206 ስር ስለሚወድቁ ይህ ትርጓሜ ለኢትዮጵያ ገበያ ብቻ የተለየ ነው።

በተመሳሳይ የአልኮል መጠጦች በአልኮል ላይ የተጣለው መጣኔ የሚከፈልባቸው የምርቱ የአልኮል ይዘት መጠን (abv) 0.5% እና ከዚያ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ነው። አንዳንድ አልኮሆል አልባ መጠጦች በምርት ሂደቱ ምክንያት ከዚህ ጋር ሊቀራረቡ ስለሚችሉ የሚጣልባቸውን ትክክለኛውን አመዳደብ እና መጣኔ ለመወሰን ናሙናዎች በየጊዜው መወሰድ አለባቸው።

ግብር ከፋዮች በራስ-ታክስ ስሌት የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያቸው ውስጥ የተጠቀሙት የታክስ መጣኔ በሚገመገምበት ጊዜ የሚመረቱት ምርቶች ባህሪ እና የማምረት ሂደቱ በግልፅ የታወቀ መሆኑኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፣ ወደ ቢራ የሚጨመር ማናቸውም የአልኮል መጠጥ ቢራውን የአልኮል መጠጦች ላይ የተጣለው የታክስ መጣኔ የሚከፈልበት ምርት እንዲሆን ያደርገዋል።

### 3.5.3. የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች በዋጋ መቶኛ ላይ የተመሠረተ የኤክሳይዝ ታክስ ይሰላባቸዋል። ይሁን እንጂ ስሌቱ በቁርጥ ዘዴ የሚከናወንባቸው ሸቀጦችም አሉ።

በዋጋ ላይ የተመሠረቱ መጣኔዎች ከሚሸጡት ዕቃዎች ዋጋ ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው በዋጋ ንረት መጨመር ምክንያት የሚኖር የዋጋ ጭማሪ ወይም በገበያ ፍላጎት ምክንያት ዋጋው ሲጨምር ከሽያጩ የሚገኝ ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ገቢን ይጨምራል።

ይሁን እንጂ በቁርጥ የሚጣለው የማስከፈያ መጣኔ ከዋጋው ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ስለዚህ በቁርጥ የሚጣሉት መጣኔዎች ከዋጋ ንረት ጋር እንዲጣጣሙ በመደበኛነት በየዓመቱ መሻሻል አለባቸው።

የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ጉዳይ በገንዘብ ሚኒስትሩ ይስተናገዳል።

### 3.5.4. ስጋቶች



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 የሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

አብዛኛዎቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ሠንጠረዥ አንድ ላይ ባለው ለምርቱ በተቀመጠው አጠቃላይ የሸቀጦች ኮድ እና ትርጓሜ በቀላሉ ሊታወቁ ይችላሉ።

ነገር ግን አንድ ዘርፍ (ለምሳሌ አልኮል) በርከት ያሉ መጣኔዎች ሲኖሩት፣ የአመራረት ሂደቱን እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምርቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችን ምንጭ በተመለከተ ጥብቅ ምርመራ መደረግ አለበት።

### 3.5.5. ምርት ተኮር ትርጓሜዎች (Specific definition)

**የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በኢትዮጵያ**

| የሸቀጦች ኮድ | ትርጓሜ |
|---|---|
| ምዕራፍ 15 | ለምግብነት የተዘጋጀ የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብ እና ዘይት እና የእነዚህ ተዋጽኦ ውጤቶች፤ ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከተለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የማይቻል በከፊል ወይም በሙሉ ሀይድሮጂን የተጨመረበት የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብ እና ዘይት። |
| 17.01 | ስኳር፤ ለህክምና አገልግሎት የሚውል ዓይነትን ሳይጨምር |
| 1704.1000 | ማስቲካ |
| 1704.90 እስከ 1806.90 | ለቀጥታ ፍጆታ እና ለማጣፈጫነት የተዘጋጀ ቸኮሌት |
| 2106.9040 | ዱቄት ለስላሳ መጠጦች |
| 2201.1000<br>2201.9000 | ውሃዎች፣ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ የማዕድን ውሃዎች እና ጋዝ ያላቸው ውሃዎች፣ ስኳር ወይም ማጣፈጫ ያልተጨመረባቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው ያልተደረጉ |
| 2202.1000 | ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ያላቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉ የማዕድን ውሃዎች እና ጋዝ ያላቸው ውሃዎች |
| 2202.9990 | ውሃ እና ስኳር በመጨመር ለፍጆታ ዝግጁ የሆኑ አልኮል አልባ መጠጦች ነገር ግን የአትክልት እና የፍራፍሬ ጭማቂን አያካትቱም፤ ያልተብላሉ፣ ስኳር ወይም ማጣፈጫ ያላቸውም ሆነ የሌላቸው የአልኮል መጠጦች ያልተጨመረባቸው |
| 2202.9100 | የአልኮል ጥንካሬው ከ0.5% ያልበለጠ አልኮል አልባ ቢራ |
| 2203.0000 | ከብቅል የተዘጋጀ ቢራ |
| | ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ በበቀለ ገብስ የተመረተ ቢራ |
| | ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ (ግብዓት) የተመረተ ቢራ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሪተ መዛግብትና ደክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| 2204.1000 | ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በሀገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ የወይን ጠጅ |
| 2204.10 እስከ 2205.90 | ውሃን ሳይጨምር ከክብደቱ ከ75% በታች በሀገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ የወይን ጠጅ |
| 2206.00 | የሚፈሱ መጠጦች (ለምሳሌ ሳይደር፣ ፔሪ፣ ሜድ፣ ኦፔክ ቢራ) እና የሚፈሱ መጠጦች እና አልኮል አልባ መጠጦች እና የአልኮል መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፤ **የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ** |
| 2207.10 እና 2208.9090 | ባህሪው ያልተለወጠ ኤቲል አልኮሆል |
| 2208.20 እስከ 2208.70 | የወይን ጠጅን ወይም ማርክን በማጣራት የሚገኙ መጠጦች ዊስኪዎች፣ ሩም፣ እንዲሁም ከተብላላ የሸንኮራ አገዳ ውጤት በማጣራት የሚገኙ ሌሎች መጠጦች ጂን፣ ጁኔቫ፣ ቮድካ፣ እንዲሁም ሊከርስና ኮርዲያልስ |
| 2208.9010 | የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ ድብልቅ መጠጦች |
| 2208.9090 | የአልኮል ይዘታቸው 7% እና ከ7% የበለጠ ነገር ግን ከ80% ያነሰ የአልኮል መጠጦች ከላይ ባለው ክፍል ያልተሸፈኑም፡፡ |
| 2401.1000 | ትምባሆ፣ ያልተፈበረከ/ያልተቀነጠሰ |
| 2401.2000 | ትምባሆ፣ በከፊል ወይም በሙሉ የተቀነጠሰ |
| 2401.3000 | የትምባሆ ውዳቂ |
| 2402.1000 | ሲጋሮች፣ ቼሩትስ፣ ሲጋሪሎስ፣ ትምባሆ የያዙ |
| 2402.2000 | ትምባሆን የያዙ ሲጋራዎች |
| 2402.9000 | ሲጋሮች፣ ቼሩትስ፣ ሲጋሪሎስ እና እንደ ትምባሆ የሚያገለግሉ ሲጋራዎች |
| 2403.1900 | የሚጨስ ትምባሆ፣ በማናቸውም ምጠና እንደ ትምባሆ የሚያገለግሉ ነገሮችን የያዘ ቢሆንም ባይሆንም፤ ይህ ምድብ የፍራፍሬ ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉም ያልተደረጉም የትምባሆ እና ግሊሰሮል ቅልቅል የያዘ ባለመዓዛ ዘይቶች እና ምዝምዞች፣ ሞላሰስ ወይም ስኳር ቢጨመርባቸውም ባይጨመርባቸውም በትምባሆ ማጨሻ የውሃ ቱቦ የሚጨስ ትምባሆን አይጨምርም፡፡ |
| 2403.9100 | የተዋሃደ ወይም እንደገና የተዘጋጀ ትምባሆ |
| 2403.9900 | ሱረት፣ የትምባሆ ምዝምዞች እና ኤሰንሶች |
| 2501.0010 | ጨው |
| ምዕራፍ 27 | ነዳጅ፡- የአውሮፕላን ነዳጅ፣ ቤንዚን ተራ ወይም ሱፐር፣ ፔትሮል፣ ጋዞሊን፣ ሌሎች የሞተር ስፕሪቶች |
| 3303.0000 | ሽቶዎች እና ቶይሌት ዋተርስ |
| 3304.1000 | የከንፈር ቀለም ዝግጅቶች |
| 3304.2000 | የዓይን መኳኳያ ዝግጅቶች |
| 3304.3000 | የእጅ ወይም የእግር ማሳመሪያ ዝግጅቶች |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ደህንነቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| 3304.9990 | ግሪስ ፔይንት፣ የቁንጅና ክሬሞች፣ ኮልድ ክሬም፣ መኳኳያ ክሬም፣ ክሊንሲንግ ክሬም፣ የተጨማደደ ቆዳ ማስተካከያ ኢንጀክተብል ኢንትራኩታኒየስ ጄል፣ ከንፈር ማወፈሪያ (ሃይሉሮኒክ አሲድ የያዙትን ጨምሮ) |
| 3305.2000 | የፀጉር ማለስለሻ ወይም ማከርደጃ ዝግጅቶች |
| 3305.3000 | የፀጉር ቀለም |
| 3305.9090 | የፀጉር ስፕሬይ፣ ፀጉር እንዲያብረቀርቅ ማድረጊያ እና የፀጉር ማንጫ ዝግጅቶች |
| 3604.1000 | ርችቶች |
| 3923.2110<br>3923.2910 | የፕላስቲክ ከረጢቶች (ፌስታል) |
| 4011.10 እስከ 4013.90 | ከላስቲክ የተሠሩ የተሸከርካሪ ጎማዎች |
| 50 | በፋብሪካ የተፈበረኩ ጨርቃ-ጨርቅ እና የጨርቃ-ጨርቅ ውጤቶች |
| 57 | ምንጣፎች እና ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ የወለል መሸፈኛዎች |
| 6702.1000<br>6702.9000 | አርቴፊሻል አበባዎች |
| 6703.00 to 6704.90 | ፀጉር |
| 6811.40 እስከ 6813.20 | አስቤስቶስ |
| 71 | ጌጣጌጦች |
| 87 | ተሸከርካሪዎች፤ በዚህ ምድብ 38 የተለያዩ የተሸከርካሪ ምድቦች አሉ |
| 9505.2000 | ሁሉም ዓይነት የቢሊያርድ ዕቃዎች እና ተጨማሪ መሣሪያዎች |
| 9504.3000 | በሳንቲሞች፣ በባንክ ኖቶች /በወረቀት ገንዘብ/፣ በባንክ ካርዶች፣ በቶክን ወይም በሌላ ዓይነት የክፍያ ዘዴ የሚሠሩ ሌሎች መጫወቻዎች |
| 9504.4000 | የመጫዎቻ ካርዶች |
| 9504.5000 | የቪዲዮ ጌም ኮንሶሎች እና ማሽኖች |
| 9504.9000 | የመዝናኛ ዕቃዎች፣ የጠረጴዛ ወይም የቤት ውስጥ ጨዋታዎች፣ ፒንቴብልስ፣ ለካዚኖ ጨዋታዎች የሚያገለግሉ ልዩ ጠረጴዛዎች እና አውቶማቲክ የቦውሊንግ መሣሪያዎች ጭምር። |
| 9505.1010 | በእጅ የተሠሩ ለገና በዓል የሚሆኑ ዕቃዎች |
| 9505.1090 | በፋብሪካ የተሠሩ ለገና በዓል የሚሆኑ ዕቃዎች |
| 9505.9000 | የበዓል፣ የካርኒቫል፣ የአስማት መጫወቻዎች እና መቀለጃዎች ወይም ሌሎች የመዝናኛ እቃዎች ጭምር |

### 3.5.6. ምርቶችን መመርመር

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ዶክመንቴሽን ቁ.1 ሰነዶችና ቤተመዛግብት
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ምርቶች አንድ ዓይነት የምርት ምድብ ውስጥ ሆነው (ለምሳሌ፣ የአልኮል መጠጦች) የተለያየ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ይኖራቸዋል። አስመጪው ወይም አምራቹ ምርቶቹን በከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ምድብ ውስጥ መመደብ ሲኖርባቸው በአነስተኛ የኤክሳይስ ታክስ መጣኔ ምድብ ውስጥ ሊመድባቸው ይችላል።

በተመሳሳይም አምራቾች ወይም አስመጪዎች ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ሊከፈልባቸው የሚገቡ ሆነው ሳለ እንዳልሆነኑ አድርገው ሊያቀርቡ ወይም ሊያመለክቱ ይችላሉ።

ስለ ምደባው መቶ በመቶ እርግጠኛ ለመሆን ብቸኛው መንገድ ጥሬ ዕቃዎቹን ጨምሮ እያንዳንዱ ምርት እንዴት እንደተሠራ በተለይም ለቢራና ወይን ዋነኛ ጥሬ ዕቃዎች በአገር ውስጥ የመነጨ ስለመሆናቸው መረዳት ነው።

በጥያቄ ውስጥ ስላለው ምርት ላይ በተለይም በጉምሩክ የሸቀጦች ኮድ ምደባ በማጣቀሻ ሲገለጽ የበለጠ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳደብ ስርዓትን የማብራሪያ ማስታወሻዎች መመርመር አስፈላጊ ነው። ይህ ለጉምሩክ ቡድን ተደራሽ መሆን አለበት።

### 3.5.7. የአልኮል ጥንካሬ

አንዳንድ ምርቶች በአልኮል ጥንካሬያቸው ይመደባሉ፡-

**ቢራ፡** በ2203 የጉምሩክ ምድብ መሠረት ቢራ የአልኮል ይዘት መጠኑ (abv) ከ0.5% ሲበልጥ አልኮል ያለው ቢራ በመሆን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል። ማንኛውም "አልኮል አልባ ቢራ" ተብሎ የተመደበ ምርት በትክክል የአልኮል ይዘት መጠኑ (abv) ከ0.5% ያልበለጠ መሆኑን ያረጋግጡ።

**ሴሎች የሚፈሉ መጠጦች፡** እስከ 7% የሚደርስ የአልኮል ጥንካሬ ያላቸው እንደ ሳይደር፣ ሜድ እና ሳኬ ያሉ የሚፈሉ መጠጦች 7% እና ከ7% የሚበልጥ የአልኮል ጥንካሬ ካላቸው ተመሳሳይ ምርቶች ዝቅተኛ የሆነ የታክስ ማስከፈያ መጣኔ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ምንም ዓይነት ዕቃዎች በተሳሳተ ምድብ ውስጥ እንዳይመደቡ ለማድረግ የምርት ሂደቱን እና የመጨረሻውን ምርት የአልኮል ጥንካሬ ያረጋግጡ።

**ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ የአልኮል መጠጦች (RTDs)፡** የአልኮል ይዘት መጠናቸው ከ7% ያልበለጠ ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ የአልኮል መጠጦች (RTDs) የአልኮል ይዘት መጠናቸው 7% እና ከ7% ከሚበልጥ የአልኮል መጠጦች ዝቅተኛ የሆነ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ አላቸው።

### 3.5.8. የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች

የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች እያንዳንዱ አምራች በሚጠቀምባቸው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ምጣኔዎች ላይ ጠቃሚ መረጃን ይይዛሉ። በተጨማሪም ደጋፊ ሰነዶቹ የምርቶቹን ዓይነት እና ስሌቱ የተከናወነባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔዎች ያሳያሉ።

### 3.5.9. ብራንዶች እና ዋና መረጃ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

እያንዳንዱ አምራች የተመረተውን እያንዳንዱን ምርት/ብራንድ መመዝገብ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ አምራቹ ለእያንዳንዱ ምርት የምርት ኮድ ቁጥር ይሰጣል። ይህ ዋና መረጃ (master data) የሚከተሉትን የሚያካትት ቁልፍ ዳታ ይኖረዋል፦

- የምርት/ብራንድ ስም፣
- የመያዣው ዓይነት እና መጠን፣
- የአልኮል ጥንካሬ (ለአልኮል)፣
- ለኤክሳይዝ ታክሱ የስሌት መሠረት የሆነው ዋጋ፣
- ምደባ
- የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ።

ይህም የቀረበውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከማስረከቢያ ሰነዶች፣ ደረሰኞች እና የምርት መዝገቦች ጋር ሊታረቁ የሚችሉ ቁልፍ መረጃዎችን ይሰጣል።

### 3.5.10. ለትንተና የሚያግዙ መረጃዎች

አምራቾች መረጃዎችን የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ የሚከተሉት መረጃዎች በገቢዎች ሚኒስቴር ውስጥ ይገኛሉ፦

- የፈቃድ ሰነድ፣
- የማስታወቂያ ቅጽ፣
- የዋጋ ዝርዝር፣ እና
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ።

**የፈቃድ ሰነድ፦** ይህ የፈቃድ ሰነድ አምራቹ እንዲያመርት የተፈቀዱለትን የሁሉንም ብራንዶች እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ምድቦችን ዝርዝር ይይዛል።

**የማስታወቂያ ቅጽ፦** የማስታወቂያ ቅጹ በእያንዳንዱ ምርት ላይ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ለማስላት የሚያገለግሉትን የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔዎችን ይዘረዝራል። የማስታወቂያ ቅጹ የአቀራረብ መስፈርት አንድ አካል ተደርጎ በተቀመጠው መሠረት አምራቾች ከፋብሪካ ከሚወጣ እያንዳንዱ ዕቃ እና ከሚከናወን ሽያጭ ጋር የተያያዙ ደረሰኞችን እና የማስረከቢያ ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው።

**ደረሰኞች፦** ይህ መረጃ የምርቱን ስም (ብራንዱን)፣ የምርት መጠን ፣ የምርት ዋጋእና የተሰላውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ይይዛል።

**ማስታወሻ፦** አንድ ምርት በተገቢው መጠን በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች መመረቱን የማስታወቅ ጉዳይ በዚህ ማኑዋል ጥሬ ዕቃዎችን በሚመለከተው ክፍል ውስጥ ተብራርቷል።

### 3.5.11. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች(Working notes)



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ ሰ.ሃ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በምዕራፍ 4 ውስጥ ያሉትን የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች/ቅጾች ይሙሉ።

የሚከተሉትን ልብ ይበሉ፡-

የእያንዳንዱን ምርት መለያ ምልክት ያረጋግጡ። ለምሳሌ፣ አምራቹ በአንድ ምርት ላይ የቢራ ኤክሳይዝ ታክስ ከፍሎ ነገር ግን መለያው የአልኮል ወይም ለመጠጣት ዝግጁ የሆነ መጠጥ (RTD) እንደሆነ የሚጠቁም ከሆነ ምርቱን ለመመርመር ይጠይቁ።

አንድ ለመጠጣት ዝግጁ የሆነ መጠጥ 7% የአልኮል መጠን ያለው ከሆነ፣ አምራቹ በተወሰኑ ጠርሙሶች ናሙና ላይ የአልኮል ጥንካሬ ፍተሻ እንዲያደረግ ይጠይቁ።

አንድ አልኮል አልባ ቢራ 0.4% የአልኮል ጥንካሬ ካለው ከ0.5% በላይ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ምርመራ እንዲደረግ ይጠይቁ።

በአባሪ "ለ" ላይ ባለው ቅጽ ውስጥ ማስታወሻዎችን ይያዙ።

በአምራቹ የማምረቻ ቦታ ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ ለተሳሳተ ምደባ ሊጋለጥ የሚችል የእያንዳንዱን ምርት ናሙናዎች ይውሰዱ።

ከእያንዳንዱ የምርት ስብስብ (ባች) 6 ጠርሙሶችን በመውሰድ ለአምራቹ በናሙናነት ያቅርቡ።

የገቢዎች ሚኒስቴር የላቦራቶሪ ምርመራዎች ለማካሄድ የሚያስችል ላቦራቶሪ ከሌለው ምርመራዎቹን ለማካሄድ የሌሎች አካላት ላብራቶሪዎችን ወይም የአምራቹን ላቦራቶሪ መጠቀም ይቻላል።

### 3.5.12. ማጠቃለያ

የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ማሳወቅን ከሚያስከትሉ ዋነኛ ስጋቶች አንዱ አምራቾች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ትክክለኛ ባልሆነ ምድብ ውስጥ በማስገባት ዝቅተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን እንዲይዙ ማድረጋቸው ነው።

በዚህ ረገድ ስጋቱ ለአልኮል መጠጦች ከፍ ያለ ነው፤ ምክንያቱም በዚያ ምድብ ውስጥ ያሉ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በቁጥር በርከት ያሉ የተለያዩ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን ያላቸው በመሆኑ ነው።

በተጨማሪም አንዳንድ አልኮል አልባ መጠጦች ከኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ለመውጣት በተሳሳተ መንገድ ሊመደቡ ይችላሉ።

## ክፍል 3.6. ጥሬ ዕቃዎች

### 3.6.1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ በዋጋ መቶኛ የታክስ መዋቅር ላይ የተመሠረተ ቢሆንም (ታክሱ የሚሰላው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ምርት የዋጋው መቶኛ ላይ ተመስርቶ ነው)፣ በወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ዘዴ እያንዳንዱ ብራንድ/የዕቃዎች ዓይነት ለእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ተመሳሳይ ዋጋ አለው።

በመሆኑም ከተፈቀደላቸው ፋብሪካዎች የሚደረጉ ሽያጮች እና የሚወጡ ዕቃዎች ከማምረት ሂደቱ ጋር የተያያዘ የግንኙነት መስመር ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ክፍል የተገዙ እና ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችን ዓይነት፣ አመጣጥ እና መጠን የማረጋገጥ ዝርዝር ጉዳዮችን ይመለከታል።

ለአጠቃላይ መረጃ እና በሕግ ስለተሰጡ ስልጣኖች የኤክሳይዝ ታክስ የኦፊሰር ማኑዋሉን መመልከት ያስፈልጋል።

### 3.6.2. የገቢ ስጋቶች

የተፈቀደላቸው አምራቾች የጥሬ ዕቃ አጠቃቀማቸውን አሳንሰው ካስታወቁ የሚመረቱትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መጠንም አሳንሰው ያስታውቃሉ። ይህን ተከትሎም የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ ይኖራል።

በተጨማሪም አንድ አምራች ከፍተኛ መጠን ያላቸው ጥሬ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረቱ ወይም የተገኙ እንደሆኑ ሊገልፅ ይችላል። ነገር ግን በዚህ መልክ ለቀረበ መግለጫ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

### 3.6.3. መዝገቦች

ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች በተመለከተ መዝገቦችን የመያዝ በሕግ የተቀመጠ ግዴታ አለባቸው።

ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎች መጠን ከእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ከሚጠበቀው የምርት ውጤት ጋር እኩል ሊሆን ይገባል።

በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች (LRM) በማምረታቸው ምክንያት ቅናሽ የተደረገበትን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን የሚከፍሉ የተፈቀደላቸው አምራቾችን በሚመለከቱ ጊዜ የሚከተሉትን መያዝ አለባቸው፡-

- የተረከቧቸውን እና ጥቅም ላይ የዋሉትን ሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች የሚያሳዩ መዝገቦች፤
- ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቧቸውን ሁሉንም ዕቃዎች የሚያሳዩ መዝገቦች፤
- ጥሬ ዕቃዎችን ከአቅራቢዎች የተቀበሉ መሆናቸውን የሚያሳዩ የማስረከቢያ ሰነዶች ቅጂዎች፤
- የጥሬ ዕቃውን የስሪት ሀገር የሚያሳዩ ከአቅራቢዎች የተቀበሏቸው ደረሰኞች ቅጂዎች።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቢሮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ግብር ከፋዩ እነዚህ ዝርዝር መረጃዎች ከሌሉት፣ ቅናሽ ለተደረገበት መጣኔ ማመልከት አይችልም፡፡ በመሆኑም በቢራ እና ወይን ላይ የተጣለውን መደበኛ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት፡፡

### 3.6.4. የሚያስፈልጉ መረጃዎች መረጃዎች

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደላቸው ሁሉም አምራቾች በየወሩ የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፡-

- ማስታወቂያ ቅጽ፣ እና
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ(Stock Invontory form)፡፡

እነዚህ ሰነዶች አምራቾቹ የተረከቧቸውን እና ጥቅም ላይ የዋሉትን ጥሬ ዕቃዎች የተመለከቱ መረጃዎችን ያካትታሉ፡፡

የማስታወቂያ ቅጹ በጥሬ ዕቃዎች (እንደ የትምባሆ ቅጠል፣ ስኳር እና ኤቲል አልኮሆል ያሉ) ላይ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር መረጃዎችን ጭምር ይይዛል፡፡

- የማስታወቂያ ቅጹ በተመረተው ምርት መጠን ላይ መረጃን የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ከተመረተው የመጨረሻ ምርት ከዕቃ ቆጠራ ቅጽ(Stock Invontory form) ላይ ከሚታየው መጠን ጋር ሊታረቅ ይገባል፡፡

በተጨማሪም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ምርቶችን በተመለከተ የጉምሩክ መረጃን ማጣራት ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባት እንቅስቃሴው ጋር የተያያዘ ተጨማሪ ማስረጃን ይሰጣል፡፡

### 3.6.5. መረጃውን መሰብሰብ

አምራቾች ጥሬዕቃዎችን በሚከተሉት መንገዶች ሊያገኙ ይችላሉ፡-

- በቀጥታ ከውጭ በማስገባት፣
- በቀጥታ በኢትዮጵያ ውስጥ የበቀሉ ወይም የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎችን ከሚያቀርብ ኢትዮጵያዊ አቅራቢ፣ ወይም
- ኢትዮጵያ ውስጥ ከውጭ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን ከሚያቀርብ አቅራቢ፡፡

ጥሬ ዕቃዎች ከአገር ውስጥ አቅራቢ የተገኙ በሚሆንበት ጊዜ የአቅራቢውን የገቢ ንግድ ታሪክ ላይ ግምገማዎችን ማካሄድም አስፈላጊ ነው፡፡

የኤክሳይስ ኦፊሰሩ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የጥሬ ዕቃ ምንጮችን ከሚያገኝባቸው መረጃዎች ውስጥ የሚከተሉት የመረጃ ምንጮች ናቸው፡

#### 1. የማስታወቂያ ቅጽ

የማስታወቂያ ቅጹ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች በተመለከተ መረጃን ይይዛል፡፡ ተመላሽ ለማይፈቀድላቸው ጥሬ ዕቃዎች ለምሳሌ ትምባሆ፣ አልኮል እና ስኳር በስተቀር



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቢሮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ማናቸውም ተመላሽ የሚፈቀድላቸው ጥሬ ዕቃዎች ግዥ መረጃ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ጥሬ ዕቃዎች መጠን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊውል የሚገባ ነው፡-

የማስታወቂያ ቅጹ ጥቅም ላይ ከዋሉት ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱ በወሩ የተሸጡትን የሽያጭ መጠን በተመለከተ መረጃዎችን ይይዛል፡፡

### 2. የጉምሩክ መረጃ

በአምራቹ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን ጥሬ ዕቃዎች ለመከታተል ከጉምሩክ ሲስተም መረጃን ይጠይቁ፡፡ እያንዳንዱን ጥሬ ዕቃ እና የሸቀጥ ኮዱን ዝርዝር በማዘጋጀት እና የእያንዳንዱን ዓይነት ጥሬ ዕቃ መጠን ለመከታተል ያግዛል፡፡

### 3.6.6. መረጃውን መተንተን

ለዚህ ሂደት በተለያዩ የምርት ሂደቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን እያንዳንዳቸውን የጥሬ ዕቃ ዓይነቶች መለየት እና የተገዛው መጠን፣ ጥቅም ላይ የዋለው መጠን፣ እንዲሁም የተመረተው ምርት መጠን ላይ የመረጃ ትንተና ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡

አንዳንድ ጥሬ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ ያሚጣልባቸው ሲሆን ይህም ሌላ የማስታረቂያ እድል ይሰጣል፤ ነገር ግን እንደ እርሾ፣ የጌሾ እንክብሎች፣ የሲጋራ ማጣሪያዎች እና ወረቀት፣ የካርቶን ማሸጊያ፣ ቆርቆሮ፣ ጠርሙሶች፣ ቆርኪዎች እና መለያዎች ያሉ ጥሬ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ አይጣልባቸውም ነገር ግን መዝገቦች መያዝ አለባቸው፡፡

ሆኖም ግን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደለት አምራች የተቀበለውን እና ጥቅም ላይ የዋሉትን ሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች መዝግቦ እንዲይዝ በሕግ ይገደዳል፡፡

ከዚህ ክፍል ጋር የተገናኘው በኤክሴል ሠንጠረዥ ውስጥ የተተነተነው ዳታ በታክስ ከፋዩ የተያዘውን መረጃ ለማጣራት በቂ መረጃ ይሰጣል፡፡

ግብር ከፋዮች ለእያንዳንዱ የምርት ዓይነት፣ የመያዣ መጠን እና ዓይነት የምርት ኮድ በመስጠት እያንዳንዱን ምርት ይለያሉ፡፡ እንዲሁም ለገዙት እና ለሚያከማቹት ለእያንዳንዱ ዓይነት የምርት ኮድ እና ማስተር ዳታ ይመድባሉ፡፡

ይህ በመነሻነት የሚከናወነው የመረጃ አሰባሰብ ዓላማ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚውለውን ዋጋ ለመሞገት የሚያስችል ማነፃፀሪያ ማቅረብ ነው፡፡

የተነተኑትን መረጃ እና ግኝቶቹን የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ኢንስፔክሽኑ ለእያንዳንዱ ዓይነት ምርት እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ጥቅም ላይ የሚውለውን ጥሬ ዕቃ መጠኑን እና ዓይነቱን በማጣራት ላይ ያተኩራል፡፡

### 3.6.7. ስለታሰበው ጉብኝት እና የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባ ለግብር ከፋዩ ማሳወቅ



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ግብር ከፋዩ ከኢንስፔክሽን በፊት አስቀድሞ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን እና ሁኔታዎችን አመቻችተው እንዲጠብቁ ከሚታሰበው ኢንስፕፔክሽን ቀን ቀደም ብሎ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ኢንስፔክሽን የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባን በተመለከተ ከላይ የተተነተነውን መረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት የቀረቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል የሚደረጉ ማጣራቶች ላይ ያተኩሩ፡፡ ለምሳሌ፡-

- የእያንዳንዱን ዓይነት ጥሬ ዕቃ መጠን እና ዓይነት ማረጋገጥ
- የጥሬ ዕቃዎቹን ምንጭ ወይም የስሪት ሀገር ማረጋገጥ
- የሚመረቱትን የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መጠን ማረጋገጥ
- የአምራቹን የአስመጭነት ታሪክ ማጣራት
- የአቅራቢዎች ዝርዝር የሚገኝ ከሆነ ቁልፍ የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎችን የአስመጭነት ታሪክ ያጣሩ፡፡

በተጨማሪም የቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው የሚከተሉትን መረጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

- በምርመራው ቅልጥፍና ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የግብር ከፋዩ የታክስ ሕግ ተገዥነት ታሪክ እና ሌሎች የሚታወቁ የስጋት ምክንያቶች (ጥበቃና ደህንነትን ጨምሮ)፤
- የታክስ ማስከፈያ ነጥብ፣ የምርት ዓይነቶችን እና የጣጣመ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳደብ ሥርዓት (HS codes) ግንዛቤ፤
- ያለፈው የኢንስፔክሽን ውጤቶች በተለይም በገቢዎች ሚኒስቴር የተጠየቁ የታክስ ህግ ተገዥነት ማሻሻያ ርምጃዎች፤
- በግብር ከፋዩ ፈቃድ ውስጥ የተቀመጡትን ሁኔታዎች ማወቅ፡፡

### 3.6.8. የቁጥጥር እቅድ

በቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው ወቅት ለመሥራት ስምምነት ላይ ከደረሱባቸው ተግባራት ጋር በሚጣጣም መልኩ የኢንስፔክሽን እቅዱን በማርቀቅ በተገቢው የሥራ ኃላፊ ፀድቆ እንዲፈረም ይቀርባል፡፡

ምርመራውን ለማጠናቀቅ የሚወስደውን ያህል ጊዜ የተፈቀደላቸውን የማምረቻ ቦታዎች እንደገና ለመጎብኘት መጠባበቂያ መጥቀስዎን ያረጋግጡ፡፡ ቁጥጥሩን በአንድ ቀን ሳይገድቡት ቢያንስ አንድ ቀን ቢበዛ ሦስት ቀን እንደሚወስድ ይጥቀሱ፡፡ ሌላ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ከሆነ ከቅርብ ኃላፊው ጋር በመነጋገር ተጨማሪ ጊዜ እንዲፈቀድ ማድረግ ይቻላል፡፡ የተጨማሪው ጊዜ ሲፈቀድ የቅርብ ኃላፊው የፈቀደ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ በፋይል ውስጥ መያዝ አለበት፡፡

### 3.6.9. የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም ላይ የሚጣል ዝቅተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጫኔ አጠቃቀም



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነዶች መዝገብና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በቢራ ወይም ወይን ፋብሪካ ሲገኙ የሚከተሉትን ያድርጉ፡-

- የሁሉንም የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ያዘጋጁ፤
- የጥሬ ዕቃዎችን የማስረከቢያ ሰነዶች (በ3 ወራት ጊዜ ውስጥ የተከናወኑ ሁሉንም የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ርክክቦች) ናሙና ይገምግሙ፤
- አቅራቢውን እንዲሁም የጥሬ ዕቃዎችን ዓይነት እና ብዛት በማስታወሻ ይያዙ፤
- ጥሬ ዕቃዎቹ በእርግጥም በኢትዮጵያ ውስጥ ስለመመረታቸው የሚያሳዩ ማስረጃው እንዲያቀርቡ ማድረግ
- በእያንዳንዱ የማስረከቢያ ሰነድ ላይ ያሉትን መጠኖች እና የተረከቡበትን ቀን በጥሬ ዕቃ መቀበያ መዝገብ ውስጥ ከሚገኙት ዝርዝር መረጃዎች ጋር ማመሳከር፡፡

በተመረጠው ጊዜ ውስጥ ወደ ማምረቻው የገቡት የሁሉም ጥሬ ዕቃዎች መረጃ ሲኖርዎ በጥሬ ዕቃዎቹ የተመረቱትን ዕቃዎች ዓይነት በመለየት እና ትክክለኛው የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ መጠን በምርት አዘገጃጀቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ማጣራት፡፡

በቢራ ፋብሪካው / ወይን ፋብሪካው ውስጥ እንዳሉ ማስታወሻ ይያዙ ወይም የሁሉንም ሰነዶች ቅጂ ወደ ቢሮ ይውሰዱ፡፡ እንዲሁም ሁሉንም የተወሰዱ መዝገቦች የሚገልጽ መተማመኛ ቅፅ ለግብር ከፋዩ መሰጠቱን ያረጋግጡ፡፡

ልዩነቶች ካሉ ወይም መዝገቦቹ ከሌሉ ይህ በሪፖርትዎ ውስጥ መገለጽ ያለበት ሲሆን ይህም ለቅጣት እርምጃ ወደ ክፍል ኃላፊዎ መቅረብ አለበት፡፡

ለመተማመኛ ቅጽ አጠቃቀም በክፍል 4 ውስጥ ያሉትን የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ይጠቀሙ፡፡

### 3.6.10. የሚያስፈልጉ መረጃዎች

ጥሬ ዕቃዎችን የተመለከቱ መረጃዎች የሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ ይገኛሉ፡-

- ከዚህ ቀደም የተከናወኑ ኦዲቶች / ኢንስፔክሽኖች፤
- የመጨረሻው የዕቃ ቆጠራ፤
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ (Inventory form)፤
- ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ፡- የኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት (ECMS) መረጃ፤
- የጠፉ ጥሬ ዕቃዎች ብዛት (ከዕቃ ቆጠራ ቅፅ)፡፡

ከዚህ ምርመራ ጋር የተገናኘ ሁሉንም አስፈላጊ ዳታ በኤክሴል ሰንጠረዥ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ የተጠበቀ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ከትንተናው በመነሳት የሚከተሉትን የመሳሰሉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መለየት፡-

- ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ጥሬ ዕቃዎች ከሌሉየሀገር ውስጥ የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎችን ዝርዝር ያግኙ(ለቢራ እና ለወይን)፡፡
- በተጨባጭ የተገኘው የምርት ውጤት ከሚጠበቀው የምርት መጠን ውጪ ነው፡፡
- **የተመዘገበው ኪሳራ ከፍተኛ ነው፡፡**

3.6.11. የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን አላማዎች

**ዓላማዎች**

| ዓላማ | ማረጋገጫ |
|---|---|
| በክምችት ቆጠራ ፎርም ላይ የተገለፀው የጥሬ ዕቃ መጠን ትክክል ነው፡፡ | የማስረከቢያ ሰነዶችን እና የተረከቡትን መጠን ያረጋግጡ፡፡<br>እንዲሁም በጉምሩክ ሲስተም (ECMS) እና የኢምፖርት ሰነዶች ላይ ያለውን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገቢያ መረጃ ያረጋግጡ፡፡ |
| ዝቅተኛ የኤክሳይስ መጠን በሚተገበርበት ጊዜ፣ የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች ብዛት የተረጋገጠ ነው | የሀገር ውስጥ አቅራቢዎችን ያጣሩ እና እነዚያ አቅራቢዎች ጥሬ ዕቃውን ከየት እንደሚያገኙት ያረጋግጡ፡፡<br>በጥሬ ዕቃው ላይ ያለውን ማሸጊያ በአካል ይፈትሹ፡፡ |
| ኪሳራዎች/ የጠፉ ወይም የተበላሹ ዕቃዎች | ለዋና ጥሬ ዕቃዎች የተመዘገቡትን ኪሳራዎች ያረጋግጡ (ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተዘርዝረዋል)፡፡ |
| የተያዙ እና ጥቅም ላይ የዋሉ የኤክስፖርት መለያዎች ከትክክለኛው ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች ጋር መጣጣም እንደሚችሉ ያረጋግጡ፡፡ | በቆጠራው መክፈቻ እና መዝጊያ ላይ ወደ ውጭ የሚላኩ መለያዎችን መጠን ያረጋግጡ፡፡ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደንክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1


የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቁ.1 መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

## ክፍል 3.7: ከጥሬ ዕቃ የሚጠበቅ ምርት ወይም ያለቀሉት ምርት ኢንስፔክሽን

### 3.7.1. መግቢያ

የጥሬ ዕቃዎችን መግኛ ወይም የስሪት ሀገር ከማጣራት በተጨማሪ የተገለፀው ምርት የተወሰነ መጠን ካላቸው ዋነኛ ጥሬ ዕቃዎች ይመረታሉ ተብለው ከሚጠበቁ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች መጠን ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

ይህ ክፍል ከተገለፀው ምርት አንፃር ጥቅም ላይ የዋለውን ጥሬ ዕቃ መጠን ለማረጋገጥ የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን በሚካሄድበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን እና የአሠራር ሂደቶችን የማረጋገጫ ዝርዝር ያቀርባል።

ለአጠቃላይ መረጃ እና በሕግ ስለተሰጡ ስልጣኖች የኤክሳይዝ ታክስ የኦፊሰር ማኑዋሉን ይመልከቱ።

### 3.7.2. የገቢ ሰጋቶች

የተፈቀደላቸው አምራቾች የጥሬ ዕቃ አጠቃቀማቸውን አሳንሰው ካስታወቁ የሚመረቱትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መጠንም አሳንሰው ያስታውቃሉ። ይህን ተከትሎም የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ ይኖራል።

ዋናው ጉዳይ አምራቹ ከጥሬ ዕቃ ግዥና አጠቃቀም ጋር ሊጣጣም የማይችል የምርት እና የሽያጭ / የክምችት አሃዝን አለማስታወቁን ማረጋገጥ ነው።

### 3.7.3. መዝገቦች

ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች በተመለከተ መዝገቦችን የመያዝ በሕግ የተቀመጠ ግዴታ አለባቸው።

ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎች መጠን ከእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ከሚጠበቀው የምርት ውጤት ጋር እኩል ሊሆን ይገባል።

ከሚጠበቀው ምርት ጋር በተያያዘ የኢንዱስትሪ ደረጃዎች ያሉ ሲሆን ይህም በእያንዳንዱ ምርት ላይ በምርት ዓይነት በኤክሳይስ ታክስ የኦፊሰሩ ማንዋል ውስጥ ይበልጥ በዝርዝር ተገልጿል።

ይህ ክፍል በእያንዳንዱ ምርት የሚጠበቀውን የምርት ውጤት መጠን በመውሰድ በዕቃ ቆጠራ እና በማስታወቂያ ቅጽ ላይ የተገለፀው የምርት መጠን ከሚጠበቀው የምርት ውጤት አንፃር ሲተነተን ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስታረቂያ እና የመረጃ ትንተና ያቀርባል።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ያክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደላቸውን አምራቾች በምንመለከትበት ጊዜ በየወሩ በአምራቹ የሚቀርቡ መረጃዎች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህንም ከሚከተሉት ሰነዶች ማግኘት እንችላለን፡-

- የማስታወቂያ ቅጽ፤ እና
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ (Stock Invontory form)።

የተመረተው ብዛት ለተገቢው ምርት ከተመደበው መጠን ጋር የሚመጣጠን መሆኑን ለማወቅ የቀረበውን መረጃ መተንተን ያስፈልገናል።

ከዚህ በማስከተልም የጥሬ ዕቃዎቹ መረጃ እና ምርቱ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የጉብኝት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት ይኖርብናል።

### 3.7.4. የሚያስፈልጉ መረጃዎች

ሁሉም የተፈቀደላቸው አምራቾች በየወሩ የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፡-
- የማስታወቂያ ቅጽ፤ እና
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ።

እነዚህ ሰነዶች አምራቾቹ የተረከቧቸውን እና ጥቅም ላይ የዋሉትን ጥሬ ዕቃዎች የተመለከቱ መረጃዎችን ያካትታሉ።

የማስታወቂያ ቅጹ በጥሬ ዕቃዎች (እንደ የትምባሆ ቅጠል፣ ስኳር እና ኤቲል አልኮሆል ያሉ) ላይ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር መረጃዎችን ይይዛል።

የማስታወቂያ ቅጹ በተመረተው ምርት መጠን ላይ መረጃን የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ከተመረተው የመጨረሻ ምርት ብዛት ጋር ሊታረቅ ይችላል።

### 3.7.5. መረጃውን መሰብሰብ

**የማስታወቂያ ቅጽ**

የማስታወቂያ ቅጹ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና የምርት ደረጃዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን ይይዛል።

አብዛኛዎቹ ጥሬ ዕቃዎች (ለቢራ የሚውል የገብስ ብቅልን የመሳሰሉት) የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልባቸውም። ስለዚህ የምርት መጠኑን ከጥሬ ዕቃዎች አንፃር ለማጣራት በአምራቹ የማምረቻ ቦታ ያሉ መረጃዎች ላይ እንመሰረታለን።

የማስታወቂያ ቅጹ ጥቅም ላይ ከዋሉት ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱትን የተጠናቀቁ ምርቶችን የተመለከቱ መረጃዎችንም ያካትታል።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነዶች መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

**የዕቃ ቆጠራ ቅጽ**

የዕቃ ቆጠራ ቅጹ ሊተነተኑ የሚችሉ በርከት ያሉ መረጃዎችን ይይዛል።

ምንም እንኳ ቅጹ በወረቀት ቅጂ (hard copy) ቢቀርብም ተገቢውን መረጃ ለመተንተን እና የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዩ የቀረበውን መረጃ እንዲያረጋግጥ ለመሞገት እንዲቻል መረጃውን ወደ ኤክሴል ሠንጠረዥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

ከተወሰነ የጥሬ ዕቃ መጠን የሚገኘው ምርት ከክምችት እና ከሽያጭ ጋር የሚታረቅ መሆን አለበት።
ለምሳሌ፦ በወሩ መጀመሪያ ያለ ያለቀለት ምርት መጠን ሲደመር በወሩ የተመረተ የምርት መጠን ሲቀነስ በወሩ የተሸጠ የምርት መጠን ከመጨረሻው የምርት መጠን ጋር እኩል መሆኑን ማመሳከር ያስፈልጋል። ለዚህም መረጃ የሚሆነን የሽያጭ መጠን ከማስታወቅ ቅጽ እና ሌሎችን ከኢንቨንተሪ ማስታወቂያ ቅጽ በመውሰድ ማመሳከር ይቻላል።

### 3.7.6. መረጃውን መተንተን

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥቅም ላይ የሚውሉት ጥሬ ዕቃዎች መገኛ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ፣ የዚህ ኢንስፔክሽን ትኩረት የምርቱ መጠን ለምርቱ ከዋሉት ጥሬ ዕቃዎች መጠን ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

በዚህም መሠረት ትክክለኛዎቹ የምርት ደረጃዎች መመርመር አለባቸው።

ስለዚህ የመረጃ ትንተናው ትኩረት የሚከተሉት የኦዲት ፍሰት መከታተያዎች ላይ ይሆናል፦

- ወደ ፋብሪካው የገቡ ጥሬ ዕቃዎች፣
- ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎች፣
- የተመረተ ምርት (ከመታሸጉ በፊት)፣
- የታሸጉ ምርቶች ብዛት፣
- በፋብሪካው ግቢ ውስጥ ያለቀለት ምርት መጋዘን የገባ
- ከፋብሪካው መጋዘን በሽያጭ የወጣ ብዛት
- በማምረቻው መጋዘን ተገቢ ወደ ሆኑ የድርጅቱ ማከማቻ ቦታዎችበዲሊቨሪ ኖት የወጡ ምርቶች ብዛት።

ከፋብሪካ የሚወጡ ዕቃዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በዕቃ አወጣጥ ኢንስፔክሽን ውስጥ ተገልፀዋል።

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደለት አምራች የተረከባቸውን እና የተጠቀማቸውን ሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች በተመለከተ መዝገቦችን የመያዝ በሕግ የተቀመጠ ግዴታ አለበት።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ከዚህ ክፍል ጋር የተገናኘው በኤክሴል ሠንጠረዥ ውስጥ የተተነተነው ዳታ በታክስ ከፋዩ የተያዘውን መረጃ ለማጣራት በቂ መረጃ ይሰጣል።

ግብር ከፋዮች ለእያንዳንዱ የምርት ዓይነት፣ የመያዣ መጠን እና ዓይነት የምርት ኮድ በመስጠት እያንዳንዱን ምርት ይለያሉ። እንዲሁም ለገዙት እና ለሚያከማቹት ለእያንዳንዱ ዓይነት የምርት ኮድ እና ማስተር ዳታ ይመድባሉ።

በማምረቻ ቦታው ውስጥ በሚሆኑ ጊዜ፣ ከተመረቱ ምርቶች የምርት ኮዶች ጥቅም ላይ እስከዋሉት ጥሬ ዕቃዎች የተመለከቱ መረጃዎችን በመገንባ አያያዝ ሥርዓቱ ውስጥ ይመልከቱ።

ይህ በመነሻነት የሚከናወነው የመረጃ አሰባሰብ ዓላማ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚውለውን ዋጋ ለመሞገት የሚያስችል ማነፃፀሪያ ማቅረብ ነው።

የተነተኑትን መረጃ እና ግኝቶቹን የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

### 3.7.7 የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች

በምዕራፍ 4 ላይ ያለውን የሥራ ማከናወኛ ሰነድ በመጠቀም በቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው ወቅት ለመሥራት ስምምነት ላይ ከደረሱባቸው ተግባራት ጋር በሚጣጣም መልኩ የኢንስፔክሽን እቅዱን በማርቀቅ በተገቢው የሥራ ኃላፊ ፀድቆ እንዲፈረም ያቅርቡ።

ምርመራውን ለማጠናቀቅ የሚወስደውን ያህል ጊዜ የተፈቀደላቸውን የማምረቻ ቦታዎች እንደገና ለመጎብኘት መጠባበቂያ መጥቀስዎን ያረጋግጡ። ቁጥጥሩን በአንድ ቀን ሳይገድቡት ቢያንስ አንድ ቀን (ቢበዛ ሦስት ቀን) እንደሚወስድ ይጥቀሱ። ሌላ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ከሆነ ከቅርብ ኃላፊው ጋር በመነጋገር ተጨማሪ ጊዜ እንዲፈቀድ ማድረግ ይቻላል። የተጨማሪው ጊዜ ሲፈቀድ የቅርብ ኃላፊው የፈቀደ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ በፋይል ውስጥ መያዝ አለበት።

### 3.7.8. በኢንስፔክሽኑ ወቅት

ሁሉንም የሚመለከታቸውን የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በማነጋገር፣ አጠቃላይ መረጃውን ወቅታዊ ከተደረገ እና የማምረቻ ቦታውን ተዘዋውረው ከጎበኙ በኋላ የጥሬ ዕቃዎችን አጠቃቀም እስከ መጨረሻ ምርቶች ድረስ እንዴት መከታተል እንደሚቻል መረዳትዎን ያረጋግጡ።

በታክስ ከፋዩ የሚያዙ ዋነኛ መዝገቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ያክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- ጥሬ ዕቃዎች የታዘዙባቸው ማዘጋጆች፣
- የጥሬ ዕቃዎች ርክክብ የተፈፀመባቸው የማስረከቢያ ሰነዶች / ወደ ሀገር ውስጥ ማስገቢያ ሰነዶች፣
- ወደ ምርት የገቡ ጥሬ ዕቃዎች፣
- የምርት ስብስብ ዙሮች/ባቾች፣
- ከመታሸጉ በፊት በማጠራቀሚያ ያለ የምርት መጠን (Bulk production)፣
- የማሸጊያ ሥራዎች፣
- ከማሸጊያ መስመር ወደ ማከማቻ ቦታ የተደረገ ዝውውር።

ልዩነቶች ካሉ ወይም መዝገቦቹ ከሌሉ ይህ በሪፖርትዎ ውስጥ መገለፅ ያለበት ሲሆን የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድም ለክፍል ኃላፊዎ መተላለፍ አለበት።

በምዕራፍ 4 ውስጥ ባለው በሚመለከተው የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ላይ ማስታወሻ ይያዙ።

### 3.7.9. ማረጋገጫ የሚካሄድባቸው መዝገቦች

የሚከተሉት መዝገቦች በአምራቹ የሚያዙ ሲሆን ተገቢውን ማመሳከር ለማካሄድ ያስችላሉ፡-

- በመጀመሪያ ለሁሉም የተገዙ ጥሬ ዕቃዎች ግዢ የተዘጋጀ የግዢ ማዘዣ ሰነድ ይኖራል።
- ጥሬ ዕቃዎቹ ወደ ማምረቻው ቦታ በሚገቡ ጊዜ የማስረከቢያ ሰነዱ የግዢ ማዘዣ ቁጥሩን ይይዛል፤ ስለዚህም የታዘዘውን እና በተጨባጭ ገቢ የተደረገውን መጠንና አይነት ማመሳከር ይገባል።
- ጥሬ ዕቃዎች የማምረቻ ቦታው እንደደረሱ፣ ርክክብ ከመፈፀሙ እና ዕቃዎቹ በተገቢው የጥሬ ዕቃ ማከማቻ ቦታ ውስጥ እንዲከማቹ ከመደረጋቸው በፊት መጠናቸው በበመዘን መረጋገጡን የሚያሳይ ሰነድ ከገቢ ደረሰኝ ጋር ማያያዙን ማረጋገጥ፣
- ሁሉም የምርት ስብስቦች (Production Bach) ለሚጠበቀው የምርት መጠን እና ክጥሬ ዕቃ ማከማቻ ወደ ምርት ለገቡ ጥሬ ዕቃዎች መጠን የሚሰጥ የምርት ስብስብ ቁጥር(Production Bach)ይኖራቸዋል።
- ይህ የምርት ስብስብ ቁጥሮች ለሁሉም ብራንዶች እና የኤክሳይዝ ታክስ ለሚከፈልባቸው ሁሉም ዓይነት ምርቶች ይገኛል።
- ለፈሳሽ ምርቶች የማምረት ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ከመታሸጉ በፊት ያለው የምርቱ ልኬት ተወስዶ ይመዘገባል።
- በየዙሩ የሚከናወነው የእያንዳንዱ ማሸጊያ ሂደት ቀን እና ሰዓት ይመዘገባል።
- ከመታሸጉ በፊት በማጠራቀሚያ ያለ የምርት መጠን ወደ ማሸጊያዎች ከተሞሉ በኃላ ያላቸው መጠን/ብዛት ይመዘገባል።
- ዕቃዎቹ ወደ ማከማቻ ቦታው ሲገቡ ቀን፣ ሰዓት፣ የምርት ኮድ እና መጠንን የሚያሳይ መዝገብ ይኖራል።

### 3.7.10. ከጥሬ ዕቃዎች የሚጠበቅ የምርት መጠን/ገደብ



የሚከተለው ሠንጠረዥ በዓለም አቀፍ ደረጃ በማምረቻ ቦታዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ማጠቃለያ ያቀርባል። በተለይም በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ በሁሉም ደረጃ ላይ ባሉ የተለያዩ አምራቾች ላይ ጥናት ተካሂዷል።

ሠንጠረዡ ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎችን የሚያካትት ሲሆን ቢራን ለማምረት በትንሽ መጠን ጥቅም ላይ የሚውሉ እንደ እርሾ እና ጌሾ ያሉ ጥሬ እቃዎች አልተካተቱም። ይሁን እንጂ የሁሉንም ጥሬ ዕቃዎች መጠን መረዳት የአዘገጃጀት ቀመሩን እና ጥቅም ላይ የዋለውን መጠን ለመረዳት አስፈላጊ ነው።

**ከጥሬ ዕቃዎች የሚጠበቅ አማካይ የምርት መጠን/ገደብ**

| የምርት ዓይነት | ጥሬ ዕቃ | የሚጠበቀው የምርት ውጤት | የመጠን ገደብ (Range) |
|---|---|---|---|
| ቢራ (ትልቅ የቢራ ፋብሪካ) | የገብስ ብቅል | በአንድ ኪሎ ግራም 9 ሊትር | ከ6-9.5 ሊትር |
| ቢራ (አነስተኛ የቢራ ፋብሪካ) | የገብስ ብቅል | በአንድ ኪሎ ግራም 6.5 ሊትር | ከ6-8 ሊትር |
| የአልኮል መጠጦች (ከተጣራ ገብስ/ስንዴ) | የገብስ/የስንዴ ብቅል | በአንድ ኪሎ ግራም 1 ሊትር | ከ0.8 እስከ 1.5 ሊትር |
| የአልኮል መጠጦች (ከሌሎች የግብርና ጥሬ ዕቃዎች) | ድንች፣ ሞላሰስ፣ ፍራፍሬ | በ405 የአልኮል ይዘት (abv) 0.4 ሊትር | ከ0.2 እስከ 1 ሊትር |
| ወይን | ወይን/የወይን እሸት | በአንድ ኪሎ ግራም 0.7 ሊትር | 6.8 ሊትር |
| ካርቦን ያላቸው ለስላሳ መጠጦች | ውሃ | በ2 ሊትር ውሃ 1 ሊትር የመጨረሻ ምርት | በአንድ ሊትር ምርት ከ1.2 እስከ 3 ሊትር |
| የማዕድን ውኃ | ውሃ | በ1.4 ሊትር ውሃ 1 ሊትር | በአንድ ሊትር ምርት ከ1.4 እስከ 2 ሊትር |
| ሲጋራ | የተፈበረከ ትምባሆ | በፍሬ 1 ግራም | በአንድ ሲጋራ ከ0.6 እስከ 1 ግራም |

### 3.7.11. መረጃ

ለዚህ ኢንስፔክሽን ዋናው ቁልፍ ጉዳይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችን መጠን ማረጋገጥ ነው።

በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች ሲመረቱ አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ ለሚጣልባቸው ዕቃዎች፣ በተናጠል የተዘጋጀውን የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን ይመልከቱ።

የሚገኙ መረጃዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡-



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 የታ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- በኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት (ECMS) በኩል ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች፤
- በዕቃ ቆጠራ ቅጽ ላይ ያለ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች ብዛት፤
- በዕቃ ቆጠራ ቅጽ ላይ ያለ ምርት።

የመጀመሪያው ማመሳከሪያ በግብር ከፋዩ በሚቀርበው መረጃ ላይ ሊከናወን ይችላል።

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ይለዩ እና እያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ በምርት ወሰን ውስጥ መሆኑን ለማየት ማስታወሻ መያዝ አለበት።

በግብር ከፋዩ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ እና በምርት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዋነኛ ጥሬ ዕቃዎችን የአቅርቦት ሰንሰለት እና የኦዲት ፍሰት መረጃን መከታተል ያስፈልጋል።

ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትን ጥሬ ዕቃዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን ከኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ ሥርዓት ማስታወሻ በመውሰድ እና ተመሳሳይ እንደሆኑ ለማረጋገጥ የማስረከቢያ ሰነዱን የገቡትን ዕቃዎች መጠን መመልከት ይገባል።

እንዲሁም ሁሉንም የሀገር ውስጥ የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎችን ማስታወሻ በመያዝ የተገለፁ አሃዞችን ለማመሳከር ማሸጊያዎችን እና የማስረከቢያ ሰነዶችን ያረጋግጡ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

### 3.8. የብክነት / ብልሽት ኢንስፔክሽን

#### 3.8.1. መግቢያ

የሀገር ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ በኢትዮጵያ ውስጥ ተመርተው ጥቅም ላይ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ፍጆታ ላይ የተመሠረተ ታክስ ነው።

በማንኛውም የፋብሪካ አካባቢ ኪሳራ የሚከሰት ሲሆን በተለመደ ብክነት እስከተከሰተ ወይም በሌላ መልኩ ማብራሪያ ሊቀርብበት እስከቻለ ድረስ በእነዚህ ኪሳራዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል አይኖርበትም።

በማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ የሚያጋጥም ድንገተኛ ኪሳራዎች፣ ለምሳሌ በቢራ ላይ የሚያጋጥሙ የጠርሙሶች መሰባበር ተገቢ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስ የኤክሳይዝ ታክሱ ሊነሳላቸው ይችላል።

በተጨማሪም ዕቃዎች ሲወገዱ አምራቾች ሊከተሉት የሚገባ የተወሰነ ሂደት አለ።

የተወገዱ ወይም ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎች መጠን በወርሃዊ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ ላይ መገለፅ አለበት።

ይህ ኢንስፔክሽን የሚያተኩረው እንደተወገዱ ወይም ከጥቅም ውጪ እንደሆኑ የተገለፁት ዕቃዎች መጠን ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ ላይ ነው።

#### 3.8.2. ስጋቶች

ብክነትን ወይም ውድመትን ከመጠን በላይ ከፍ አርጎ ያስታወቀ ማንኛውም አምራች ዕቃው የጠፋ፣ የተወገደ ወይም ከጥቅም ውጪ እነደሆነ እያሳወቀ ነገር ግን ያንን ዕቃ ወደ ገበያ እያወጣ ሊሆን ይችላል።

ይህም ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ምርቶች ወደ ገበያው እንዲገቡ ያደርጋል።

#### 3.8.3. መዝገቦች

ምንም እንኳን ኪሳራዎች የሥራ እንቅስቃሴዎች ተለምዷዊ ውጤቶች ቢሆኑም ሁሉም አምራቾች መጠኑን ዝቅተኛ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ምንም እንኳን ለኪሳራ የተፈቀደ ገደብ ባይኖርም የሚከተሉት ኪሳራዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፦

- የማሸጊያ ኪሳራዎች፣ እና



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- በማምረቻ ቅጥር ግቢው ውስጥ ዕቃዎቹን በማከማቸት እና
  በማንቀሳቀስ ጊዜ የሚከሰቱ ድንገተኛ ኪሳራዎች።

በተጨማሪም ጥሬ ዕቃዎች ሊበላሹ ወይም ሊወድሙ ይችላሉ (ለምሳሌ አይጦች ወደ ጥሬ ዕቃው ማከማቻ ቦታ ውስጥ ዘልቀው ሊገቡ ይችላሉ) እና የመጨረሻ ምርቶች ሊበላሹ ወይም መሸጥ ባለባቸው ጊዜ ላይሸጡ ይችላሉ።

ማንኛውም አምራች የሚከሰተውን እያንዳንዱን የኪሳራ ዓይነት የተመለከቱ መዝገቦችን እና ማስረጃዎችን መያዙ አስፈላጊ ነው።

### 3.8.4. የሚያስፈልጉ መረጃዎች

ሁሉም የተፈቀደላቸው አምራቾች በየወሩ የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፡-

- የማስታወቂያ ቅጽ፣ እና
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ።

እነዚህ ሰነዶች ወደ ፋብሪካ የገቡ እና ጥቅም ላይ የዋሉትን ጥሬ ዕቃዎች የተመለከቱ መረጃዎችን ያካትታሉ።

የማስታወቂያ ቅጹ በጥሬ ዕቃዎች (እንደ የትምባሆ ቅጠል፣ ስኳር እና ኤቲል አልኮሆል ያሉ) ላይ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር መረጃዎችን ይይዛል።

የማስታወቂያ ቅጹ በተመረተው ምርት መጠን ላይ መረጃን የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ከተመረተው የመጨረሻ ምርት ብዛት ጋር ሊታረቅ ይገባል።

### 3.8.5. መረጃውን መሰብሰብ

**የማስታወቂያ ቅጽ**

የማስታወቂያ ቅጹ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና የምርት ደረጃዎች መረጃን ይይዛል።

አብዛኞቹ ጥሬ ዕቃዎች (ለቢራ የሚውል የገብስ ብቅልን የመሳሰሉት) የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልባቸውም። ስለዚህ የምርት መጠኑን ከጥሬ ዕቃዎች አንፃር ለማጣራት በአምራቹ የማምረቻ ቦታ ያሉ መረጃዎች ላይ እንመሰረታለን።

የማስታወቂያ ቅጹ ጥቅም ላይ ከዋሉት ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱትን የተጠናቀቁ ምርቶችን የተመለከቱ መረጃዎችንም ያካትታል።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ማዕከል ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

**የዕቃ ቆጠራ ቅጽ**

የዕቃ ቆጠራ ቅጹ ወደ ኤክሴል ሠንጠረዥ መግባት ያለባቸውን እና ከጉብኙቱ በፊት ሊተነተኑ የሚገባቸውን በርካታ መረጃዎችን ይይዛል።

### 3.8.6. መረጃውን መተንተን

እያንዳንዳቸው አምራቾች ተመሳሳይ ሂደቶች ቢኖራቸውም ነገር ግን የተለያዩ ቴክኒኮች ሊኖራቸው ይችላል፤ እንዲሁም አንዳንድ መሣሪያዎችም ከሌሎቹ የበለጠ ብቃት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

ስለዚህ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች በመተንተን ምክንያቱም ይህ በዓመቱ ውስጥ ያለውን አዝማሚያ እና አማካይ ብክነት/ኪሳራ ይሰጣል።

ከዚህ ማኑዋል ጋር የተገናኙ በአምራቾች የሚቀርቡ ሁሉም መረጃዎች ያሉባቸው የኤክሴል ሠንጠረዦች ያሉ ሲሆን ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ተገቢውን መረጃ ከአጠቃላይ የኤክሴል ሰንጠረዥ ውስጥ መውጣት የሚቻልባቸው እንዲሁም ለእያንዳንዱ ኢንስፔክሽን ተገቢውን መረጃ መተንተን የሚቻልባቸው የግለሰብ ኤክሴል ሰንጠረዦች ይገኛሉ።

በማምረቻ ቦታው ውስጥ በሚሆኑ ጊዜ፣ ከተመረቱ ምርቶች የምርት ኮዶች ጥቅም ላይ እስከዋሉት ጥሬ ዕቃዎች የተመለከቱ መረጃዎችን በመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱ ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

ይህ በመነሻነት የሚከናወነው የመረጃ አሰባሰብ ዓላማ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚውለውን ዋጋ ለመሞገት የሚያስችል ማነፃፀሪያ ማቅረብ ነው።

የተነተኑትን መረጃ እና ግኝቶቹን የሚያሳይ ሪፖርት ይዘጋጃል።

### 3.8.7. የኢንስፔክሽን እቅድ

በቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው ወቅት ለመሥራት ስምምነት ላይ ከደረሱባቸው ተግባራት ጋር በሚጣጣም መልኩ የኢንስፔክሽን እቅዱን በማርቀቅ በተገቢው የሥራ ኃላፊ ፀድቆ እንዲፈረም ያቅርቡ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 መዛግብትና ይክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የተተነተኑትን ሁሉንም ተዛማጅ መረጃዎች በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ ከሚከናወኑት የማጣራት ሥራዎች ጋር ለመጻፍ በምዕራፍ 4 ውስጥ ያለውን የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ይጠቀሙ።

### 3.8.8. በኢንስፔክሽኑ ወቅት

ሁሉንም የሚመለከታቸውን የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ካነጋገሩ፣ አጠቃላይ መረጃውን ወቅታዊ ካደረጉ እና የማምረቻ ቦታውን ተዘዋውረው ከጎበኙ በኋላ የጥሬ ዕቃዎችን አጠቃቀም እስከ መጨረሻ ምርቶች ድረስ እንዴት መከታተል እንደሚቻል መረዳት ያስፈልጋል።

በታክስ ከፋዩ የሚያዙ ዋነኛ መዝገቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ውድመቶችን በተመለከተ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳወቁበት፤
- እያንዳንዱ የኪሳራ/ብልሽት ዓይነት በሚገለገሉበት የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት ውስጥ ይመዘገባል፤
- ኪሳራዎች የሚያጠቃልሉት፡- የታሸጉ ዕቃዎች ድንገተኛ መሰባበር፣ በማሸግ ወቅት የሚደርስ ኪሳራ፣ በምርቱ ባህሪ/ተፈጥሮ በሆነ ብክነት የሚደርስ ኪሳራ።

ልዩነቶች ካሉ ወይም መዝገቦቹ ከሌሉ ይህ በሪፖርትዎ ውስጥ መገለጽ ያለበት ሲሆን ይህም ለቅጣት እርምጃ ወደ ክፍል ኃላፊዎ መተላለፍ አለበት።

በምዕራፍ 4 ውስጥ ባለው ተገቢው የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ላይ ማስተወሻዎችን ይያዙ።

### 3.8.9. መረጃ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚያጋጥሙ ውድመቶችን በሙሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር ማሳወቅ ይገባል።

ስለዚህም ይህ ኢንስፔክሽን ሁሉም የዕቃዎች ውድመት ወይም አወጋገድ ከቀረበው መረጃ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ላይ የሚያተኩር ነው።

የብክነት እና ውድመት ደረጃዎችን ይፈትሹ እና ከምርት መጠኑ ከ1% (በአለማቀፍ ተሞክሮ) በላይ የሆኑትን ማናቸውንም መጠኖች ይመዝግቡ።

ኪሳራዎች የሚፈቀዱበት የተወሰነ የተቀባይነት መጠን የለም። ነገር ግን፣ ከኢንዱስትሪ የአሠራር ልምድ 1% አማካይ የኪሳራ መጠን ነው።

ይሁን እንጂ አምራቹ ጥቅም ላይ በሚውሉ መሣሪያዎች ምክንያት ወይም በምርት ሂደቱ ያጋጠመን የ1% የኪሳራ መጠን ማብራሪያ ሊቀርብበት እንደሚችል እስካረጋገጠ ድረስ ያንን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ይህን ዓይነቱን ኢንስፔክሽን በአንድ ዓይነት ኢንዱስትሪ ውስጥ ባሉ በርካታ ግብር ከፋዮች ላይ ካደረጉ በኋላ የኢትዮጵያን መደበኛ ሁኔታ በመረዳት በተመሳሳይ ኢንዱስትሪ ውስጥ ካሉ ተመሳሳይ ግብር ከፋዮች ይበልጥ ከፍተኛ የተመዘገበ ኪሳራ ያላቸውን ግብር ከፋዮች መጠየቅ ይችላሉ።

## ክፍል 3.9: ከፋብሪካ የሚወጡ ዕቃዎች ላይ የሚካሄድ ኢንስፔክሽን

### 3.9.1. መግቢያ

ከተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች ዕቃዎች ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ምክንያት ሊወጡ ይችላሉ፡-

- ታክሱ ተከፍሎባቸው የሚወጡ (በሽያጭ የሚወጡ)
- ታክሱ ተከፍሎባቸው የሚወጡ (ሽያጭ ሳይከናወን የሚጡ)
- በእግድ ውስጥ ሆነው የሚወጡ(Duty Suspended Movements)
- ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚወጡ
- በአውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ላሉ ከቀረጥ ነፃ መደብሮች/ለዲፕሎማቲክ ባለመብቶች የሚወጡ

በዚህ ረገድ ገቢ የተደረጉ የማዘዣ ሰነዶች (እና ማምረቻ ወዳልሆኑ የማከማቻ መጋዝኖች የተደረጉ የማጓጓዝ እንቅስቃሴዎች) የማስረከቢያ ሰነዶች፣ ከሀገር ውጭ የመላኪያ ሰነዶች፣ የማስታወቂያ ቅጾች እና ደረሰኞች መኖር አለባቸው።

### 3.9.2. ቅድመ-ኢንስፔክሽን

***የሚያስፈልጉ ማሸረጃዎች***

ሀ. የማስረከቢያ ሰነዶች

ለ. ደረሰኞች

ሐ. የማስታወቂያ ቅጾች

መ.ወደ ውጭ ሀገር የመላኪያ ሰነዶች

***የሚያስፈልጉ መረጃዎች***

ሀ. የሁሉም ሽያጮች መዝገብ

ለ. ታክሱ የተከፈለባቸው ሽያጮች መዝገብ

ሐ. የፈቃድ ቅጂ/ኮፒ

መ.ከማስታወቂያ ቅጹ ጋር የሚዛመዱ የማዘዣ ቅጾች እና ደረሰኞች

ሠ. በእያንዳንዱ የርክክብ ዓይነት የተከፋፈለ የደንበኞች ዝርዝር

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 3.9.3. በኢንስፔክሽኑ ውስጥ የሚጠየቁ ሰነዶች

ሀ. በእያንዳንዱ የዕቃ አወጣጥ ዓይነት የተከፋፈለ የደንበኞች ዝርዝር

ለ. በእያንዳንዱ የሽያጭ ዓይነት የተከፋፈለ የቀን ሽያጭ

ሐ. ከእያንዳንዱ ቀን የዕቃ አወጣጥ ጋር የሚዛመዱ የቀረቡ ትዕዛዞች እና የተሰጡ ደረሰኞች

መ. የኤክስፖርት ማስረጃ

ሠ. ከታክስ ነፃ የሆኑ ደንበኞች ዝርዝር እና ከታክስ ነፃ ለሆኑት ርክክቦች ትክክለኛ የአሠራር ሂደቶችን መከተላቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች

### 3.9.4. የመረጃ ትንተና

በዕቃ አወጣጥ ላይ ከሚደረገው ኢንስፔክሽን አንፃር ልንመረምራቸው የሚገቡን ዋነኛ መረጃዎች የማስታወቂያ ቅጹን፣ የዕቃ ቆጠራ ቅጹን እና ደረሰኞችን (ግብር ከፋዩ ካቀረበ) ነው።

ወደ ውጭ የተላኩ ዕቃዎችን በተመለከተ፣ በጉምሩክ የመረጃ ቋት ላይ ያለውን የኤክስፖርት መረጃ ያረጋግጡ እና ሁሉንም ወደ ውጭ የተላኩ ምርቶች ከቀረቡት ሰነዶች (እና በዕቃ ቆጠራ ቅጹ ላይ ወደ ውጭ እንደሚላክ ከተመዘገበው ከእያንዳንዱ ምርት ብዛት) ጋር ያገናኙ።

ስለዚህ ሦስት ግልጽ ስጋቶች ይኖሩብናል፡-

1. የኤክሳይዝ ታክስ እንደተከፈለባቸው የተገለፁት ሁሉም ከፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች ላይ ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ የተገለፀ እና የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. የኤክሳይዝ ታክሱ ሳይከፈልባቸው ወጪ የተደረጉ ሁሉም ምርቶች ወደ ውጭ መላካቸውን ወይም ወደሚመለከተው ደንበኛ መድረሳቸውን ማረጋገጥ፤
3. ዕቃዎቹን የሚረከበው ሰው ያለ ኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ዕቃዎቹን እንዲረከብ የተፈቀደለት መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ።

### 3.9.5. የመረጃ እና ትንተና ማጠቃለያ

ሀ. የተነተኑትን መረጃ እና ግኝቶቹን የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት፤

ለ. ኢንስፔክሽኑ ከፋብሪካው የሚወጡትን እያንዳንዳቸውን የዕቃ አወጣጥ ዓይነቶች ብዛት በማረጋገጥ ላይ ያተኩራል፤

ሐ. ከእያንዳንዱ ደንበኛ ጋር የሚከናወነውን የትዕዛዝ እና የማስረከብ ድግግሞሽ ልብ ይበሉ። አዲስ ደንበኞችን ወይም ወደ ውጭ የመላክ እንቅስቃሴዎችን ይለዩ።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ቁጥጥር ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

### 3.9.6. በኢንስፔክሽኑ ወቅት

ሀ. ከሚመለከታቸው የግብር ከፋዩ አባላት ጋር በመገናኘት በሥራው ላይ ውይይት ያድርጉ እና ከትንተናዎ የመነጨ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፤ ለምሳሌ፣ በእግድ ውስጥ ሆነው የሚወጡ ወይም ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች መጨመር፤

ለ. ይህን ካላደረጉ፣ ርክክብ በሚደረግበት ጊዜ በአካል በመመልከት በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ ያለው መጠን ከሚረከበው እያንዳንዱ የምርት ዓይነት/ብራንድ መጠን ጋር እንዴት እንደሚታረቅ ያመሳክሩ፤

ሐ. መዝገቦቹ በሙሉ በእጅ የሚያዙ (ማኑዋል) ከሆኑ በሲስተሙ ላይ ያሉትን ተመሳሳይ መዝገቦች ለማየት ይጠይቁ እና በሲስተሙ እና በእጅ በሚያዙት መዝገቦች መካከል ያለውን መስተጋብር ይረዱ፤

መ. አስፈላጊ ሲሆን የቅድመ-ምርመራ ትንታኔዎን ይመልከቱ፤

ሠ. ስልታዊ አካሄድን ይከተሉ፤ ማለትም በየቀኑ ያለውን እንቅስቃሴ ከግልፅ የኦዲት ፍሰት እይታ አንፃር ይመልከቱ። ለምሳሌ፣ ለእያንዳንዱ ርክክብ የሚደረገውን የተለመደ ሂደት ይመልከቱ እና የሚከተሉትን ያረጋግጡ፡-

- የቀረበውን የማዘጋጃ ሰነድ
- ከማከማቻው ቦታው የሚወጡ ዕቃዎችን
- የሚሰጠውን ደረሰኝ
- የእያንዳንዱን ርክክብ/የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ/በእግድ ላይ ያለ የዕቃ አወጣጥ ተገቢውን የማስረከቢያ ሰነድ

ረ. በኢንስፔክሽኑ ወቅት ያረጋገጧቸውን ጉዳዮች እና የተገኙትን ማናቸውም ግኝቶች በማስታወሻ ይያዙ (ይህ በመጨረሻው ሪፖርት ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዲጂታል ምስሎችን በማንሳት ሊደገፍ ይችላል)፤

ሰ. በኢንስፔክሽን እቅዱ ውስጥ የተቀመጡትን ሁሉንም የኢንስፔክሽኑ ዓላማዎች ለማሳካት ጥረት ያድርጉ፤

ሸ. በቀኑ መጨረሻ ላይ ካላጠናቀቁ በቀጣዩ ቀን ይመለሱ፤

ቀ. የግብር ከፋዩ ሠራተኞች ሲስተሙን ለማሳየት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ምንም ዓይነት መዝገብ ሊያቀርቡልዎ ካልቻሉ ይህንን ማስታወሻ በመያዝ ለሚመለከተው ሪፖርት ማድገር ያስፈልጋል፤

በ. የመዝገብ አያያዙን ስታንዳርድ እና መዝገቦቹን አዲት ለማድረግ ምን ያህል ቀላል እንደነበር ማስታወሻ ይያዙ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 3.10. የምርት እና የማሸጊያ ኢንስፔክሽን

#### 3.10.1. መግቢያ

ከመጠን በታች ዝቅ እንዲሉ ተደርገው የሚገለፁ የምርት መረጃዎች የኤክሳይዝ ታክስን አሳንሶ ማስታወቅን ያስከትላሉ።

ይህ ኢንስፔክሽን የመጨረሻው ምርት ከተመረተበት ነጥብ በመነሳት እስከ ማሸጊያ ድረስ ያለውን ሂደት ይሸፍናል።

የምርት ስብስብ/ባች ቁጥሮች በእያንዳንዱ ዙር ከሚሰጡ የማሸጊያ ቁጥሮች ጋር መገናኘት አለባቸው (ይህም በተራው ከጥሬ ዕቃ አጠቃቀም ጋር መልሶ መገናኘት ይኖርበታል)።

የዕቃ ቆጠራ ቅጹን በሚያጣሩበት ጊዜ የአንድ ወር መዝጊያ የቆጠራ መዝገብ ከሚቀጥለው ወር የመክፈቻ የቆጠራ መዝገብ ጋር መላመድ አለበት፤ ተያይዞም የዚያ ወር የመዝጊያ ቆጠራ መዝገብ የተመረቱ ምርቶች መጨመርን ማካተት እና የጠፉ ወይም የወጡ ዕቃዎችን በሙሉ መቀነስ አለበት። ማናቸውም ልዩነቶች ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።

#### 3.10.2. መዝገቦች

መዝገቦች የተመረቱ፣ የተከማቹ እና ወጪ የተደረጉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መጠን ማሳየት በሚችሉበት አግባብ መያዝ አለባቸው።

የተፈቀደላቸውን አምራቾችን በምንመለከትበት ጊዜ በሚከተሉት ሰነዶች በኩል በየወሩ በአምራቹ የሚቀርቡ መረጃዎች ይኖሩናል፦

- የማስታወቂያ ቅጽ፤ እና
- የዕቃ ቆጠራ(stock inventory form) ቅጽ።

ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ ወጪ የተደረገው መጠን ከተመረተው እና ከታሸገው መጠን ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማወቅ የቀረበውን መረጃ መተንተን አለብን።

#### 3.10.3. የሚያስፈልጉ መረጃዎች

በእያንዳንዱ ወር ሁሉም የተፈቀደላቸው አምራቾች የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፦

- የማስታወቂያ ቅጽ፤ እና
- የዕቃ ቆጠራ ቅጽ።

እነዚህ ሰነዶች ከምርት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ያካትታሉ።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቴክ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 3.10.4. መረጃውን መሰብሰብ

**የማስታወቂያ ቅጽ**

ማስታወቂያ ቅጹ ስለምርት፣ ስለተቀመጠ ክምችት እና ከፋብሪካው ወጪ ስለተደረጉ ዕቃዎች መረጃን ይይዛል።

**የዕቃ ቆጠራ ቅጽ (stock inventory form)**

የዕቃ ቆጠራ ቅጹ ሊተነተኑ የሚችሉ በርከት ያሉ መረጃዎችን ይይዛል።

ምንም እንኳ ቅጹ በወረቀት ቅጂ (hard copy) ቢቀርብም ተገቢውን መረጃ ለመተንተን እና የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዩ የቀረበውን መረጃ እንዲያረጋግጥ ለመሞገት እንዲቻል መረጃውን ወደ ኤክሴል ሠንጠረዥ በማስገባት አስፈላጊ ነው።

### 3.10.5. መረጃውን መተንተን

የአንድ ወር የመዝጊያ ቆጠራ መረጃን በመውሰድ የገቡ ዕቃዎች ሲጨመሩ እና ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች እና ውዳቂ ምርቶች ሲቀነሱ በቀጣዩ ወር በመዝጊያ ቆጠራነት ከተገለፀው መጠን ጋራ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያሰፈልጋል ።

### 3.10.6. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች

በምዕራፍ 4 ላይ ያለውን የሥራ ማከናወኛ ሰነድ በመጠቀም በቅድመ-ኢንስፔክሽን ስብሰባው ወቅት ለማከናወን ስምምነት ላይ ከደረሱባቸው ተግባራት ጋር በሚጣጣም መልኩ የኢንስፔክሽን እቅዱን በማርቀቅ በተገቢው የሥራ ኃላፊ ፀድቆ እንዲፈረም ያቅርቡ።

### 3.10.7. በኢንስፔክሽኑ ወቅት

ሁሉንም የሚመለከታቸውን ሠራተኞች ካነጋገሩ፣ አጠቃላይ መረጃውን ወቅታዊ ካደረጉ እና የማምረቻ ቦታውን ተዘዋውረው ከጎበኙ በኋላ የጥሬ ዕቃዎችን አጠቃቀም እስከ መጨረሻ ምርቶች ድረስ እንዴት መከታተል እንደሚቻል መረዳትዎን ያረጋግጡ።

በግብር ከፋዩ የሚያዙ ዋነኛ መዝገቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ጥሬ ዕቃዎች የታዘዙባቸው ማዘዣዎች፣
- የጥሬ ዕቃዎች ርክክብ የተፈፀሙባቸው የማስረከቢያ ሰነዶች / ወደ ሀገር ውስጥ ማስገቢያ ሰነዶች፣
- ወደ ምርት የገቡ ጥሬ ዕቃዎች፣
- የምርት ስብስብ ዙሮች/ባቾች፣
- ከመታሸጉ በፊት በማጠራቀሚያ ያለ ምርት፣
- የታሸጉ ምርቶች ፣
- ከማሸጊያ መስመር ወደ ማከማቻ ቦታ የተደረገ ዝውውር።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ልዩነቶች ካሉ ወይም መዝገቦቹ ከሌሉ ይህ በሪፖርትዎ ውስጥ መገለፅ ያለበት ሲሆን የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድም ለክፍል ኃላፊዎ መተላለፍ አለበት።

በምዕራፍ 4 ውስጥ ባለው በሚመለከተው የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ላይ ማስታወሻ ይያዙ።

### 3.10.8. ማረጋገጫ የሚካሄድባቸው መዝገቦች

የሚከተሉት መዝገቦች በአምራቹ የሚያዙ ሲሆን ተገቢውን ማስታረቅ እንዲያካሂዱ ያስችሉዎታል፡-

- ከማሽኒያው የማጣቀሻ ቁጥር ጋር የሚገናኝ የምርት ስብስብ ቁጥር ይኖራል።
- እያንዳንዱ ብራንድ የተለየ ቁጥር ይኖረዋል።
- የተመረቱበት እና የታሸጉበት ቀኖች ይመዘገባሉ።
- ለፈሳሾች፣ ከማሽኒያው በፊት የነበረውን የሊትሮች ብዛት ከማሽኒያው በኋላ ከሚኖረው የእያንዳንዱ ማሽኒያ ብዛት እና መጠን ጋር የሚያስታርቅ ማመሳከሪያ ይኖራል።
- ኪሳራዎች ወይም የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎች እነዚሁ መዝገቦች ላይ የሚመዘገቡ ይሆናል።

### 3.10.9. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች

ሁሉንም መረጃዎች ለመመዝገብ በምዕራፍ 4 ውስጥ ያሉትን የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ይጠቀሙ።

## 3.11. የመለኪያ እና የመቁጠሪያ መሣሪያዎች

### 3.11.1. መግቢያ

ይህ ኢንስፔክሽን ከምርት / ማሽኒያ ኢንስፔክሽን ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ሊከናወን ይችላል።

የመለኪያ እና የመቁጠሪያ መሣሪያዎች የጥሬ ዕቃዎችን፣ በምርት ሂደት ላይ ያሉ ምርቶችን እና የመጨረሻ ምርቶችን መጠን በትክክል ለመለካት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉት የመለኪያ እና የመቁጠሪያ መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የፍሰት መለኪያ - ቆጣሪዎች፣ እና
- የክብደት መለኪያ - ሚዛኖች።

### 3.11.2. ማስተካከል

የመሣሪያዎችን ትክክለኛ ንባቦች ለማረጋገጥ የመቁጠሪያ ወይም የመለኪያ መሣሪያዎቹ በየጊዜው እንዲመረመሩ እና እንዲስተካከሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዜግ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

መሣሪያዎቹ ቢያንስ በየሦስት ወሩ በትክክል ብቁ በሆነ የሦስተኛ ወገን የመሣሪያ ፍተሻ ድርጅት መስተካከል አለባቸው (አለም አቀፍ ተሞክሮ)።

የመሣሪያ ፍተሻውን ያከናወነው ኩባንያ ያቀረበውን ሪፖርት እና ኩባንያው ለኤክሳይዝ ታክስ ክፋዩ የሰጠውን ደረሰኝ ጨምሮ የተደረጉትን ፍተሻዎች እና ማስተካከያዎች እንዲሁም ማናቸውንም ማሻሻያዎች የተመለከቱ መረጃዎች በመዝገብ መያዝ አለባቸው።

### 3.11.3. ትክክለኛነት

በማምረቻ ግቢው ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎቹን በተግባር ለማየት ይጠይቁ።

ደረቅ ቁሳቁሶች በመደበኛነት ቀድሞ የተለካ ክብደት ባላቸው ከረጢቶች ወይም ጥቅሎች ይረከባሉ። ለምሳሌ 250 ኪሎ ግራም የትንባሆ ጥቅል።

የእነዚህ ከረጢቶች ክብደት መታወቅ ስላለበት የክብደቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አንድ ከረጢት/ጆንያ በሚዛን ላይ እንዲቀመጥ በማድረግ ነዉ ።

በምዕራፍ 4 ውስጥ ባለው የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ላይ ማናቸውንም ልዩነቶች በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ።

### 3.11.4. የመሣሪያዎች የንባብ ድግግሞሽ

ወደ ፋብሪካው የሚገቡ ሁሉም ደረቁ ጥሬ ዕቃዎች በትክክል መለካት አለባቸው። ቀድሞ የተለካ መጠን ያላቸው መያዣዎች በሚደርሱበት ጊዜ የከረጢቶቹ ናሙና መፈተሽ አለበት።

ፈሳሽ ምርቶችን በሚመለከት ለእያንዳንዱ የምርት ስብስብ ዙር የሚመረተውን ምርት ዓይነት እና ስም፣ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችን፣ የሚጠበቀውን ምርት መጠን እና በተጨባጭ የተመረተውን እና የታሸገውን ምርት መጠን የተመለከቱ መረጃዎችን የሚይዝ የማጣቀሻ ቁጥር ይመደባል።

የጥሬ ዕቃዎችን አገባብ በሚመለከተው መዝገብ ላይ የምርት ባች ቁጥር እና የማሸጊያው የዙር ቁጥር መረጃዎች በሙሉ ልኬቱ የተወሰደበትን ሰዓት እና ቀን እንዲሁም የልኬት ንባቡን ያከናወነውን ሰው ጨምሮ የተደረጉትን ልኬቶች በተመለከቱ መረጃዎች የተደገፉ መሆን አለባቸው።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቴሽን ቁ.1 * Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1


የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

### 3.12. ከማሸጊያ እስከ ማከማቻ እንዲሁም የቆጠራ ማመሳከሪያ ኢንስፔክሽን

#### 3.12.1. መግቢያ

ይህ ኢንስፔክሽን በመዝገብ አያያዝ እና በዕቃ ቆጠራ መዝገቦች ላይ ያተኩራል። የዕቃዎቹን ማሸጊያ ከመጨረሻው የማከማቻ ቦታ ጋር የሚያገናኙ ደካማ ወይም ውጤታማ ያልሆኑ መዝገቦች ሲያዙ ስጋት ይኖራል።

ይህ ኢንስፔክሽን የዕቃዎችን የመዝገብ አያያዝ ፍሰት በመፈተሽ ከማምረት እና ከማሸግ (ከላይ በክፍል 3.10 ባለው ኢንስፔክሽን ውስጥ የተገለፀ) እና የመጨረሻዎቹ የታሸጉ ዕቃዎች ወደ ማከማቻ ቦታዎች በሚገቡበት ቀጣዩ የመጨረሻ ደረጃ ምርት መካከል ግልፅ ግንኙነት መኖሩን ያረጋግጣል።

#### 3.12.2. የሚጠበቁ መዝገቦች እና የማከማቻ መስፈርቶች

መስፈርቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ማጣቀሻ ቁጥሮችን በመጠቀም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከማምረቻ እና ማሸጊያ እስከ ማከማቻ ቦታዎች ድረስ የሚኖር ግልፅ የግንኙነት መስመር።
- ዕቃዎቹ በግልፅ ተለይተው በሚታወቁ እና የማከማቻ ቦታ ቁጥሮች በተሰጣቸው የተለዩ ቦታዎች ውስጥ መከማቸት አለባቸው።
- በመዝገቦቹ ውስጥ የምርት ስብስብ/ባች ቁጥሩን፣ ተከታታይ የማሸጊያ ቁጥሩን እና የማከማቻ ቦታዎቹን የሚያገናኝ መስመር መኖር አለበት።

#### 3.12.3. የሚተነተኑ መረጃዎች

በተፈለገው ወር ውስጥ ያለውን (እንዲሁም ከሱ በፊት እና በኋላ ያሉትን ወራት) የክምችት መረጃ ለመተንተን ከዕቃ ቆጠራ ቅጹ እና ከማስታወቂያ ቅጹ መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል ።

ተዛማጅ የሆኑ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶችን እና የኤክሴል ሰንጠረዦን ሞልተው ያጠናቁ።

#### 3.12.4. በቦታው ላይ የሚከናወኑ ተግባራት

በማምረቻ ቦታው ላይ በሚገኙበት ወቅት ምርመራው ለሚካሄድበት ተገቢው ወር አስፈላጊ የሆኑትን ምርቶች እና ማሸጊያዎች ይፈትሹ።

የምርት ስብስብ ቁጥሮችን እና የማሸጊያ ቁጥሮችን ይመርምሩ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ደህንነቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የማከማቻ ቦታዎችን በመፈተሽ እያንዳንዳቸው በግልፅ የተሰጣቸው የተናጠል የቦታ ቁጥር እንዳላቸው ያረጋግጡ።

በክምችት ቦታ ውስጥ ያለ የእያንዳንዱ ብራንድ ብዛት/መጠን ላይ ቆጠራ ያካሂዱ።

ግብር ከፋዩ በክምችት አስተዳደር ሥርዓቱ ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን ብራንድ መጠን እንዲያሳይ ይጠይቁ።

ማናቸውንም ልዩነቶች በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ።

### 3.12.5. ምክረ-ሃሳቦች

ምክረሃ-ሳቦች በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ የማከማቻ ቦታዎችን የበለጠ ግልፅ በማድረግ እና ከምርት እና ማሸጊያ እስከ ማከማቻ እንዲሁም አወጣጥ ድረስ በዕቃዎች ላይ የሚደረግ የክትትል ማስረጃን በማሳደግ ላይ የሚያተኩሩ ትምርቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## 3.13. የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች

### 3.13.1. መግቢያ

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ናቸው።

ይህ በቴሌኮሙኒኬሽን የንግድ ድርጅት የሚሰጡ ሁሉንም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦትን ያካትታል።

እነዚህ የንግድ ሥራዎች በባህሪያቸው የተወሳሰቡ የሶፍትዌር ሲስተሞች ያሏቸው ትልልቅ ንግዶች ይሆናሉ። በመሆኑም የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች፣ የደንበኞችን ክፍያ እንዲሁም የሚሰላው፣ የሚገለፀው እና የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ መጠንን በተመለከተ ግልፅ የሆነ ትስስርን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

### 3.13.2. መረጃ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደላቸው አምራቾች ከሚያቀርቡት መረጃ በተለየ መልኩ የቴሌኮሙኒኬሽን ግብር ከፋዮች የዕቃ ቆጠራ ቅጾችን ወይም የዋጋ ዝርዝሮችን ማቅረብ አያስፈልጋቸውም።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በቴሌኮሙኒኬሽን ላይ የሚጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ልክ እንደ ተጨማሪ እሴት ታክስ በተመሳሳይ መልኩ ይከናወናል። የኤክሳይዝ ታክሱ ለተጠቃሚው በሚሰጠው ደረሰኝ ላይ የሚጨመር ሲሆን ይህን ተከትሎም የኤክሳይስ ታክሱ በታክስ ማስታወቂያው ይገለፃል።

### 3.13.3. ስጋቶች

ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ዋነኛው ስጋት ሁሉም ታክስ የሚከፈልባቸው እንቅስቃሴዎች በታክስ ማስታወቂያ የተገለፀ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው።

ለምሳሌ፣ ነፃ የአየር ሰዓት ለተጠቃሚዎች በሚሰጥበት ጊዜ ምንም እንኳን በተጠቃሚው ላይ ወጪ ባይኖርም፣ ይህ ነፃ የአየር ሰዓት የንግድ ውሳኔ (commercial decision) ነው፤ በመሆኑም ልክ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ነፃ ናሙናዎች በሚቀርቡበት አኳኋን ነፃ የአየር ሰዓቱም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል።

### 3.13.4. የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቶች

የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱ በኤሌክትሮኒክ ሲስተም አማካይነት የሚካሄድ ይሆናል።

በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ በሚገኙበት ጊዜ የአሠራር ሥርዓቱን በሚገባ ይመልከቱ እና የታክስ ማስታወቂያው እንዴት እንደሚዘጋጅ ይረዱ።

የሚያቀርቧቸው ተግባራት ዓይነቶች በሲስተሙ ውስጥ በኮዶች እና በማጣቀሻ ቁጥሮች አማካይነት ይለያሉ።

የተለያዩ ኮዶችን ይገምግሙ እና እያንዳንዱ ኮድ የኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልበት አገልግሎት ጋር የተገናኘ መሆኑን ያረጋግጡ።

### 3.13.5. ነፃ የአየር ሰዓት

ነፃ የአየር ሰዓት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ነው። ስለዚህ ሁሉንም የነፃ የአየር ሰዓት አቅርቦቶች በመገምገም የኤክሳይዝ ታክሱ በዚህ አገልግሎት ላይ በመዝገብ የተያዘ መሆኑን እና መከፈሉን ያረጋግጡ።

ምንም እንኳን በተጠቃሚው ላይ ምንም ወጪ ባይኖርም ለእያንዳንዱ ሽማች የሚሰጠውን ነፃ የአየር ጊዜ መጠን መከታተል ስለሚያስፈልጋቸው የአየር ጊዜ አቅርቦቱ በቴሌኮም ኩባንያው መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል።

### 3.13.6. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቅጂ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ነዳ የአየር ሰዓት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በመሆኑ ሁሉንም የነዳ የአየር ሰዓት አቅርቦቶች በመገምገም የኤክሳይዝ ታክሱ በዚህ አገልግሎት ላይ በመዘገብ የተያዘ መሆኑን ያረጋግጡ።

በሲስተሙ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለውን እያንዳንዱን ኮድ በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ እና በእያንዳንዱ ኮድ የቀረበውን አገልግሎት ይለዩ።



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

## ምዕራፍ 4፡ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች(working notes)

### 4.1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በሂደቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉት የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

- ከኢንስፔክሽን በፊት እቅድ ማዘጋጀት፤
- ከኢንስፔክሽን በፊት የመረጃ ትንተና፤
- በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ የሚከናወኑ ተግባራት፤
- ከኢንስፔክሽኑ በኋላ ግኝቶችን ሪፖርት ማድረግ፡፡

ይህ ምዕራፍ አጠቃላይ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶችን ቅርፅ የሚመለከት ሲሆን ምዕራፍ አምስት ከላይ በምዕራፍ ሦስት የተዘረዘረውን እያንዳንዱን ዓይነት ኢንስፔክሽን በምሳሌ ለማሳየት የሥራ ማከናወኛ ሰነዶችን ለሥራ ተስማሚ በሚሆኑበት አግባብ ያቀርባል፡፡

### 4.2. የኤክሴል ሠንጠረዥ

እነዚህ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች በኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ፣ በዕቃ ቆጠራ ቅጽ፣ በዋጋ ዝርዝር እና እቃን ከወጪ ሀገር ማስገባት / ወደ ውጪ ሀገር በመላክ ላይ በግብር ከፋዩ የቀረበን መረጃ በኤክሴል መዝግቦ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

ለእያንዳንዱ ተገቢ የኢንስፔክሽን ዓይነት የኤክሴል ሠንጠረዥ የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

እነዚህ የኤክሴል ሠንጠረዦች ከተገቢው የፀደቀ ቅጽ ተገቢውን መረጃ የያዙ የአምድ ርዕሶች (column headings) አላቸው፡፡

የኤክሴል ስፕሪድሺቶች በወርድ ዶኩመንት (word document) ከተዘጋጀው ዋናው የአሠራር መመሪያ ተነጥለው መቀመጥ ስላለባቸው፣ ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቡድን መሪ ይቀርባሉ፤ እንዲሁም በእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን የእቅድ ዝግጅት ወቅት እነዚህ ሰነዶች ኢንስፔክሽኑን ለሚያካሂደው ቡድን የሚሰጡ ይሆናል፡፡

### 4.3. የሥራ ማከናወኛ ሰነዶቹን / የኤክሴል ሠንጠረዦቹን ለሥራ ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ

እያንዳንዱ ግብር ከፋይ መዝገቦችን በተለየ መንገድ እንደሚይዝ እና የተለያዩ የአመራረት ሂደቶችን እንደሚከተል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መሠረት የኢንስፔክሽን ሥራውን የሚያከናውኑ ኦፊሰሮች የሥራ ማከናወኛ ሰነዶቹን ለሥራው ተስማሚ እንዲሆኑ አድርገው ማስተካከል እና የኢንስፔክሽን ሥራውን የሚደግፉ የኤክሴል ሠንጠረዦችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ዐ.ተ. መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በተመሳሳይ ሁኔታ አፊሰሩ ከሚካሄደው የኢንስፔክሽን ዓይነት ጋር በሚጣጣም መልኩ በሠንጠረገጮቹ ውስጥ አምዶችን (columns) ሊጨምር ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

እነዚህ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች እና የኤክሴል ሠንጠረገጮች "መይቀር የማይችሉ" አለመሆናቸውን እና ይበልጥ ትክክለኛ የኢንስፔክሽን ሪፖርት ለማቅረብ እንዲቻልም ለበጎ ዓላማ ለሥራው ተስማሚ እንዲሆኑ ተደርገው መስተካከል የሚችሉ መሆናቸውን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው።

### 4.4. ከኢንስፔክሽኑ በፊት ጥቅም ላይ የሚውሉ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች

ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ያሉት የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ወደ ግብር ከፋዩ ከመኪዱ በፊት በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ውስጥ ተሞልተው የሚጠናቀቁና ለሁሉም/ለአብዛኛዉ የኢንስፔክሽን አይነቶች የሚያገለግሉ ሲሆኑ ሌሎች በክፍል 5 ስር የተገለጹ ናቸው።

### የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 1፡ ግብር ከፋዩን እና የጀርባ ታሪኩን መረዳት ቅጽ

| | |
|---|---|
| 1. የግብር ከፋይ ስም | |
| 2. የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቁጥር | |
| 3. የኢንስፔክሽኑ ዓይነት | |
| 4. ኢንስፔክሽኑ የሚወስደው ቀን (ከ. . .እስከ) | |
| 5. ኢንስፔክሽኑን ለማካሄድ የታቀዱት ቀናት | |
| 6. ሥራዎች የሚከናወኑባቸው ቦታዎች | |
| 7. የሚጎበኙ ቦታዎች፡ (የሒሳብ ባለሙያ ወይም የማምረቻ ቦታ) | |
| 8. መከናወን ይችላሉ ተብለው በፈቃዱ ላይ የተመለከቱ ሥራዎች | |
| 9. የሚመረቱት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች | |
| 10.የምርት ዓይነቶች/ብራንዶች ዝርዝር | |
| 11.በግብር ከፋይ ማህደር ውስጥ የሚገኝ የቦታው ፕላን፡- ቦታውን ተዘዋውሮ ለመጎብኘት የፕላኑን ቅጂ መያዝዎን ያረጋግጡ። | |
| 12.ኢንስፔክሽን/አዲት ለመጨረሻ ጊዜ የተካሄደበት ቀን | |
| 13.ኢንስፔክሽኑ/አዲቱ የሚያተኩርበት ጉዳይ | |
| 14.ለመጨረሻ ጊዜ ከተካሄደው ኢንስፔክሽን/አዲት የተገኙ ግኝቶች/ምክረ-ሃሳቦች | |
| 15.የፀደቁ ቅጾች፡- ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ሁሉም የታክስ ማስታወቂያዎች፣ የዕቃ ቆጠራ ቅጾች እና የዋጋ ዝርዝሮች ቀርበዋል? | |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| 16.እህትማማች ድርጀቶች ዝርዝር | |
| 17.ግብአት የሚያገኝበቸዉ መንገዶች | |
| 18.ምርቶች የሚሸጡበት/የሚተላለፉበት አግባብ | |
| 19.የቡድን መሪው ስም | |
| 20.ለኢንስፔክሽኑ የተመደቡ ኦፊሰሮች ስም | |
| 21.የገምጋሚው ስም | |
| 22.ቀን | |

የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 2፡ መረጃ መሰብሰብ እና መተንተን ቅጽ

የመረጃ ምንጮቹን በመለየት ሁሉንም መረጃ ወደ ተገቢው የኤክሴል ሠንጠረዥ ያስገቡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ግብር ከፋይ | |
| 2. የኢንስፔክሽኑ ዓይነት | |
| 3. ቀን | |
| 4. የኦፊሰሩ ስም | |
| 5. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት | |
| 6. የመረጃ ምንጮች | የማስታወቂያ ቅጽ (ዳታ ዌርሃውስ)<br>የዕቃ ቆጠራ<br>የዋጋ ዝርዝር<br>ወደ ሀገር ውስጥ የገባበትና ወደ ዉጭገር የተላከ ምርት መረጃ |
| 7. የመረጃው አቀራረብ ትክክለኛነት፡- የመረጃ አቀራረቡን በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ፡፡ መረጃው በግልፅ ሊነበብ | በቀረቡት ቅጾች ላይ የሚታዩ ሁሉንም ችግሮች በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ፡፡ |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | |
|---|---|
| ይችላል? ሁሉም የሠንጠረዡ ክፍሎች በትክክል ተሞልተዋል? | |
| 8. መረጃዎችን ኤክሴል ማደራጀት | ሁሉንም ተገቢ መረጃዎች ወደ ተገቢው የኤክሴል ስፕሪድሺት ያስገቡ፡፡ |
| 9. የመረጃ ትንተና | ሁሉንም ትንተናዎች በየኢንስፔክሽኑ መሠረት ለማቅረብ የኢንስፔክሽኑን የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች ይጠቀሙ፡፡ |

የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 3፡ ከመረጃ ትንተና የተገኙ ግኝቶች ቅጽ

የመረጃ ትንተናውን በማጠቃለል ማናቸውም ችግር የሚታይባቸውን ቦታዎች ይለዩ፡፡ ይህም በቦታው ላይ የሚካሄደው ኢንስፔክሽን በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ያስችላል (በምዕራፍ 3 *መመሪያዎች* መሠረት)፡፡

| | |
|---|---|
| **የኩባንያው ስም** | |
| **የኩባንያው የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥር** | |
| **ከታች ባለው ክፍት ቦታ ውስጥ ከትንተናው የተገኙ ግኝቶችን ይጻፉ፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ የኤክሴል ገጾችን ይጠቀሙ፡፡** | |
| በኤክሴል ውስጥ ከገባው መረጃ እንዲሁም ከግብር ከፋዩ ማህደር የተገኙ ግኝቶችን ይዘርዝሩ፡፡ | የኢንስፔክሽን አይነት |
| ምሳሌ፡-ድርጅቱ ለአንድ ብራንድ የተለያዩ ሶስት አይነት ዋጋ በዋጋ ማቅረቢያ ላይ ያቀረበ በመሆኑ የሚጠራ | የዋጋ ኢንስፔክሽን |
| የወራቶች የመጨረሻ ምርት መጠን ካላፈዉ ወር የዞረዉ በወሩ የተመረተዉ ተደምሮ የባከነዉ/የተበላሻዉ ተቀንሦ ከምገኘዉ መጠን ጋር ሰለማይጣጣም ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ | የወጪ ምርት ኢንስፔክሽን |
| ሌሎችን ይጨምሩ | |

**የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 4 ፡ ለአጠቃላይ አመታዊ ዕቅድ የኤክሳይዝ ታክስ ስጋት መለያ ቅጽ**



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| ተቁ | የድርጅቱ ስም/ ቲን | የሲጋት መገምገምያ መስፈርት | የሲጋት ደረጃዉ (ከፍተኛ /መካከለኛ/ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | አአአ | የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በምዝገባ ወቅት ከማመልከቻ ፎርማቱ ጋር መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች በኤክሳይዝ ህጉ መሠረት ሳያሟላ ከአንድ ወር በላይ የቆየ | ከፍተኛ |
| | | ግብር ከፋዩ ባለፉት 6 ወራት መገብኘቱንና አስፈላጊዉን ማስተካከያዎች መዉሰዱን ማጣራት (ካተገበኘ ወይም አስፈላጊዉን የማስተካከያ እርምጃ ካልተወሰደ) | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ ባለፉት 3 ወራት ፈቃድ ወስዶ ያልተጎበኘና አዲስ ከሆነ | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ ባለፉት 2 ዓመታት ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች በጊዜው ማቅረቡንና በትክክል ተሞልቶ የቀረበ መሆኑን ማጣራት (ከሲድስት ወር ባለይ ለሆነ ጊዜ ካለቀረበ) | ከፍተኛ |
| | | ግብር ከፋዩ ሁሉንም ኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ በጊዜው የከፈለ መሆኑን ማጣራት (ከሶስት ወር በላይ አሳዉቆ ያልተከፈለ ታክስ ካለ) | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ የዕቃ ቆጠራ እና የዋጋ ዝርዝር ቅጾችን በጊዜው ማቅረቡን ማጣራት (ከሁለት ወር በላይ ሳያቀርብ የቆየ ከሆነ) | ከፍተኛ |
| | | በታክስ ከፋዩ የቀረበዉ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ እና የዋጋ ዝርዝር በትክክል የተሞሉ፣ ግልጽና ትክክል መሆናቸዉን ማጣራት(ችግር ካለዉ) | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ ባለፉት 12 ወራ ዉሥጥ አዳዲስ ዳይሬክተሮችን ጨምሮ የመዋቅር ለውጥ አድርጓል ማድረጉን ያጣሩ (አድርጎ ከሆነ) | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ ለጊዘዉ ማምረት መቆሙን፣አድራሻ ላዉጥ ማድረጉን በማሳወቅ ታክሱን ከአንድ ወር በላይ የሞላቸዉ | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ ለጊዘዉ ማምረት መቆሙን ሳያሳዉቅ (ድርጅቱ ሳይዘጋ) ዜሮ የሚያሳዉቁ | |
| | | ታክስ ከፋዩ የሚያሳወቀዉ ወደ ወጪ የሚላከዉ ፣የተበላሹና የጠፉ ምርቶችናሌሎች ኤክሳይዝ የማይከፈልባቸዉ ምርቶች የአመቱ አማካይ መጠን ከ10 በላይ ሲሆን | ከፍተኛ |
| | | ታክስ ከፋዩ በግብር ዘመኑ የሚያሳወቀዉ አጠቃላይ የአመቱ ኤክሳይዝ ታክስ መጠን ከለፈዉ አመት የታክስ መጠን ከ10 በታች ከሆነ | ከፍተኛ |
| | | ሌሎች | |
| | | አጠቃለይ የሲጋት ደረጃ | ከፍተኛ |
| 2 | | | |

**የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 4.1 ለአጠቃላይ አመታዊ ዕቅድ የሚመረመሩ (ኢንስፔክት የሚደረጉ) ድርጅቶች መመዘኛ ቅጽ**

በኢንስፔሽን ማነዋሉ 2.1.1 መሰረትና ከለይ በሰንጠረዥ 4 በተገለ ጸዉ ሁኔታ ሲጋት ያላቸዉ ድርጅቶች በስጋት ደረጃቸዉ ተጣርተዉ ከተለዩ በኃላ እንስፔክሽን ለማካሄድ ድርጅቶችን በቀደምትነት ለማስቀመጥ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ነጥብ ከተሰጠ በኃላ አጠቃላይ የነጥብ ድምር ብልጫ መሰረት መጀመሪያ ከፍተኛ ስጋት ያለቸዉ ጨርቃጨቅ ፋብሪካ፣ቀጥሎ ከከፍተኛ ሲጋት ካላቸዉ አልኮል ከዚያም ለሎች



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ምርቶች ከፍተኛ ሲጋት ያለቸዉን በማስቀደም ቁጥሉ ወደ መካከለኛ ስጋትና ከዚያም ወደ አነስተኛ ሲጋት በመሻገር እንደ ሲጋት ደረጃቸዉና ነጥባቸዉ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ በአመቱ መጀመሪያ እንደ ድርጅቱ ዉስብስብነትና ስፋት ደረጃ ታይቶ ለሙያተኞች የሚደለደሉ ይሆናሉ። ይህ አቅድ አንደ ሁኔታዉ እየተገመገመ በየወሩ ወይም ሩብ አመቱ ልከለስ የሚችል ሆኖ አስፈላጊ ከሆነ አንድ ድርጅት ከአንድ ጊዜ ባለይ ልታይ የሚችል መሆኑን መገንዘብ የስፈልጋል።

የግብር ካፋይ ስም ----------ኤክሳይዝ ታክስ ቁጥር---------- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር-------

| ተ ቁ | መሰፈርት | አጠቃላይ ነጥብ | የስጋት ደረጃ | የሚሰጥ ነጥብ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 10 | 8-9 | 6-7 | 1-5 |
| 1 | የገቢ /ሽያጭ መጠን | 10 | ከፍተኛ ግ/ከ | 1 ቢልዮን በላይ | 500 ሚ-900 ሚ | 100ሚ-500ሚ | 900 ሺ በታች |
| | | | መካከለኛ ግ/ከ | ከ10 ሚ በላይ | 2ሚ-9 ሚ | 500 ሺ - 1ሚ | 400 ሺ በታች |
| | | | ዝቅተኛ/ግ/ከ | ከ 1ሚልዮን በላይ | 200 ሺ - 1ሚ | 100ሺ-50 ሺ | 40ሺ |
| 2 | የታክስ ማስታወቂያው የቀረበ እና የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ | 10 | ከፍተኛ ግ/ከ | 100 ሚልዮን በለይ | 10ሚ-900ሚ | 1ሚ-98ሚ | 800 ሺ በታች |
| | | | መካከለኛ ግ/ከ | ከ1ሚልዮን በለይ | 200ሺ-900ሺ | ከ50 ሺ-800ሺ | 49 ሺ በታች |
| | | | ዝቅተኛ/ግ/ከ | 100 ሺበላይ | 50-99ሺ | 10-40ሺ | 9ሺ በታች |
| 3 | ለመጨረሻ ጊዜ ኢንስፔክት የተደረገበት ጊዜ | 10 | | ኢንስፔክት ተደርጎ የማያውቅ | ከ1 ዓመት በፊት ኢንስፔክት ከተደረገ | 6-12 ወራት ውስጥ ኢንስፔክት ከተደረገ | በ6 ወራት ውስጥ ኢንስፔክት ከተደረገ |
| 4 | በቅርቡ አዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ | 10 | | አዲት ተደርጎ የማያውቅ ከሆነ | ከ1 ዓመት በፊት አዲት ከተደረገ | ከ6-12 ወራት ውስጥ አዲት ከተደረገ | በ6 ወራት ውስጥ አዲት ከተደረገ |
| 5 | ፈቃድ የተሰጠበት ጊዜ | 10 | | ፈቃድ የተሰጠው ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ከሆነ | ፈቃድ የተሰጠው ባለፉት ከ3-6 ወራት ውስጥ ከሆነ | ፈቃድ የተሰጠው ከ6-12 ወራት በፊት | ቃድ የተሰጠዉ ከ አንድ አመት በፊት ከሆነ |
| | **አጠቃላይ ነጥብ ድምር** | **50** | | | | | |

**የሥራ ማከናወኛ ሰነድ5፤የሙያ ስኔ ምግባር መከታተያ ቅጽ (CODE OF ETHICS)**

**የተመርማሪ ድርጅት ስም፡-**_____

**የኢንስፔክሽን አይነት፡-** _____

**የምርመራዉ የሂሳብ ጊዜ**_____

**ለዚህ ድርጅት ምርመራ ዓለማና ጊዜ፡-**



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ★ የሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

1.እኔ ራሴ ወይም የእኔ የቅርብ ቤተሰቤ አባላት (የድርጅቱ ስም ይጠቀስ) ጋር ምንም ዓይነት የገንዘብ ጥቅም/ድጋፍ እንደሌላቸው አረጋግጣለሁ።
2.እኔ ምርመራ ከሚደረገዉ አካል ወይም ከማንኛውም ዳይሬክተሮች፣ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ጋር የንግድ/የሰራ ግኑኝነት የለለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ።
3.እኔ ባለፉት ሁለት የፋይናንስ ዓመታት ውስጥ ተቀጣሪ ሰራተኛ፣አፊሰር ወይም ዳይሬክተር አለመሆኔ እና የተመርማር ድርጅቱ አካል ያልነበርኩ መሆኔን አረጋግጣለሁኝ።
4.ምርመራ በተደረገው የሒሳብ ዓመት በአሁኑ ጊዜ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብና የመቆጣጠር ሥራ የሚይዝ ወይም ይህን የመሰለ የሥራ ቦታ የሚይዝ የቅርብ ወይም የቅርብ የቤተሰብ አባል የለለኝም መሆኑን አረጋግጣለሁ።
5.ነፃነቴን ሊጎዳ የሚችል የድርጅቱ ዳይሬክተር እና ሰራተኛ ሆኖ ከምመረመረዉ ነገር ጋር ግኑኝነት ካለቸዉ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለለኝ መሆኔን አረጋግጣለሁኝ።
6. በገቢዎች ሚኒስቴር ሰኔ ምግባር ደንብ እና አለምአቀፍ የሂሳብና ኢዲቴሮች የሥነ ምግባር ደንብ ውስጥ ያሉትን መስፈርቶች እረዳለሁ፡-
6.1 ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ፣ በሙያዊ መንገድ እና በተቻለኝ አቅም ኢንስፔክሽንን ማከናወን አለብኝ።
6.2 ኢንስፔክሽንን በሐቀኝነት፣ በታማኝነት፣ ባለማዳላት እና በፖለቲካ ገለልተኛነት ማከናወን አለብኝ።
6.3 በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኘውን የመረጃ ሚስጥራዊነት መጠበቅእና በዙህ አይነት የተገኘዉን መረጃ ለሶስተኛ ወገኖች ፡ መግለጽ የሌለብኝ መሆኑን አረጋግጠለሁ።

ከላይ ለኢንስፔክሽን የተዘረዘሩ የስነምግባር መግለጫዎች ጋር ያለኝን ተገዢነት ሊያበላሹ የሚችሉ ሁኔታዎች፡---(ካለ ይግለጹ ከለለ ምንም በሉ)

መግለጫ (Declaration)
እኔ፣ ከታች የተፈረምኩት በሥነ ምግባር ህጉ ውስጥ የተካተቱትን መስፈርቶች እና ኃላፊነቶች ሙሉ በሙሉ ተረድቻለሁ። ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተገዢነቴን ሊያበላሹ የሚችሉ ሁኔታዎችን መዝግቤያለሁ።
የቡድኑ አባል ስም:_____
ደረጃ_____ፊርማ_____

ለኢንስፔክሽን ሰራ የተሰጠ መደምደሚያ ( CONCLUSION FOR THE INSPECTION)
በቡድንአባላት የተለዩ ስጋቶች፡-
_____
ስጋቶችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች :-
_____
_____
_____
ከላይ የተዘረዘሩትን የኦዲት ቡድኑ መግለጫዎች እና ከቡድን አባላት ጋር የተደረጉ ቃለመጠይቆችን ከግምት ውስጥ ካስገባሁ በኋላ፣ በሙያዊ የሂሳብ ባለሙያዎች የሥነ ምግባር ደንብ ውስጥ የተካተቱት ሁሉም መስፈርቶች ለኢንስፔክሽን ተሳትፎ የተሟላ መሆኑን አረጋግጣለሁ። የኢንስፔክሽን ቡድኖችን ነፃነት ጋር የሚጋጩ ሚናቸውም ስጋቶች ተወግደዋል ወይም ተቀባይነት ወዳለው ደረጃ ዝቅ ተደርገዋል። ለሪፖርቱ ኃላፊነት ያለው ሰው ስምና ፊርማ_____ ቀን_____



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የሥራ ማከናወኛ ሰነድ6፡ የኢንፔክሽን ዕቅድ ቅጽ

| | |
|---|---|
| **የኩባንያው ስም** | |
| **የኩባንያው የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥር** | |
| **የተዘጋጀበት ቀን** | |
| **ለስራዉ የተመደቡ ሙያተኞች ስምና ፊርማ** | 1_____<br>2_____ |

| **የኢንስፔክሽን አይነት** | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ የጊዜ ግምት በቀን |
|---|---|
| የየኤክሳይዝ ፈቃድ አሰጣጥ ኢንስፔክሽን | |
| የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውለው ዋጋ ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | |
| የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና ትርጉማቸዉ | |
| የጥሬ ዕቃ ኢንስፔክሽን፡- ከውጭ የሚገቡ እና የሀገር ውስጥ | |
| የመጨረሻ ምርት / የምርት ውጤት ኢንስፔክሽን | |
| የባከኑ ወይም የጠፉ/የተበላሹ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | |
| ማምረቻ እና ማሸጊያ | |
| የመለኪያ እና መቁጠሪያ መሣሪያ/የርቀት መከታተያ | |
| ከማሸጊያ እስከ ማከማቻ | |
| ከፋብሪካ ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎች ኢንስፔክሽን | |
| የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን | |

ዕቅዱን ያረጋገጠዉ ኃላፊ ስም_____ ፊርማ _____ቀን_____



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁጥር 1 ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 4.5. ግብር ከፋይን ስለማሳወቅ (Notify Taxpayer)

የኢንስፔክሽን ሥራው ሊካሄድ ከታሰበበት ቀን ቢያንስ 10 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ስለኢንስፔክሽኑ እና በኢንስፔክሽኑ ወቅት እንዲቀርቡ ስለሚፈለጉት መዝገቦች/ሰነዶች ለግብር ከፋዩ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

ይህም ግብር ከፋዩ ሁሉንም አስፈላጊ መዝገቦች/ሰነዶች እንዲያሰባስብ ጊዜ የሚሰጥ ሲሆን ኢንስፔክሽኑም በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል።

ግብር ከፋዩ ሆን ብሎ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያን በፀደቁ ቅጾች ላይ ዝቅ አድርጎ ያሳውቃል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ድንገተኛ ፍተሻ ሊደረግ ይችላል። ነገር ግን ተመራጭ የሆነው ዘዴ አስቀድሞ ማቀድ ነው።

### 4.6. በግብር ከፋዩ የሥራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ የስራ ማከናወኛ ሰነዶች

የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 5፡ የኢንስፔክሽን ማስታወሻ (Query)

የኩባንያው ስም፡ _____ የሂሳብ ባለሙያው/የታክስ ኦፊሰሩ ስም፡ _____

የኢንስፔክሽኑ ጊዜ፡ ከ _____ እስከ _____

የኢንስፔክሽኑ ዓይነት፡ _____

የረዳት ኢንስፔክተሩ ስም፡ _____

ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ኢንስፔክተር ስም፡ _____

| ተ.ቁ | ማስታወሻ (የሚጣራ ምልከታ) | የተጠናቀቀበት አግባብ |
|---|---|---|
| | **የኢንስፔክተሩን መግለጫ እና ግኝት እዚህ ይጻፉ።** | በምርመራ ላይ ያለው ኩባንያ የሰጠውን ምላሽ እና የኢንስፔክተሩን ማጠቃለያ ሃሳብ እዚህ ይጻፉ። |
| 01 | **ለምሳሌ፡-** በደረሰኝ ቁጥር ከ00100 እስከ 00200 ላይ ያለው ካስትል ቢራ ለግንቦት ወር 2017 ዓ.ም ከእንግሊዝ በመጣ ብቅል 2000 ሊትር የተመረተ ሲሆን ዋጋውም በሊትር 40 ብር ነው። የኤክሳይዝ ታክሱ የተሰላው ብቅሉ በሀገር ውስጥ እንደተመረተ ተደርጎ በ30% ቅናሽ የማስከፈያ መጠን ነው። ነገር ግን በቁርጥ የተሰላው የኤክሳይዝ መጣኔው በኤክሳይዝ ታክስ መመሪያ ቁጥር 1007/2016 መሠረት በሊትር 28 ብር ነው።<br>**<u>ግኝት</u>** | **የግብር ከፋይ ምላሽ፡-** አዎ በስህተት የተፈፀመ ነው።<br>**ፌርማ እና ቀን**<br><br>**የኢንስፔክተሩ ማጠቃለያ፡-**<br>ግኝቱ የተሳሳተ መጣኔ በመጠቀም ኤክሳይዝ ታክስን በማሳነስ የተከፈለ በሚል የግኝት ሪፅስ ስር የሚጠቃለል በማለት ሃሳቡን መግለጽ አለበት። |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

| | | |
|---|---|---|
| | በተጠቀሰው ወር የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያው የቀረበው 40% ወይም 28 ብር ከሁለቱ አንዱ የበለጠውን የማስከፈያ መጠን ወደ 30% ዝቅ በማድረግ ነው። ዝቅ ተደርጎ የተገለፀው 28 ብር በሊትር 40 ብር ከሆነው 40% ጋር ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም 16 ብር ነው። ስለዚህ ዝቅ ተደርጎ የተገለፀው የኤክሳይዝ ታክስ (28-16)*2000 =24000 ብር ነው።<br>**ፊርማ እና ቀን** | **የኢንስፔክተሩ ፊርማ እና ቀን** |
| 02 | | |
| 03 | | |

**ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ኢንስፔክተር ፊርማና ቀን----------**

**የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 5.1 ፡ የግኝት ማጠቃለያ ቅጽ**

ሁሉንም የተከናወኑትን የኢንስፔክሽን ሥራዎች ግኝቶችን በኢንስፔክሽን ማስታወሻ ተይዘዉ ለግብር ከፋዩ በማሳወቅ ግኝቶቹ ሲጠናቀቁ ሪፖት መደረግ ያለባቸዉን ተመሳሳይ ግኝቶችን ለማጠቃለል ሪፅስ መስጠት ያስፈልጋል ። በመሆኑም በሚሰጠዉ ሪፅስ መሰረት በማጠቃለል እንዲፈርም ማድረግ አስፈላጊ ነው።በግብር ከፋዩ መስፈረም የግኝት ማስታወሻ ላይ ከፈረሙ የግድ ላይሆን ይችላል፡

የኩባንያው ስም፡ _____ የሂሳብ ባለሙያው/የታክስ አፊሰሩ ስም፡ _____

የኢንስፔክሽኑ ጊዜ፡ ከ _____ እስከ _____

የኢንስፔክሽኑ ዓይነት፡ _____

የረዳት ኢንስፔክተሩ ስም፡ _____

ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ኢንስፔክተር ስም፡ _____

ቀን፡ _____

| ተ.ቁ | የኢንስፔክሽን ዓይነት | የግኝት አርዕስት | የማመሳከሪያ ቁጥር (የማስታወሻ ቁጥር) | ታክስ የሚሰላባት የብር መጠን | ሳያስታውቁ የቀሩት የኤክሳይስ ታክስ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምሳሌ፤ የዋጋ ኢንስፔክሽን | ዋጋን አሳንሶ ማስታወቅ | ግኝት 1 | ዋጋ በማሳነስ የተገኘ የብር መጠን XXX | |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነቱ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ኢንስፔክተሮች ስምና ፊርማ፡-

1._____ _____

2._____ _____

የድርጅቱ፡-1. የታክስ ኦፊሰሩ ስም፡ _____ _____

2. የሂሳብ ባለሙያው ሰራተኛዉ ስም_____ፊርማ ____

ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ኢንስፔክተር ፊርማና ቀን----------

ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ የተጠቀሱት መረጃዎች በሙሉ ትክክልመሆናቸውን እናረጋ

የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 6፡ የምርት/ዕቃ ከወጪ ቀሪ ማመሣዘን

ለሥራ ማከናወኛ ሰነድ 6 ከዚህ በታች የቀረበትን ምሳሌ በመጠቀም በኢንስፔክሽን ጊዜ በቆጠራ የተገኘዉን ምርት/ዕቃ ደርጅቱ ከሚይዘዉ የመዝገብ ከወጪ ቀር (stock record balnce) ጋር ጋር በማመሣዘን የሚከናወን የኢንስፔክሽን ሥራ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ የኢንስፔክሽን ተሣማጅ የሆኑ መረጃዎችን ከዚህ በታች በተገለጸ ፎርማቶች ከድርጅቱ መተማመኛ መዉሰድ ያስፈልጋል (የመዝገብ ከወጪ ቀር ቅጽ፣የምርት/ዕቃ ቆጠራ ቅጽ፣ እና ሳይመዘገብ የተገኘ ገቢ ና ወጪ ምርት/ዕቃ ቅጽ) እንደሚከተሉት በ ምሳሌ ተካተዋል፡፡

**6.1 የምርት/ዕቃ መዝገብ ከወጪ ቀር ቅጽ**

የድርጅቱ ስም_____

የሩብሪካዉ ቦታ_____የመጋዘን ሰም_____
የመጋዘን ቦታ_____ ቀን_____

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | የምርት ኮድ | መለኪያ | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቦክሰር (BOXER) 100CC | 1702 | ቁጥ | 265 |
| 2 | | | | |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ ዉስጥ የተገለጹት መረጃዎች ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

**<u>ኢንስፔክተሮች ስምና ፊርማ፡-</u>**

1._____ _____

2._____ _____

**የድርጅቱ**፡-1. የሂሳብ ባለሙያው/የታክስ ኦፊሰሩ ስም፡ _____ _____



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 የታክስ መዛግብትና ሰነዶች ማዕከል
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

2. የንብረት ያዥ ሰራተኛዉ ስም_____ፊርማ _____

**6.2 የምርት/የዕቃ ቆጣራ መተማመኛ ቅጽ**

የድርጅቱ ስም_____

የሩብሪካዉ ቦታ_____የመጋዘን ሰም_____
የመጋዘን ቦታ_____

የቆጠራዉ ቀን_____

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | የምርት ኮድ | መለኪያ | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቦክሰር (BOXER) 100CC | 1702 | ቁጥ | 14 |
| | | | | |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ ዉስጥ ለተገለጹት መረጃዎች ትክክል መሆኑንና በናሙና ከተወሰዱት ለላ ያልተቆጠሬ አለመኖሩን እናረጋግጣለን፡፡

**<u>ኢንስፔክተሮች ስምና ፊርማ፡-</u>**

1._____ _____

2._____ _____

**የድርጅቱ**፡-1. የሂሳብ ባለሙያው/የታክስ አፊሰሩ ስም፡ _____ _____

2. የንብረት ያዥ ሰራተኛዉ ስም_____ፊርማ _____

**6.3 ሳይመዘገብ የተሸኘ ገቢና ወጪ ምርት/ዕቃ መተማመኛ ቅጽ**

የድርጅቱ ስም_____

የሩብሪካዉ ቦታ_____የመጋዘን ሰም_____የመጋዘን
ቦታ_____ቀን_____

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | የምርት ኮድ | የሰነድ ቁጥር | መለኪያ | ገቢ | ወጪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቦክሰር (BOXER) 100CC | 1702 | 00049 | ቁጥ | 1494 | | |
| 2 | | | 10004 | | | 1679 | |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ ዉስጥ የተገለጹት መረጃዎች ትክክል መሆኑንና ለላ በናሙና ለተመረጡት ምርቶች/ዕቃ ያልተመዘገበ ገቢና ወጪ የለለ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሬኮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

**ኢንስፔክተሮች ስምና ፊርማ**

1._____ _____

2._____ _____

**የድርጅቱ፡-1**. የሂሳብ ባለሙያው/የታክስ አፊሰሩ ስም፡ _____ _____

2. የንብረት ያዥ ሰራተኛዉ ስም_____ፊርማ _____

**6.4 የዕቃ ቆጠራና መዝገብ ማመሣከሻ ቅጽ**

የድርጅቱ ስም_____

የፋብሪካዉ ቦታ_____የመጋዘን ሰም_____
የመጋዘን ቦታ_____ ቀን_____

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | የምርት ኮድ | መለኪያ | የመዝገብ ሚዛን (ሀ) | ሳይመዘገብ የገባ (ለ) | ሳይመዘገብ የወጣ (ሐ) | የተስተካከለ የመዝገብ ሚዛን (መ)= (ሀ + ለ-ሐ) | የተቆጠረ ዕቃ (ሠ) | ልዩነት ረ= (መ-ሠ) | | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | ትርፍ የመጣ | የጎደለ | |
| 1 | ቦክሰር (BOXER) 100CC | 1702 | ቁጥር | 265 | 1494 | 1679 | 80 | 14 | | 66 | |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ ዉስጥ የተገለጹት መረጃዎችና ማመሣከሻዉ ትክክል እናረጋግጣለን፡፡

**<u>የኢንስፔክተሮች ስምና ፊርማ፡-</u>**

1._____ _____

2._____ _____

**የድርጅቱ፡**-1. የሂሳብ ባለሙያው/የታክስ አፊሰሩ ስም፡ _____ _____

2. የንብረት ያዥ ሰራተኛዉ ስም_____ፊርማ _____



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

### 6.5 ፡ ለሎች መተማመኛዎች

ሁሉንም የተከናወኑ የማረጋገጫ ሥራዎችን በግኝት ማስታወሻ በመያዝ የምርት/የእቃ ማመላዘኛ ሰንጠረዥ ዉሥጥ ሌላ አምድ መጨመር ያስፈልጋል ። ለምሳሌ በብልጫና በማነስ የተመዘገበ እና ሌሎች።

የሥራ ማከናወኛ ሰነድ 7፡ የኢንስፔክሽን ሪፖርት

ኢንስፔክተሮች ወደ ቅርንጫፉ ቢሮ ሲመለሱ ስለተከናወኑት ተግባራት፣ ስለመዝገቦቹ ጥራት በግብር ከፋዩ ስለተደረገለት የስራ ትብብር፣ ግኝቶችና የማስተካከያ እርምጃ፣ ስለ ድርጅቱ የዉሥጥ ቁጥጥር ጥንካሬና ድክመት እና ስለ መረጃዎች አያያዝ በማጠቃለያ ሪፖርት ያዘጋጁሉ።

| የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ሪፖርት ተምፕለት | |
|---|---|
| **የድርጅቱ ስም** | |
| **የኩባንያው የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥር** | |
| **የኢንስፔክሽን ጊዜ** | |
| **የመርማሪዎች ስም** | 1_____<br>2_____ |
| **ሪፖረቱን የከለሰዉ** | |
| ማጠቃለያ (excutive summery)<br>..... | |
| 1.መግቢያና ወሰን (introduction &scope)<br>..... | |
| 2.የምርመራ ዘዴ(methodology)<br>..... | |
| 3.ምልከታና ግኝት (Observation&findings)<br>..... | |
| 4.ምክሬ-ሃሳብ/የማስተካከያ እርምጃ (recommendations and actions needed)<br>..... | |
| 5 መደምደምያ (conclusion)<br>..... | |
| 6. አጋዥ ሰነዶች (supporting evidences)<br>..... | |
| 7.ዕዝል (appendixes) | |



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

## ምዕራፍ አምስት፡ የሥራ ማከናወኛ ሰነዶች፡ ለእያንዳንዱ የኢንስፔክሽን ዓይነት የቀረቡ ማሳያ ምሳሌዎች(Templates)

### 5.1. መግቢያ

